## ያንድ ጌታ አስተዋይነት

ድሃ... እባክዎ ጌታ ምጽዋት ያርጉልኝ፣
ችግር የበዛበት ፍጹም ድሃ ነኝ።
ጌታ... እኪሴ ያለውን የመቶ ብር ኖት፣
እስከመንዝረው ታገሠኝ ሩብ ሰዓት።
ድሃ... ጌታ ይቅርታዎን ልድፈርዎትና፣
ስንት እንደሚሰጡኝ ይንገሩኝ ለገና።
ጌታ... እኔስ የምሰጥህ አንድ ብር ነው፣
ምንዛሬ ታጣ ምን ይሁን ለዚያው፣
ድሃ... ዘጠና ዘጠኝ ብር አለኝ በምንቸት፣
እዚህ ይጠብቁኝ መጣሁ በፍጥነት፣
ይኸው ይገፍ ከተፍ አልኩኝ አሽክርዎ፣
ኖቱን ይስጡኝና ምላሹን ልስጥዎ።
ጌታ... የኔ ብልጽግና ካንተ ድኅነት፣
ባንድ ብር እኮ ነው የሚበልጥበት፣
እንካ ምክርን ልስጥህ ሥራ ሥራበት።

ያንን ያህል ያስጨነቀችኝ ይቺው ብቻ ናት። ርዝመቷ 'እጣ ሞገር' ቅኔ 'ዘአዓሠረ ንጉሥን' ታህላለች። ግን በቅኔ ደረጃ ሰምና ወርቅ የሌለባት፣ ወርቃወርቅ መሳይ ብትሆንብኝም ታሪኳ ከሥንክሣር ወይም ከመምህር አፍ ያልተገኘ የኔው የራሴ፣ ራሴ ፈልጌ ተጨንቄ ተጠብቤ ያገኘኋት መሆኑ በኔ ዓይን ታላቅ ዋጋ ተሰጥቷት ነበር። ቶሎ ብዬ ባንድ ገጽ በወረቀት ላይ ጽፌ ወደተማሪቤት ይገፍ ሄድኩና ለስም ጥሪ (ሮልኮል) ጧት ተሰልፈን ስማችን ተጠርቶ ወደየክፍላችን ልንገባ ስል ወደ ቢሮ ሄድኩ። ሙሴ እንቶንን እቢሮዋቸው ሊገቡ ሲሉ ስላገኘኋቸው ወረቀቱን ከደብተር ውስጥ አውጥቼ ስሰጣቸው ግምባራቸውን ቋጠሩ።

"እንዲሁ፣ የምን ማመልከቻ ነው? " አሉ ሙግቴን የጀመርኩ መስሏቸው።

"በጀስቴትነር ለሚባዛው የፊደል ማስተማሪያ መጽሐፍ የፃፍኩት ግጥም ነው" አልኳቸው።
ይህን ሲሰሙ ፊታቸው ፈገግ አለና ንጣቱን ትቶ ሳምባ እንደመምሰል አለ። "ጥሩ ነው፣ ጥሩ ነው... በኋላ... ቢሮ ስትመጣ እንናገራለን" አሉና ግጥሜን ይዘው ወደ ቢሮዋቸው ገቡ። እኔም ገና ግጥሙን ሳያነቡ ጥሩ ነው በማለታቸው ጥቂት ቅሬታ ቢሰማኝም፣ የፊታቸው ሳምባ መምሰል አስደስቶኝ ስሮጥ ወደ ክፍል ገባሁ። እንደተለመደው



ከሰዓት በኋላ ወደ አሥር ሰዓት ግድም እቢሮ ብሄድ የሙሴ አንቶን ፊት ከጧት ይበልጥ ሳምባ መስሎ አገኘሁ።

"እንዲሁ አንተ መንግሥቱ... እንዲሁ ይኸ ግጥም በታም ትሩ ነው።... በታም በታም... እጅግ በታም ቴሩ ነው" አሉ እኔን ለማበራታት። "እንዲሁ በእውነት አንተ ነህ የትሳፍከው? ወንድሞችህ አልትሳፉልህም፣ አልነገሩህም?" አሉ።

"ወንድሞቼ ሁለቱ አዲሳባ ናቸው፣ አንዱ አቦከር ነው የሚኖረው፣ እኔው ራሴ ዛሬ ጧት ነው ታሪኳን ከእንቅልፌ ስነሣ ያገኘኋት" አልኳቸው።

"በታም በታም ቴሩ። አሁኑኑ በእስቴንስሉ ላይ ትሳፊው። ትሩ አርገህ ትሳፈው። የግጥም ስህፈት ከተራ ንባብ ጽህፈት በታም ማማር አለበት እንዲሁ" አሉ። እኔም የራሴን ግጥም አሳምሬ መፃፍ አላስቸገረኝም።

መጽሐፉ በጀስቴትነር ወዲያው ተባዛ። ለጀማሪ ተማሪዎች ታደለ። የከፍተኛ ክፍል ልጆችም ብርቅ ሆኖባቸው እየተሻሙ አነበቡት። ግጥሜን ሁሉም ወደደው። ዝናዬ በተማሪ ቤቱ ተነዛ። እኔም ስውር የሆነ የካህን፣ የደብተራ ኩራት በትህትና ተሰማኝ። ወዲያው ግን አባቴ ለፈረንጅ ትምህርት የፈቀዱልኝ የስድስት ወር ጊዜ ማለቂያው ስለተቃረበ ከተማሪ ቤት መውጣቴ መሆኑን ለሙሴ አንቶን ሄጄ ነገርኳቸው። እሳቸውም በጣም ነው በዚህ የተገረሙት።

"እንዲሁ ለኤሌሜንታሪ ስኩል፣ እንዲሁ ስድስት ወር ይበቃል ይላሉ አለቃ?" አሉ። እኔ አልመለስኩም፣ ሐዘን አሰንፎ ለጎመኝ። "እንዲሁ እኔ ራሴ ሄጄ አነጋግራቸዋለሁ። ነገ ከምሳ በኋላ እሄዳለሁ" አሉኝ እጅ ነስቼ ወጣሁ። ተስፋ በጭላንጭል ብልጭ ብላ ስለታየችኝ ሃዘኑ ወዲያው ቀለለኝ።

ሙሴ አንቶን እውነታቸውን ነው። በስደተኞች ተማሪ ቤት አራት ፎርም የሚባል ክፍል አለ። ከአራቱ ሌላ ትምህርት ሳይማር ለገባ ተማሪ አራት ዓመት ነው የሚፈጀው። እኔ ግን በስድስት ወር ለመጨረስ ብዬ በመጀመሪያ ተርም ከሁለተኛ ክፍል ነው የጀመርኩት። በተርሙ መሀከል በተደረገው 'ቴስት' ጥሩ ስለሠራሁ እኔና ዮሐንስ መንክር ወደ ሶስተኛ ክፍል ተዛወርን። እዚያም ደህና ቀንቶን በ'ቴስቱ' ፈተና እኔ አንደኛ፣ እሱ ሁለተኛ መሆን ጀምረን ነበር። በዚያ አያያዝ

በዓመቱ መጨረሻ በሚሰጠው ፈተና ወደ አራተኛ ክፍል መዛወራችን ግልጽ ነበር። አራተኛ ክፍል አንድ ዓመት አድርገን ወዲያ መጨረስ ነበር የቀረን። አባቴ በስድስት ወር ይበቃል ሲሉ ሶስተኛ ክፍልን እንኳን ሳትጨርስ ውጣ ማለታቸው ሆነ።

ሙሴ አንቶን ወደኛ ቤት ሲመጡ በራሳቸው ጋሪ፣ በራሳቸው ፈረስ፣ ራሳቸው እየነዱ ነበር። እንዲህ ያለ ነገር በሰፈራችን ታይቶ ስለማይታወቅ መጠነኛ ሽብር ሆኖ ነበር። ከሁሉም የተሸበረው የኛ ግቢ ነው። እኔ ግን መምጣቸውን እጠባበቅ ነበርና ሙሴን እጅ ነስቼ ቀደም ብዬ በመግባት መምጣታቸውን ለአባቴ ነገርኩ። አባቴ የብራና መጽሐፍ ይመለከቱ ነበር። ሙሴ አንቶን ካሁን በፊት እቤታችን መጥተው ባያውቁም፣ አባቴንም እናቴንም ደህና አድርገው ያውቃሉ። ለእናቴ በተለይ ባለውለታዋ ነበሩ። ይኸውም የትርፌ እናት አይክሬ የተሰቀለ ቋንጣ እሰርቃለሁ ብላ ስትቀብጥ፣ ከክፍት በርሜል አፍ ላይ ቆማ ስትንጠራራ እንሸራቷት እበርሜሉ አፍ ላይ በመቀመጫዋ ስለወደቀች አጉል ቦታ ላይ ተጎድታ ነበርና እነሙሴ አንቶን ሐኪም ቤት ለብዙ ቀን ተኝታ ነው አክመው ያዳኑላት። ስለዚህ ሁልጊዜ በደህና ነበር የምታነሣቸው። እሷ ምግባራቸውን ነበር እንጂ ያየችው ሃይማኖታቸውን አልነበረም። አባቴ ግን የሙሴ አንቶንን ሥራና ምግባር ቢወዱም "ማርያም አታማልድም" ይላሉ ብለው በዚህ ቂም ይዘውባቸዋል። ሆኖም እቤት በመጡ ጊዜ በታላቅ ክበሬታ ነው የተቀበሏቸው። እናቴ ቡና እንዲፈላ ትዕዛዝ ብትሰጥም ሙሴ ግን "እዝጌር ይስጥልኝ፣ በአሁኑ ሰዓት እኔ ቡና አልተታም፣ ቷት ብቻ ነው የምተታው" አሉ።

"ያለወትሮ ሙሴን ዛሬ ምን አመጣዎ?" አሉ አባቴ በርጋታ።

"የርስዎ ልጅ፣ የትንሹ ነገር ነው..." ሲሉ ጉዳዩ የኔ ስለሆነ ሹልክ ብዬ ወጣሁና ውጤቱን እውጭ ሁኜ እጠባበቅ ጀመር።

ጥቂት ቆይተው ሙሴ ወጡ። እናቴ "ተከተል" አለችኝ። አጅቤ እሠረገላቸው /ጋሪ/ ድረስ አደረስኳቸው። ሙሴ እኔን አላነጋገሩኝም፣ ፈረሳቸውን "ጁ!" አሉት። እያሶመሶመ ይዟቸው ሄደ። እቤት ስመለስ አባቴ ወዲያውኑ አስጠሩኝና እሳቸው ዘንድ ገባሁ። በእጃቸው ያቺን በጀስቴትነር የተባዛችውን የፊደል መማሪያ መጽሐፍ እያገላበጡ ሥዕሎቹን ያስተውላሉ። "ሙሴ ይህን ሥዕሉን የሳልክላቸውና የእጅ ጽህፈቱን የፃፍክላቸው አንተ መሆንክን ነገሩኝ። እውን ግጥሙን አንተ ነህ የገጠምከው?" አሉኝ።

"አዎን፣ " አልኩ ራሴን ደፍቼ።



"ብያለሁ፣ ተናግሬአለሁ፣ "አሉ። "የሚሰማ የለም፣ ቅኔ ተማሩ ነው እኔ የምለው። ቅኔ ለተማረ ምንም የሚያውከው ነገር የለም። ቅኔ ባትቆጥር ኖሮ የቋንቋውም ትምህርት እንዲህ አይቀልህም ነበር።" አሉና፡ የሚያመናቱ ይመስል ዝም ብለው ጥቂት ቆዩ። እኔም የስድስት ወሩ ነገር ነበረና ያሳሰበኝ። ካሁን አሁን አይሆንም አሉ ብዬ በሥጋት እጠባበቅ ነበር።

"ለፈረንጅ ቋንቋ ትምህርት የሰጠሁህ መንፈቅ ነበረ። እንደኔ በዚሁ በቢቀህና ሐዲስን በጀመርክ። ግን ሙሴ አንቶን ስድስት ወር ያንሳል ብለው ይኸንኑ ሊነግሩኝ እቤቱ ድረስ መጥተዋል። ለሳቸው ስል መንፈቅ አክዬልሀለሁ። እናትህም ደስ ይበላት" አሉኝ። እጅ ነስቼ፣ ደስ ብሎኝ እናቴ ጋ ሄድኩና ቸሩን ወሬ አጫወትኳት።

"የፃፍከውን መጽሐፍ ሙሴ አንቶን ለኔም አንድ ሰጡኝ። ይኸው" ብላ በብሩህ ገጽ መፃፉን አሳየችኝ። "ሥዕሉንም አሳምረህ ነው የሠራህላቸው" አለችኝ፣ ዓይኗ እያበራ። ሲበዛ ብስል ቀይ ነች። ያን ቀን ግን ሌላ፣ ልዩ ፍጡር መስላ ታየችኝ።

እንግዲህ "አስተዋይነት" የኔ የመጀመሪያዋ ያማርኛ ድርሰት መሆኗ ነው። በትእዛዝ የተደረሰች ነበረች። ሁለተኛ መቼም እንደዚያ ያለ ነገር አይለምደኝም። ወዲያ ጽፌ ለሙሴ አንቶን ወርውሬ በመገላገሌ እንደዔ ወጥቶልኛል ብዬ ነበር። ግን ለብዙ ጊዜ ሳይሆን ቀረ። ምክንያቱም በሚቀጥለው ዓመት አራተኛ ፎርም መግባቴ ከተረጋገጠ በኋላ ተማሪ ቤት በመስከረም ሲከፈት፣ ለመስቀል ደመራ በሐረር ያሉት ሁለት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን አሰልፈው በዓሉን ለማድመቅ ሸዋ በር ሜዳ መሄድ ስለጀመሩ ነበር። በዚያን ጊዜ የኛ ትምህርት ቤት ስም ከ "ስደተኞች" ወደ "ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ" ተለውጦ ነበር። ከኛ በኋላ መንግሥት ያቋቋመው ሁለተኛው ትምህርት ቤት በአባታቸው ስም "የራስ መኮንን ትምህርት ቤት" ተብሎ ተሰይሞ ነበር። ቦታችንም የኛ የልጅየው ከግንቡ፣ ከፈረስ መጋላ አካባቢ ወጥቶ ወደ አቦከር አፋፍ ሲል በቀላድ አምባ አካባቢ፣ ጣልያን በስራው ትልቅ ቤት ውስጥ ሆኖ ነበር። የኛ ተወዳዳሪ የሆነው ያባትየው ደግሞ አደሬ ጢቆ ጣልያኖች በሠሩት የነጭ ትምህርት ቤት ሕንፃ ሆኖ ነበር። ታዲያ በዚያን ጊዜ በነኒህ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሀከል ከፍተኛ ውድድርና ፉክክር ተፋፍሞ ነበር። ውድድሩም በኳስ ጨዋታ፣ እንዲሁም በመስቀልና በጥምቀት በዓላት ጊዜ ለሕዝቡ በምናሳየው ሰልፍና በምናሰማው መዝሙር ነበር። መቼም "በፉትቦል" /ኳስ ጨዋታ/ እኛ እናይል ነበር። በመዝሙርና በሰልፍ ግን እነሱ ያይሉ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት የኛ ትምህርት ቤት የሚሲዮን ጠቀስ በመሆኑ የሃይማኖት ስሜትና ቃና ስላለው ለሕዝብ በመስቀል ጊዜ የሚያሰማው መዝሙር "እየሱስ ይወደኛል ወደ ሰማይ ያወጣኛል"... ዓይነት ሲሆን፣

የተቀናቃኞቻችን መዝሙር ግን እንዲህ ያለ አንጉል መንፈሳዊነት ስለማያጠቃው፣ በሕዝቡ ዘንድ በኛም በተማሪዎች ዘንድ ያለው ብልጫ በጉልህ የታየና የታወቀ ነበር። ይህ ሁኔታ ሊፈጠር የቻለው፣ ማለትም ያባትየው የራስ መኮንን ትምህርት ቤት ከልጅየው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት በመዝሙርና በሰልፍ ብልጫ ማሳየቱ፣ ከአስበ ተፈሪ በመጣ አንድ አስተማሪ ምክንያት ነበር። ይህ ሰው የጠባዩንት ዓመል ቢኖረውም እንግሊዝኛን አቀላጥፎ የሚናገርና የሚያስተምር፣ በዚያ ላይ ምን የመሳሰለ ጥሩ ጥሩ መዝሙር ግጥሙን ከነዜማው እየደረሰ፣ ተማሪዎቹን እያስጠና፣ ራሱንም ሆነ ተማሪ ቤቱን ያስመሠግን ነበር። በዚያን ዓመትም ለመስቀል በዓል ያዘጋጀውን አዲስ መዝሙር ቀደም ብሎ ለተማሪዎቹ ማስጠናት መጀመሩ ስለተሰማ እኛ ካመት እስካመት ለመስቀል የምንዘምረውን "መስቀል ቤዛ ነፍሳት" "መስቀል መድሃኒት" እና "የይሁዳ አንበሳ አንተ ንጉሣችን"ን ለሕዝብ ማቅረባችን ማፈሪያ ነገር መስሎ ታየ። ይህን ከሙሴ አንቶን ይበልጥ የተገነዘበው አልነበረም። ስለዚህ አንድ ቀን ሙሴ አንቶን እኛ ክፍል፣ ማለት አራተኛ ፎርም በትምህርት ላይ እንዳለን መጥተው ስለሁኔታው ያላቸውን ስሜትና ሐሣብ ዘረዘሩልን።

"እንዲሁ እናንተ የአራተኛ ፎርም ልጆች፣ የዚህ ተማሪ ቤት የከፍተኛ ክፍል ተማሪዎች ናችሁ። ስለዚህ በዚህ ዓመት እኛም እንደ ራስ መኮንን ትምህርት ቤት ልጆች አዲስ መዝሙር ለመስቀል በዓል ለሕዝብ ማሰማት እንዲሁ አለብን። ስለዚህ እናንተ ተመካከራችሁና ተጋግዛችሁ፣ ተረዳድታችሁ እንዲሁ አንድ አዲስ መዝሙር በአንድ ሣምንት ውስጥ ማድረስ አለባችሁ።" አሉና ያልታሰበ ዱብ ዕዳ ትዕዛዝ ሰጥተውን ወጡ።

ከክፍል በኋላ በነገሩ ብዙ ተከራከርን። እውነትም የራስ መኮንን ተማሪዎች በሰልፍ መዝሙር ጥለውን የትና የት ቀድመው ሄደዋል፣ እኛም ዘንድሮ ችሎታችንን ማሳየት አለብን። ስለዚህ ባጭሩ እያንዳንዱ የአራተኛ ፎርም ተማሪ/ብዙ አልነበርንም/ በአንድ ሣምንት ውስጥ የቻለ ዜማውን ከነግጥሙ፣ ያልቻለ ግጥሙን ወይም ዜማውን ብቻ ደርሶ እንዲያመጣ፣ እስከዚያው ግን በ "ጠላት" ሰፈር ምን ዓይነት ዜማና ግጥም እንደሚያጠኑ ከኛው መሀከል ሰላይ ተልኮ፣ ሳይታወቅ ከተማሪዎቹ ጋር ተደባልቆ ግጥሙንና ዜማውን አጥንቶ መጥቶ እንዲነግረን ተስማማን። ይህን የስለላ ሥራ የሚፈጽሙ ሁለት ልጆች፣ አንዱን ከኛ መሀከል፣ አንዱን ከሶስተኛ ፎርሞች መረጥን።

በበኩላው ሰላዮቻችን መልእክታቸውን ለመፈጸም ወደ ተቀናቃኞቻችን ሰፈር ሄደው ከተማሪዎቹ መሀከል ገብተው መዝሙሩን



አብረው በማጥናት ላይ ሳሉ ባንድ ባልታወቀ ምክንያት የመዝሙሩ ደራሲና አስጠኝ መምህር፣ ባዕድነታቸውንና ሰላይነታቸውን በመጠርጠር ለተማሪዎቹ "ያዟቸው እኒህ ፈርማቶሪዎች ናቸው" ብሎ ድንገት ስለጮኸና ስላዘዘ ሰላዮቻችን በመጠኑ ጡጫና ካልቾ ቀምሰው፣ የድንጋይ ናዳ እየወረደባቸው፣ ነፍሴ አውጭኝ ብለው አምልጠው መጡና የደረሰባቸውን ሁሉ ነገሩን። በ'ጠላት' ሰፈር የሚጠናውን አዲሱን መዝሙር በቃላቸው ይዘውት የነበር ቢሆንም፣ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት በድንጋጤው የቃል ጥናታቸውን "ረስተውታል"ና መልእክተኛነታቸው ለኛ አልጠቀመም። ለነሱም "ዱላ ትርፌ"፣ "ዘጥዘጥ ትርፌ" ሆነ። በሳምንቱ መጨረሻ ከኛ ክላስ ልጆች ሁለት ይሁኑ ሶስት የመዝሙር ዜማና ግጥም ይዘው መጡና አሰሙን። እኔም ከዜማ ቤትና ከቅኔ ቤት የተመረቅሁ ወጣት ደብተራ በዚያ ላይ የግጥም ችሎታዬን በዚያች በግጥሜ ያስመሰከርኩ እንደመሆኔ የራሴን መዝሙር፣ ዜማውንም ግጥሙንም ራሴ ፈልስፌ፣ አቀናብሬ ይዤ ነበር። በዚህ የረዳኝ ከዜማና ከቅኔ ትምህርቴ ጋር በጣልያን "ባሊላ" ትምህርት ቤት ያጠናሁዋቸው የፋሺስት የሰልፍ ማርሽ መዝሙሮች እነ "ከብ ደቤስታ" እነ "ሮማ ቴቬንዱካ ሊምፔሮ" እነ "ጆቪኔዛ! ጆቪኔዛ! ፕሪማቬራ ዱ ቤላሳ "ነበሩ። ሌሎቹ ያቀረቡት የሚሲዮን የጸሎት ዜማ ስለሆነ ዝግ ያለና ጎተት ያለ፣ ግጥሙ የተንዛዛ፣ ለሰልፍ የማይመች ከመሆኑ በላይ ስሜቱ መንፈሳዊ ሲሆን ለሕዝቡ፣ ከኛም ላብዛኛዎቹ ባዕድ መሆኑ ግልጽ ነበር።

ቢሆንም ከኔ ሌላ፣ በተጨማሪ ሶስቱን መዝሙር ድምፃቸው የሆኑ ተማሪዎችን ከአንደኛ እስከ አራተኛ ፎርም እየዞርን መርጠን አስጠንተን ሙሴ አንቶንና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን መምህራን በተሰበሰቡበት በቆይታ መልክ አሰማንና፣ ዳኝነቱን ለነሱ ልንተው ስምምነት አደረግን። ሥራው በዚህ መሠረት ተከናወነ። የሚያስገርመው ሙሴ አንቶን ራሳቸው የሚሲዮኑን ልጆች የተንዛዛ መንፈሳዊ መዝሙር ሳይቀበሉ፣ መንፈሳዊ ያልሆነውን የኔን መዝሙር መምረጣቸው ነው። ኢትዮጵያውያኑ መምህራንማ፣ በተለይ መምሬ ዘውዴና ያማርኛና የግብረገብነት መምህራችን፣ የኔን መምረጣቸው ሳይታለም የተፈታ ሆነ። ስለዚህ የኔ መዝሙር ስለተመረጠ በየፎርሙ እየዞርኩ ለተማሪዎቹ አስጠናሁ። ቀጥሎ ተማሪውን ሁሉ ባንድነት እሜዳ ላይ ሰብስቤ አስጠናሁ። ቀጥሎ የጅምናስቲክ መምህራችን/ አሁን ታርቀናል/ በሰልፍ እያስረገጠ የኔን መዝሙር ራሱ እየዘመረ ደህና አድርጎ አሰለጠናቸው። ወዲያው የመስቀል በዓል ደረሰና ተሰልፈን ቁልቁለቱን፣ አምና የዘመርናቸውን ልዩ ልዩ መዝሙሮች "መስቀል ቤዛ፣ መስቀል መድሃኒት" እና "አይሁድ የካዱት" የተባሉትን በሕብረት እያንጎራጎርን፣ የኢትዮጵያን ባንዲራ የተመረጠ ረዥምም

ተማሪ ከፊት ይዞ፣ ጅምናስቲክ አስተማሪያችን ፊሽካው‹ን ፉር- ፉር እያደረገ አገረ ገዥው‹ና ሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የየአድባራቱ ካህናትና የከተማው ሕዝብ ከተሰበሰበበት ሸዋ-በር ሜዳ ደረስን።

እዚያ ልንደርስ ጥቂት እስኪቀረን ያዜምነው "መስቀል ቤዛ ነፍሳት" የሚለውን ነበር። የራስ መኮንን ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸው ለሸዋበር ሜዳ ስለሚቀርብ ቀድመው ደርሰው በሰልፉ ቦታቸውን ይዘዋል። እንደተለመደው አዳዲስ መዝሙር ዘምረው ተጨብጭቦላቸዋል። እኛ አዲሱን ዜማችንን የዘመርነው ልክ አደባባዩ ስንደርስ ነበርና ተቀናቃኞቻችንንና ባለሥልጣኖቹን፣ ሕዝቡንም እዚያው በዚያው ነው ያስገረምነው። ጭብጨባው ከዳር እስከዳር አስተጋባ፣ ሙሴ አንቶንም ከባለሥልጣኖቹ ጋር ቆመው የደስታው ተካፋይ ሆኑና ስሜታቸው ተቀስቅሶ፣ ፊታቸው ብሩህ ሳምባ መስሎ በየደቂቃው መነጽራቸውን ያስተካክሉ ነበር። ማየት አቅቷቸው ሳይሆን የደስታው ስሜት የሚጨብጡትን አሳጥቷቸው ነው። የኛ ተቀናቃኞች ያሰሙት መዝሙር አዲስም ቢሆን ረዘምዘም ያለ፣ ወደ መንፈሣዊነት የሚቃጣው መዝሙር ስለሆነ፣ የኛ ግን አዲስ ሆኖና ቀልበጭ ብሎ ወደማልያን ማርሽ የሚያደላ፣ ፈጠን ላለ የሰልፍ አረማመድ ምቹ በመሆን አካሄድና አረማመዳችን፣ እንዲሁም ድምፃችን የተመልካችን ልብ እንዳናወጠው ተሰማኝ። የመዝሙራችን ግጥም እንዲህ የሚል ነበረ፣

ሙሉ ሥልጣን አለን
እንድንንቀሣቀስ፣
በሃይለ ሥላሴ በተቀባው ንጉሥ።
ኢትዮጵያ እናታችን ደስ ይበልሽ
ላንቺ ስንል እንሞታለን ልጆችሽ።
ነፃነት አወረዱልን ወደ እግዚአብሔር
የዘረጋሻቸው እጆችሽ
ከእንግዲህስ የውጭ ጠላት እንዳይደፍርሽ
ፈጣሪያችን አጥር ቅጥር ይሁንሽ
ከእንግዲህስ የውጭ ጠላት እንዳይደፍርሽ
ፈጣሪያችን አጥር ቅጥር ይሁንሽ።
አንዲት ስለሆንች ወላጅ እናታችን
የምታሳድገን እያጠባች ጡቷን
እስላም አማራ ትግሬ ጋላ
አንድ ነንና ቀርቷልና መለያየት በወገን
እስላም አማራ ትግሬ ጋላ አንድ ነን
ቀርቷልና መለያየት በወገን



# ከቅኔ ቤት ወደ እስኳላ

፩

የኤሌሜንታሪ ተማሪ ቤት ነገር አለቀ፣ ሥራ ጠፋ። በአደሬ ጢቆ አደባባይ መንቀዋለል ሆነ። አባቴም እኔን ሐዲስ ለማስተማር የቸኮሉትን ያህል አሁን ጉዳዩን ቸል አሉት። እኔም ጉዳዬ ስላልሆነ አላነሣሁባቸውም። በዚህ ላይ እንዳለሁ የቅርብ የተማሪ ቤት ጓደኛዬ መስፍን ፋንታ የሶስተኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ ከአጎቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ ተዛውሮ ነበርና ቀሪውን ያጎቱን ዕቃ ይዞ ለመሔድ ወደ ሐረር ከተማ ሲመለስ ካውቶቡስ ሲወርድ ተገናኘን። መስፍን ያመጣው ወሬ ሁላችንንም በጣም ነበር እንደ ተአምራት ያስገረመን። እኛ የፈረንጅ ትምህርት ጨርሰናል ብለን የምንሠራው አጥተን በአደባባይ እንንገዋለላለን እሱ የፈረጅ ትምህርት ገና አላለቀም አለ። "ደሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተባለ ነገር በአዲስ አበባ ኮተቤ በሚባል ቦታ በቅርቡ ተከፍቶአል፣ ግን ተማሪዎቹ የመኳንንት ልጆች ብቻ ስለሆኑ፣ እዚያ ለመግባት ወገን ያስፈልጋል። እንዳውም አንተማ ወገን አታጣም፣ ታላቆችሁ አቶ መዓዛ እንደምንም ብለው ያስገቡሃል፣ እኔን አጎቴ ሊያስገባኝ ነው። እዚህ ምን ታረጋለህ? አብረን አዲሳባ እንሂድ" አለኝ።

አባቴን ፈራሁ። መስፍን ያለኝን ለእናቴ ነገርኳት። እናቴ "ምናለበት አዲስ አባም ቤትህ ነው፣ መዓዛ አለ፣ ቤቱ መሬቱ- ቀላዱ የኔም ነው። ከዚህ ቀደም እንደፃፍኩላቸው ላባትህ ደብዳቤ ፃፍና ስጠኝ እኔ እሰጣቸዋለሁ" አለችኝ።

"አሁንስ እሺ የሚሉ አይመስለኝም" አልኳት። "በስንት መከራ አንደዬ የፈረንጅ ትምህርት እንድማር ፈቀዱ። ያሁኑን እሺ የሚሉ አይመስለኝም፣ ቁጣ ነው ትርፉ" አልኳት። መስፍን እንቢ ካሉህ ከናትህ መሣፈሪያ ገንዘብ ተቀበልና ጠፍተህ አብረን እንሄዳለን ብሎኝ ነበርና ይኸንን አነሣሁባት።

"ጠፍተህ ብትሄድ ታስቀይማቸውና ይረግሙሃል። ነርምሶ ነው፣ ጠግቦ ነው ይሉሃል" አለችና ጥቂት ካሰላሰለች በኋላ" ምሥጢር አታወጣ እንደሁ ልንገርህ" አለች። ማልኩላት፣ ተገዘትኩላት።

"አባትህ አሁን በዚህ ዓመት ሐዲሱን ሊያስጀምሩህ ተነሥተው ነበር። እስካሁን የቆዩት ችግሮአቸው ነው። ወደው አይምሰልህ፣ ካዲሳባ ከንጉሡ ደብዳቤ መጥቶላቸዋል። አንድ ትልቅ ሥራ እንዲሠሩ ታዘዋል። እሳቸውም ጥቂት ቆይተው እዚያው መምጣታቸው ነው፣ እኔም እመጣለሁ። አንተ አሁን ልሂድና ልማር ብትላቸው ለዚህ ነው እምቢ እማይሉህ"፣ አለችኝ። ፍንጥዝጥዜ ወጣ። "ብቻ ወሬውን እንዳልሰማህ፣ እንደማታውቅ ሆነህ ነው ልመናህን ማቅረብ፣ ኋላ አበበች ነገረችኝ ብትል ታስገድለኛለህ። ልብ አርግ!" አለች።

ወዲያውኑ ያንደኛ ደረጃውን ትምህርት ባንደኛነት ስለጨረስኩትና ሥራ ስለፈታሁ፣ አዲሳባ እጋሼ መዓዛ ዘንድ ሂጄ አዲሱን ትምህርት እንድማር ይፈቅዱልኝ ዘንድ የሚል ደብዳቤ ጽፌ ሰጠኋት። ከምሳ በኋላ ተጠራሁ።

"ደሞ ሁለተኛ ደረጃ የሚባል ተማሪ ቤት አለ ነው የምትለው?" አሉ።

"አዎን፣ መስፍን ፈንታ አሁን ካዲሳባ መጣ። አብረን ልንሄድ ነበር ያሰብነው፣ እሱ ሲገባ እኔም አብሬ ለመግባት።" አልኳቸው። መስፍን ፈንታ የወዳጃቸውና የታላቃቸው የአቶ ወንዱ የልጅ ልጅ በመሆኑ አባቴ ይወዱት ነበርና ለዚህ ነው ያነሣሁት።
"መቼ ነው መስፍን ፈንታ የሚነሣው?" አሉ።

ከሶስት ቀን በኋላ መሆኑንና መቸኮሉን፣ እኔን የማይጠብቅ መሆኑንም ነገርኳቸው። "እኔም ሰነባብቼ ሸዋ መውጣት አልቀረልኝም፣ ንጉሡ ለሥራ አስጠርተውኛል። ሥራው ታላቅ ሥራ ነው፣ ከባድ ሥራ። ያንተ ሐዲስ ለጊዜው መቆየቱ ነው። ሥራው ሲያልቅ ሐዲሱን አስጀምርሃለሁ፣ አንተም በዚያ ጊዜ በሰል ትላለህ፣ ምራቅ ትውጣለህ" አሉ። ለደስታዬ በልቤ ወሰን አልተገኘለትም፣ ግን በፊቴ ላይ እንዳይታይ ተጠንቅቄአለሁ።

"ወይዘሮ አበበች፣ ከዚህ ድሬዳዋ ባውቶቡስ፣ ከድሬዳዋ አዲሳባ በባቡር ለሚሳፈርበት ከነስንቁ ሰላሣ ብር ስጪው። ርግጥ ሠላሣው ይበዛል ግን ሩቅ አገር ለሚሄድ ሰው አይሰስትም" አሉ። ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው። እጅ ነሣሁ።

አዲስ አበባ መጥቼ ከስንትና ስንት ፈተና በኋላ ኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪቤት የመግቢያ ፈተና ተፈትኜ፣ ከሁለት መቶ ልጅና



ወጣት መሀከል አንደኛ ወጥቼ እተማሪ ቤቱ ገባሁ። መስፍን ስላላለፈ ተለያየን። እሱ መምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤት ገባ።

ኮተቤ እንደገባሁ እነ ዮሐንስ ጽጌ ተሽቀዳድመው መጥተው ቅዳሜ ማታ እጸሎት ቤት እንድመጣ እንደማባበል ብለው ጠየቁኝ። እንዳሉት በዕለቱ ብሔድ በጸሎት ቤቱ አንድ ፒያኖ አለ፣ ከበላዩ አንድ ምን የመሰለ ሥዕለ ማርያም፣ ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ተሰቅሏል። ስብከቱ ግን የጠረማርያሞች፣ መዝሙሩም በእንግሊዝኛ ነው አብዛኛው አልፎ አልፎ "ኢየሱስ ይወደኛል፣ ወደ ሰማይ ያወጣኛል" የሚለው የአማርኛ ትርጉም ይዘመራል። ሰባኪያኑ እዚያው አስተማሪ የሆኑ ባልና ሚስት እንዲሁም ሁለት ሌጣ የካናዳ አሜሪካኖች ናቸው። እንግሊዞችም አሉ። አስተማሪዎችና ዳይሬክተሩም እንግሊዛውያን ናቸው። እነሱ ግን ዓለማውያን ስለሆኑ ሃይማኖት አይሰብኩም፣ ጸሎት ቤትም አይመጡም። ይህን ተረድቼ በሁለተኛው ቅዳሜ ከጸሎት ቤቱ ቀረሁ። ቢያዩኝ ቢያዩኝ አልመጣም። "እሺ እመጣለሁ" ነው፣ ግን አላረጋትም። በዚህ ፀረ ማርያሞች ቂም ያዙብኝ። ጥቂት ቆይቼ አንድ በቅዱስ ሚካኤል ስም በድብቅ የተቋቋመ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተቆርቋሪ ተማሪዎች ማኅበር ኖሮ፣ እነሱ እሁድ እሁድ ማታ በዶርሚቶሪ( መኝታ ቤት) በሚያደርጉት ጸሎት እንድሳተፍ በምሥጢር ጠየቁኝ። ሄድኩ። ማኅበርተኞቹ ከሰባት ከስምንት አይበልጡም፣ ሁሉም ተማሪዎች ናቸው። መሪያቸው ገድሌ ይባላል። ቀይ አጭር፣ ደልዳላ፣ ወዛም፣ ፊቱ ለምላማ መንዜ ነው። ማተቡም እንደሰው ወፍራም የሆነ፣ ግን እሱም እነሱም ድቁና ወይ ድብትርና ያልቀመሱ የወታደር ልጆች ነበሩ። ግን በአባቶቻቸው ሃይማኖት የሚቀኑና የሚቆረቆሩ፣ በተራ አስተማሪነት መልክ ተማሪ ቤቱን የያዙት ሚሲዮናውያን ተማሪውን "እፈረንጅ አገር ለትምህርት እንልካችኋለን፣ እዚህም እንረዳችኋለን" እያሉ እንዴት እንደማረኩት፣ እንዴት እንዳስካዱት እያዩ በንዴት የሚጨሱ ነበሩ።

ከሁሉም የሚያናድዳቸው የጸሎት ቤት ተብሎ ምን የመሰለ ሥዕለ ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ በተሰቀለበት ክፍል ውስጥ የጠረማርያሞች ስብከት መነገሩ ነበር። ይኸን ሁሉ ገድሌ ዝግ ብሎ ቃሉን እየቆጠረ በርጋታ በስብሰባው ላይ ከተናገረ በኋላ ሌሎችም ጨማመሩበት። "እንደኛ ያለነው ለሃይማኖታችን ተቆርቋሪዎች ዝም ብለን ካየን፣ ሁሉም መክዳቱ ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ በዋናው ሰባኪ በዶክተር ቶምሶን በመኪና እየተጫኑ፣ ከተማ እየሄዱ በቡሩስታንት ቤተስኪያን 'መቁረብ' ጀመረዋል" አሉ። ስብሰባው የተጀመረው መቼም "በስመ አብ" "ጸሎተ ሃይማኖት" ን ከፍ ባለ ድምፅ በገድሌ መሪነት፣ ባንድነት በመውጣት ነበር። ከዚያ በኋላ ከላይ

የጠቀስኩትን ሀሣብ ያዘለ የጋለ ስብከት ከተሰማ በኋላ ከወንጌል አንዱን ክፍል በአማርኛ ገድሌ ያነብና ለመደምደሚያ" አቡነዘበሰማያት"፣ "በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል"፣ "ኦ እግዚእትነ ማርያም ሰላም ለኪ፣ ድንግል በሕሊናኪ፣ ወድንግል በሥጋኪ..." በሚለው በታላቅ ስሜት ስብሰባው ይደመደማል።

ይህ ማኅበር ግን እንደ ብሩስታንቶቹ ፒያኖና አዲስ ፈረንጃዊ ዜማ ስለሌለው በዚህ ረገድ ከነዚያ ጋር ውድድሩን አልቻለውም ነበር። ቢሆንም ይህን ለማሟላት እሁድ እሁድ ጧት በሌሊት፣ እነገድሌና ጓደኞቻቸው እየካ ሚካኤል እየሄዱ የቅዳሴ ዜማ ይሰሙ ነበር። የመጀመሪያው ዕለት በስብሰባው ተገኝቼ እንግዳ እንደመሆኔ መጠን በካህን ደንብ፣ በትህትና ራሴን ደፍቼ ስብከቱን- ዲስኩሩን ልበለው እንጂ- ሰምቼ ጸሎቱን አብሬ ከነሱ ጋር ወጣሁ። ፈረንጅ አገር ለትምህርት ለመሄድ ብሎ፣ ወይም በአድልዎ ከክፍል ክፍል፣ ቶሎ ለመሸጋገር ብሎ የአባቶቹን፣ የቅድማያቶቹን፣ የላሊበላን፣ የተክላይማኖትን፣ ያቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን፣ የቴዎድሮስን፣ የምኒልክን እየጣለ የብሩስታንት ጸሎት የሚዘፍነው ተማሪ ብዛት ግን እኔንም በጣም ነበር ያስቆጨኝ።

አንድ ቀን እኔ ራሴ ሄጄ የፈረንጆቹን ጸሎት ሰምቼ ከዚያ በኋላ እርም ብዬ ነው የተውኩት። "ተው በትምህርት ያደሉብሃል፣ ይጎዱሃል፣ መምሰል ይሻላል" ብለው ልጆች ቢመክሩኝም፣ "እንደዚያ ቢያደርጉ ከሰማእትነት ነው የምቆጥረው" ብዬ በልቤ በእምቢታዬ ጸንቻለሁ። እነ ዶክተር ቶምሰን ድንገት በኮሪዶር አግኝተውኝ "ምነው ቀረህ? ለምን አትመጣም?" ሲሉኝ፣ "እሺ እመጣለሁ፣ አልቀረሁም" እላለሁ እንጂ ፊት ለፊት "እምቢ" አልልም። ግን ደግሞ ያቺን ነገር ብሞት አላረጋትም። ብቻ ይህ ይበቃል ወይ? ራስን መጠበቅ ለራስ መጠንቀቅ በቂ ነወይ? ሌሎቹን፣ የሄዱትን እንዲመለሱ ፣ በመሄድ ላይ ያሉትን እንዲቆሙ፣ ለመሄድ እያሰቡ የሚያመነቱትን ባለመሄዱ እንዲረጉ ማድረግስ አያስፈልግም ወይ? እንዲህ እንዲህ ያለው ሃሣብ በልቤ ይጉላላ ጀመር። በዚህ ላይ ሳለሁ ሁለተኛው እሁድ ደረሰና እንደተለመደው ማኅበሩ ተሰበሰበ። ጸሎቱ ተደገመ፣ ስብከቱንም ገድሌ ባጭሩ ደግሞ ሲያበቃ" አንተም ዕንግዳው አንድ ነገር መናገር አለብህ እንጂ፣ እኔ'ኮ የወታደር፣ የነፍጠኛ ልጅ ነኝ፣ አንተ ግን ቅኔ የተቀኘህ የካህን ልጅ መሆንህን የሐረር ዶርሚቶሪ ልጆች ነግረውኛል" አለ፣ ሌሎቹም ሃሣቡን በመደገፍ አጨበጨቡ። እኔም ተነሥቼ በልቤ ይቁላላ የነበረውን የሃይማኖት ተቆርቋሪነት ሃሣብ በጋለ ስሜት፣ በስንክሣር ንባብ፣ በሰላ አንደበት አኾጎደጎድኩላቸው። ቀጥዬም ስሜቱ



ያለመጠን ስለተቀሰቀሰ ሰሞኑን የገጠምኳትን ያማርኛ ጉባዔ ቃና "ለመደምደሚያ ላሰማችሁ" አልኳቸው። አጨበጨቡ። ግጥሟ ይቺ ብቻ ነበረች።

በስኳር በብስኩት እየተደለለ
ኧረ ሄደ ሄደ ሄደ ኮበለለ።

ጭብጨባው እንደገና አገረሸና ብዙ ቆየ። እኔም እጅ ነሥቼ ወደ መቀመጫዬ ስመለስ ጭብጨባው እንደገና አገረሸና" ቢስ! ቢስ! ቢስ! ጣመን ድገመን" የሚለው በዛ። ያች ግጥም ለገድሌ ባጭሩ ስለነገረችው ወፍራም ጉንጩ በፈገግታ ፍርጥምጥም ብሎ "እባክህ እንዲህ ሲለምኑህ አንዲት ደሞ ድገመን" አለኝ።

ምን ላድርግ? ሌላ ግጥም የለኝ። እነሱ እያጨበጨቡ ወጥረው ያዙኝ። ይኸንኑ ነገርኳቸው ግን "አንሰማም" አሉ። "አለህ አታጣም... እባክህ፣ አንድ ድገመን" ብለው ድርቅ አሉብኝ። ቢቸግረኝ ጊዜ "እሺ እምቢ ካላችሁ አንዲት ግጥም ደሞ አሰማችኋለሁ፣ ግን ይቺኛዋ የሃይማኖት ግጥም አይደለችም" አልኩ፣

"ባይሆንም ግዴለም፣ ደስ ይበላቸው" አለኝ ገድሌ። አይ እሱ ከፈቀደ ምንም አይደለ ብዬ ያቺን ሐረር በሙሴ አንቶን ጉትጓችነት የፃፍኳትን "ያንድ ጌታ አስተዋይነት"ን በቃሌ ወጣሁላቸው። ጭብጨባው አስተጋባ፣ እኔም እጅ ነሥቼ በትህትና ወደ ወንበሬ ተመለስኩ። ቀጥሎ ገድሌ የመደምደሚያ ንግግር አደረገ። እሱ የነፍጠኛ ልጅ መሆኑን፣ አባቱም አርበኛ ቢሆኑም ካህን አለመሆናቸውን፣ እሱም የማኅበሩ ስብሰባ አለቃ ሆኖ ሲመረጥ ምርጫውን የተቀበለው "ሰው ሲታጣ" እንደተባለው ዓይነት መሆኑን ጠቅሶ አሁን ግን በመሀከላችን ቅኔ የተቀኘ ደብተራ ስለተገኘ ማኅበርተኞቹ ፍቀዱልኝና ሰብሳቢ አለቃነቱን ለሱ ላስረክብ ብሎ ዱብዳውን ጣለብኝ። ማኅበርተኞቹ መስማማታቸውን በጭብጨባ ገለጹ፣ እኔም እየጨነቀኝ፣ እምቢ እንዳልል ከፍራት እንዳይቆጠርብኝ በመሥጋት፣ ተነሥቼ እስብሳቢው ወምበር ላይ ተቀመጥኩኝ።

ወሬው ተማሪ ቤቱን ወዲያውኑ አዳረሰው። ግጥሚም ከብዙዎቹ ጆሮ ደረሰች። እኔም እንደ አብዛኛዎቹ ባዶ እግሬን የምሄድ በመሆኔ በአለባበሴም ብልጭልጭነት የሌለብኝ ስለሆንኩ ብዙዎቹ ተማሪዎች መንፈሳዊነቴን፣ ሃይማኖታዊነቴን ለማመን አልተቸገሩም። ጫማ አላረግም ብዬ ባዶ እግሬን የምሄደው ግን የሚገዛልኝ ዘመድ አጥቼ አለመሆኑን ብዙዎቹ አያውቁም ነበር። ከታላላቅ ወንድሞቼ አንዱ በጽህፈት ሚኒስቴር፣ አንዱ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ሥራ

ይዘው በዘመኑ ጠብደል አንኳን ባይሆን ወፈር ያለ ደመወዝ ይበሉ ነበር። ኩፍ ጫማ እንግዛልህ፣ የእጅ ሰዓት እንሸልምህ ብለው ነበር። "በነራስ እምሩ፣ በነቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፣ በነራስ ደስታ፣ በነራስ ካሣ፣ በነደጃች ገብረሥላሴ፣ በነደጃች ዓባይ፣ በነአዛዥ ሥነ ጊዮርጊስ በኋላም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጆች መሀከል ካኪ ለብሰህ ባዶ እግርህን እየዞርክ ዘር አታሰድብ" ብሎኝ ነበር ጋሼ ገብረክርስቶስ፣ እንደቀልድ አድርጎ። እኔ ግን ኩፍ ጫማም፣ ሰዓትም፣ ጠጉርን መከርከምም፣ ሱፍ ኮት መደረብም ከመንፈሳዊነት የሚያርቅ አጉል ዓለማዊነት ነው በማለት ሁሉንም "እምቢ አልፈልግም" ብያለሁ። ታላቄ መርሱ በማዘጋጃ ቤት የመለስተኛ መሀንዲስነት ትምህርት በፈረንሣይኛ ይማር ነበር፣ እሱ ግን ጫማውንም ሰዓቱንም በደስታ ተቀብሎ በኔ ጠባይ ይገረምና ይቀልድም ነበር። እኔ ግን ፍንክች!

ከዚያ ቀን በኋላ "የቅዱስ ሚካኤል ማኅበር" ዋና ሰባኪ እኔ ብቻ ሆንኩ፣ ስብከቴም እንዲሁ የቁጭትና የቁጣ፣ የብስጭት መግለጫ ሳይሆን ደንበኛ ትምህርት ያለው፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ ጠቅሶ፣ ከከሀዲያኑ ጋር ሽንጡን ገትሮ ሳይፈሩ ለመከራከር የሚያስችል እንዲሆን የታቀደ ነበር። ለዚህ የረዳችኝ አንድ እየሩሳሌም የነበሩ የኛው መነኩሴ የፃፉት መጽሐፍ ነበረች። መጽሐፉን አባቴ ወደዋትገና ሐረር ሳለሁ እንዳነባት አውሰውኝ ነበር። እኔንም በጣም ስለጣመችኝ በእጅ ጽህፈት ገልብጫት ነበር። በተለይ ላጠረማርያሞች መልስ የምትሰጠው ክፍል አሁን ሳልወድ በግዴታ፣ ሳላስበው የሃይማኖት ሰባኪ ስሆን ጊዜ በጣም ጠቀመችኝ።

ለማኅበርተኞቻችንም ሆነ በተመልካችነት ወደስብሰባችን ለሚመጡት ተማሪዎች ግን ስብከቱ ብቻ አላጠገባቸውም። ጣመኝ ድገመኝ ሆነና ከስብከቱ በኋላ ከመበተናችን በፊት ግጥም እንዳነብላቸው እየለመኑ አስቸገሩኝ። በሁለተኛው እሁድ፣ ቢያስቸግሩኝ ጊዜ ያቺኑ "ያንድ ጌታ አስተዋይነት" ደግሜ አነበብኩላቸው። በድጋሜ የሰሟትም፣ ለመጀመሪያ የሰሟትም ደስ ብሏቸው አጨበጨቡና በዚያ የተለያየን። የሶስተኛው እሁድ ነው ጣጣው። ግጥሙ ከየት ይመጣል? ለግጥም አንድ ዓይነት ታሪክ ማስፈለጉን ተረድቼዋለሁ ታሪኩ ከየት ይምጣ? "ግጥም የለኝም፣ ስብከት ብቻ ነው የማሰማችሁ፣ አታስቸግሩኝ" ብዬ ጨከኜ እንዳልገሥፃቸው አኩርፈው ወደ ጠረማርያሞቹ ስብከት እንዳይከዱብኝ ፈራሁ። ገድሌን ባማከረው "ግጥሙ ለስብከታችን በጣም ጠቅሞናል፣ ወደ ፈረንጆቹ የሄዱት የእየሱስ ይወደኛል ወደ ሰማይ ያወጣኛል" መዝሙር እየሰለቻቸው በሹልክታ ያንተን ግጥም ለማሰማት የመጡ



አይቻለሁ። በዚህ አያያዝ የኮበለሉትን በቅርብ ጊዜ እንመልሳቸዋለንና በስብከቱ ብቻ ባትወሰን በግጥሙም በርታልን። ከስብከቱ በኋላ አንዲት ግጥም ወይም ጨዋታ አጭርም ብትሆን ብታሰማልን በቂ ነው" አለኝ። የቸገረ ነገር አጋጠመኝ። ለኔ ቁም ነገሩ ያለው ከስብከቱ ላይ ነው እንጂ ከግጥሙ አይደለም፣ ግጥሙ አይረባም። ቢሆንም እሁድ እሁድ ማታ ግጥም ካላነበብኩላቸው ቅር የሚላቸው ሆኑብኝ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ለስብከቱ ሳይሆን ለግጥሙ ነበር በሁለተኛው ቀን የመጡት። አልችልም ማለት ሽሽት፣ ፈሪነት ሆነ። በኔ ግጥም አለማሰማት ምክንያት የስብከታችን ሥራ ቢጨናገፍ የሕሊና ወቀሣውን የምችለው አልመሰለኝም። ስለዚህ የግጥም ገጣሚነቱን ሥራ ልጋተረው ታጥቄ ተነሣሁ። ምን ላድርግ?

ታሪኩ ከየት ይመጣል? ለሚለው ጥያቄ መልሱን ወዲያውን አገኘሁለት። ዓላማው የአባቶቻችንን ሃይማኖት ለማጠናከሪያ፣ እመቤታችንን ለማስከበሪያ መሆኑን እሱ ፈጣሪ ስለሚያውቅ እሱው ታሪክ ይገልጥልኛል፣ እመቤታችን ለቅዱስ ኤፍሬም እንደገለጠችለት ትገልጥልኛለች፣ ከኔ የሚፈለገው ቅዳሜና እሁድን ሌሎች ተማሪዎች ኳስ ሲጫወቱ ዋና ሲዋኙ እከተማ ሄደው ሲኒማ ሲያዩ ግጥም ስቆጥር፣ ስገጥም መዋል ነው። በዚህ መንገድ ቅዳሜና እሁድን ባሳልፈው እሁድ ማታ ስለሆነ የማነበው ግጥም አላጣም። አዲስ ካጣሁ ያለፈውን በድጋሚ አሰማለሁ። አንዳንድ ታሪክ አገኝ ጀመር። ግጥሜም ረዘም እያለ ይሄድ ጀመር። አድማጮቼም በርከት እያሉ ይሄዱ ጀመር። ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት በየሳምንቱ አንዳንድ አዲስ ግጥም መግጠሙ አቀበት ሆነብኝ። ስለዚህ በተርም መጨረሻ ተማሪ ቤት ሲዘጋና ወደየቤታችን ስንመለስ የእረፍትን ጊዜ ታሪክ ለመፈለጊያ፣ ከራሴ አእምሮ ለማፍለቂያ ለማዋል ወሰንኩ። በዚህ ዓይነት ግጥም እየፃፍኩ እሁድ እሁድ ማታ ከሃይማኖቱ ስብከት በኋላ ለምእመናኑ አነብ ጀመር። ታሪካቸውን ከራሴ ያፈለቅኋቸው ግጥሞች በዚያን ጊዜ አንዳንዶቹ የእኛን የተማሪዎቹን ነገር በጨዋታና በቀልድም ሆነ በምር የሚያነሣሡ ነበሩ። ለምሳሌ እኔና ሀብቴ እሸቴ በሐረር ዶርሚቶሪ ጎንና ጎን ነበር የምንተኛው፣ ሀብቱ በጣም ወፍራም ነበር እኔ ቀጭን ነበርኩ። ከዚህ ሁኔታ የመነጨችው ግጥም "አልጋ" ነች። የሀብቱ አልጋ የሸክሟን ክብደት እያማረረች ሐዘኗን የምትገልጥበት ነበር። ሌላዋ ግጥም ስለ "መኮቸም" ነበረች። ዘውዴ በሱፈቃድ ነበር ይህን "መኮቸም" የተባለ አዲስ ቃል በተማሪቤት ያስገባው። በሱ ሳቢያ "መኮቸም" የሚል አርዕስት ያላት ግጥም ፃፍኩ። ከምንማረውና ከምናነበውም የመነጨ ግጥም ነበረ። የተማሪቤታችን ላይብራሪ /ቤተመፃህፍት/ በጣም ጥሩ ነበርና፣ አንድ ቀን የአስትሮኖሚን ነገር የሚያስረዳ መጽሐፍ ስላነበብኩ መሬትና ጨረቃን አነጋግሬ "እናትና

ልጅ" የሚል ግጥም ፅፌ ለምእመናን አሰማሁ። መጽሐፉ ጨረቃ ከመሬት ተከፍላ ተጎርዳ ነው የተገኘችው ስለሚል፣ መሬትን እናት፣ ጨረቃን ልጅ አደረግኋቸው። ባዮሎጂ ስንማር የአእዋፍን ነገር ዶክተር ቶምሶን በሚያስተምርበት ጊዜ የያዝኩትን፣ ሐረር ሳለሁ ዶሮ አረባ ነበርና በዶሮዎች ያየሁት ነገር ለጅግሮች ሰጥቼ "ሞኚት ተላሊት" የተባለችውን ግጥም ጽፌ ለምእመናን አነበብኩ። ታሪኩ ለዕለት ጥቅሟ ብላ ከፈረንጅ ወጥመድ የገባችውን ጅግራ ሃሣብ የሚገልጽ ስለነበር በእጅ አዙር በውስጥ ታዋቂ የራሱን ዶክተር ቶምሶንን አዳኝነትና በሱ የጠረማርያም ስብከት ተደልለው ሃይማኖታቸውን የለወጡትን ተማሪዎች ሞኝነት የሚጠቁም ነበር። በኔ አስተሳሰብ አንዱ ግጥም በይሉኝታ ምክንያት ከፈተና የወደቀ ተማሪን አሣዛኝ ሁኔታ የሚተርክ ነበር። ሌሎች ግጥሞች በዚህ ዓይነት ገጥሜ ነበር። ከዚህ ይልቅ ብዙ ለግጥም የሚሆን ታሪክ ያገኘሁት ባላሰብኩትና ከዚያ በፊት ባልጠረጠርኩት መንገድ ነበር። እንግዲህ ተማሪ ቤት ሲዘጋ ዕረፍቱን ወደ ቤት ሄጄ አዲስ አበባ ከእናትና አባቴ ዘንድ ነው የምቀመጠው። በፊት እታላቅ ወንድሜ ጋሼ መዓዛ ቤት ነበር፣ በኋላ ግን አባቴ ከንጉሡ ለታዘዘበት ለሃይማኖተ አበው ትርጓሜ ሥራ አዲስ አበባ ስለመጡ እናቴም አብራቸው መጥታ አራት ኪሎ ሰፌ ሠፈር ካለው ግቢያችን ገብተዋል። ጋሼ ገብረክርስቶስም መርሱም እዚያው የየራሳቸውን ቤት ይዘዋል።



ለ

አባቴ ከምሳ ወይ ከራት በኋላ በዚያ በጐሽ ዋንጫቸው ወፍራም የገብስ ጠላቸውን እየተጎነጩ የቅርብ እንግዳ ወይም እንደኔ ሰሚ ሲያገኙ ጨዋታ መጫወት፣ ታሪክ መተረክ የቆየ፣ ከጥንት ጀምሮ ያለ ልማዳቸው ነው። በዚህ መንገድ ብዙ የሚያስቁ፣ የሚያሳዝኑና የሚያስተምሩ ተረቶችና ታሪኮች ይተርታሉ፣ ይተርካሉ። ግን ከዚህ ጊዜ በፊት እንዲያው መስማት፣ በከበሬታ መሳቅም ሆነ መገረም ወይም መደመም እንጂ፣ በየጊዜው የሚተርቱትን ወይም የሚተርኩትን ልፃፈውና ላሰባስበው ያለ ሰው ከኔም ከወንድሞቼም በኩል አልነበረም። አሁን ግን ሰባኪ ከሆንኩ በኋላ፣ በየሳምንቱ አንድ ግጥም ለምእመናን የማቅረብ ግዴታ ውስጥ ከገባሁ በኋላ፣ ከሳቸው የምሰማቸውን ጨዋታዎችና ተረቶች፣ እሳቸው ሳያውቁብኝ ወዲያው እንደሰማኋቸው ሳይረሱኝ ወጣ ብዬ በወረቀት ላይ ማስፈር ጀመርኩ። ለዚሁ ብየ ከምሳና ከራት በኋላ ሌሎች እጅ ነስተው ወደሚሄዱበት ሲሄዱ እኔ ወደኋላ እየቆየሁ ለሰበቡ አንድ የሃይማኖት ወይም የታሪክ ጥያቄ እጠይቃቸው ጀመር። ግን ዋናው ምክንያት ለግጥሜ የሚሆን አዲስ ተረት ለመቅሰም ነበር። እሳቸውም ወደ ኋላ ቀርቼ መንፈሳዊ ጥያቄ በመጠየቄ ደስ እያላቸው አንዳንድዬ አንድ ብርጭቆ ጠላ እንዲሰጠኝ ያዙልኝና በጥያቄው ሳቢያ ብዙ ብዙ ምሳሌና ታሪክ ከደረደሩ በኋላ አልፎ አልፎም አንድ ተረት ጣል ያደርጉ ነበር። እኔ ቶሎ ያቺን ለቀም አርጌ በወረቀት ማስፈር ነው።

በዚህ መንገድ ተረቶች ሰበሰብኩ። የሰበሰብኩትንም ፍሬ ነገሩን ይገፎ እሳቸው በስድ ንባብ ያወጉትን ወደ ግጥም እየመለስኩ እጽፍና እሁድ እሁድ ማታ ለምእመናን ማሰማት ሆነ። ከዚያ በኋላ ስብከቱ ሰመረ፣ ተሰባኪው በረከተ፣ ለሃይማኖቱ ስብከት ቁብ የሌላቸው እንደ በላይ ዓባይ ያሉት እንኳ ሌንሶላቸውን እየተከናነቡ ይመጡ ጀመር። ይሉኝታ እየያዛቸው ለግጥሙ ብቻ መጡ እንዳይባሉ የግድ ስብከቱንም ይሰሙ ጀመር። የምእመናን ቁጥር ከስምንት ወደ አሥራ ስምንት፣ ሃያ ስምንት፣ አርባ ስምንት በመጨረሻማ ወደ ሰማኒያው ደረሰ። እኔም በስብከቱም፣ በግጥም ጸሐፊነቱም ሰለጠንኩበት። ፊት አስቸጋሪ ዳገት ሆኖ የታየኝ ያማርኛ ግጥም አሁን ሰተት ያለ ሜዳ ሆነልኝ። ያን ጊዜ ታላቁ አፍላ ደራሲ ከበደ ሚካኤል ነው። በኤሌሜንተሪ ተማሪ ቤት ሳለሁ "ታሪክና ምሳሌ"ን አንብቤአለሁ። አሁን ደግሞ "ከይቅርታ በላይ" የተባለ መፅሐፉን አንብቤ የአማርኛ ግጥም ፍቅር አድሮብኛል። በዚያ ላይ በእንግሊዝኛው የሮበርት ሉዊ ስቲቨንሰንን" ሮቢንሶን ክሩሶ"ን፣ "ትሬዥር አይላንድ"ን እንዲሁም የነላምብን "ላምብስ ቴልስ

ፍሮም ሼክስፒየር"ን በፈረሣይኛ ደግሞ "ፓርዱር"ን ወዘተረፈ. አንብቤአለሁ። ይህ ታዲያ የራሴን የገጣሚነት ስሜት ቀሰቀሰው። የግጥምን ድርሰት ለሃይማኖት ስብከት ማጣፈጫ ስኳር ነው ብዬ የሰጠሁት ግምት ቀስ በቀስ እየተወለጠ፣ የግጥም ድርሰት ራሱን የቻለ የተፈጥሮ ስጦታ የሚያስፈልገው ሙያ መሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ቁልጭ ብሎ ታየኝ።

በዚህ ጊዜ ነበር ትምህርት ቤት ለክረምት ሲዘጋ ለዕረፍት ወደ ቤት ሄጄ አንድ ቀን ከፒያሣ ስመለስ መንገድ ላይ ከባድ ዝናብ መትቶኝ በግራ ጎኔ ከደረቴ ላይ ጭምድድ አድርጎ የሚይዝ፣ አልፎ አልፎም እንደ ውጋት መሳይ ጠቅ-ጠቅ የሚያደርግ የብርድ በሽታ የያዘኝ። ይህ በሽታ ወደ ሳምባ በሽታ እንዳይለወጥብኝ ያለ መጠን ሠግቼ ነበርና ቡሉኮ ተከናንቤ እሳት እየሞቅሁ ሶስት ቀን ያህል ባስታምመው ስላልተሻለኝ እናቴ የመመርመሪያ ገንዘብ ሰጥታኝ ራሳውዲ ወደተባለው የጣልያን ፋሽስት ሐኪም ዘንድ ሄድኩ። ሐኪሙም መረመረኝና "ካልቸ" የሚባል መድሃኒት ገዝቼ በመርፌ እንድወጋው አዘዘልኝ። የሐኪሙን ማዘዣ ይዤ ወደ ፋርማሲ ብሔድ በዚያን ጊዜ ገንዘብ የመድሃኒቱ ዋጋ ወደ አርባ አራት ብር ተጠጋ። ይህን ማን ይከፈልልኝ? እናቴን ከፊይ እንዳልላት መመርመሪያዬን ከፍላለች። በዚያ ላይ የአባቴ የአለቅነት ደመወዝ ታላቅ ወንድሞቼ ከሚያገኙት እጅግ ያነሰ ነው። ስለዚህ በራሴው ፍርድ ወፈር ያለ ደመወዝ ያለውን ታላቅ ወንድማችንን መድሃኒቱን እንዲገዛልኝና ከሳምባ በሽታ አደጋ እንዲያድነኝ ተማጠንኩት። እሱም የዋጋውን መብዛት አይቶ የልጅ ነገር በተረፈው ከረሜላ ሊገዛበት ይሆናል ዋጋውን እንዲህ የቆለለው በማለት ይመስለኛል ተያይዘን ወደ ፒያሳ ሄድንና ግምቱን ከሰጡኝ መድሃኒት ቤት ዋጋውን እንደገና ጠየቀ። ያንኑ ነገሩት። ከዚያ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ ሌሎች መድሃኒት ቤቶች ጠየቅን። ዋጋው ያው አርባ አራት ብር መሆኑን ተረዳን። አንድ ነጋዴ ካንዱ የሚለይበት በተጨማሪው ሣንቲም ብቻ ሆኖ ተገኘ። እኛም መድሃኒቱን ሳንገዛ ተመለስን። ወንድሜ መድሃኒቱ በጣም ውድ መሆኑን ለእናቴ ነገራትና በአበሻ መድሃኒት ልማድ እሳት እንዲነድና በብልኮ ተሸፋፍኜ፣ ደረቴን ለስታ ቅቤ ተቀብቼ፣ እሳቱን እየሞቅሁ እንድታሸው አዞ ወደ ቤቱ ሄደ። እናቴም አባቴም የተባለውን አድርግ አሉኝና ማታውን እሳቱ ግር ብሎ ነዶ የወንድሜ ትዕዛዝ ተፈጸመ።

እኔ ግን የአበሻ መድሃኒት "የተባለውን የማላምነው ከመሆኔ ሌላ አደገኛ ነው የሚል እምነት ስለነበረኝ በጡጋው ልብሴን ለባበስኩና ወፍራም ሹራብ ደርቤ ወደ ሌላኛው ወንድሜ ወደ ጋሼ ገብረክርስቶስ



ዘንድ፣ ደጅ ልጠና በጧት ሄድኩ። እሱም የመታመሜን ታሪክ፣ የሚያሠጋኝን የሳንባ በሽታ ነገር ከሰማ በኋላ ደጀጠኚ እንደመሆኔ መጠን ተከትየው እመሥሪያ ቤቱ እንድሄድና እዚያ ከደመወዙ ብድር ቢያገኝ የሚቻለውን እንደሚያደርግ በተለመደው ፌዝና ቀልድ በቀላቀለ አነጋገሩ ገለጸልኝ። ያን ቀን ሌሊቱን ሲዘንብ አድሮ ጧት ብራ ስለነበረ ካፖርቱን ጠቅልሎ ሰጥቶኝ ይዤለት፣ እንደ አሽከር ተከትዬ አብሬው እመሥሪያ ቤቱ አገር ግዛት ሚኒስትር መዝገብ ቤት ገባን። የወንድሜ የሥራ ጓደኞች ገና ብቅ ስል ነው አይተውኝ የማያውቁትን ሰው ወዲያው ያወቁኝ። ይህ በጣም አስገረመኝ።

የመዝገብ ቤቱ ቢሮ አንድ አገር ሜዳ ነበር። ሠራተኞች በየጠረጴዛቸው ሆነው መዛግብታቸውን ፋይላቸውን ያገላብጣሉ፣ ተላላኪዎች ከዚህ እዚያ ሽር ጉድ እያሉ ያጋፍራሉ፣ ያስተናብራሉ። ወንድሜ ሲገባ ሳቅና ፈገግታ ሆነ። ዓይን ሁሉ እኔ ላይ አረፈ።

"ያቺን የምታጫውተንን ታናሽ ወንድምህን ይዘህ መጣህ እንዴ" አለ አንዱ አድናቂው።

"አዎ ዛሬ ላስተዋውቃችሁ ብዬ ነው። መንግሥቱ ለማ ይሏችኋል ይቺ ነች። እንዲህ አትምሰላችሁ የምትጸፈው ያማርኛ ግጥም። በትምህርት ማንም አይችላትም" አለ። እኔ ዓይናፋርነት ከዱሮውም አለብኝና በድንገት የዚያ ሁሉ ሰው ዓይን ሲያርፍብኝ ጊዜ በሐፍረት አንገቴን ደፍቼ፣ ወንድሜ ካሁን አሁን ገንዘቡን ከጠረጴዛው ኪስ አውጥቶ ሰጥቶኝ ከዚህ ሁሉ እገላገላለሁ በሚያሰኝ ትዕግሥት ካፖርቱን እንደያዝኩ ከበሩ ገባ ብዬ ቆሜያለሁ።

"ማሞ" አለኝ አንዱ የማላውቀው የማልጠይቀው ከራኔ። "እስቲ ያቺን ወንድምህ የሚነግረንን ግጥምህን፣ ያቺን ባላባት ማለት 'ባል-አባት' ማለት መሆኑን የምትገልጠውን ግጥምህን እስቲ አሰማን" አለ።

"ማነህ ተላላኪ! ለዚህ ወጣት ቶሎ ከሻይ ቤት ግሩም ሻይ ትኩሱን አምጣለት። በፊት ወምበር አቅርብለትና ይቀመጥ... ደሞ ስትሔድ እግረ መንገድህን እገንዘብ ቤትና እፔርሶኔል ጎራ በልና እነ እከሌን ቶሎ ኑ በላቸው። የገብረክርስቶስ ታናሽ ወንድም፣ ያቺ ግጥም የምትጽፈው አዲሷ ከበደ ሚካኤል መጥታለች በላቸው፣ እንዳያመልጣችሁ በላቸው። ያንን የባላባቱን ግጥም ራሱ ሊያነብልን ነው በልና ቶሎ ሻዩን ይዘህለት ና" አለው አንዱ ደግሞ። ተላላኪው እየተፋጠነ በፈገግታ ወንበር አቅርቦልኝ መላኩቱን ሊያደርስ ሄደ። ወንድሜን ባየው ገና ጠረጴዛው ላይ የተቆለለውን ፋይል ያስተካክላል፣

እንኳን ገንዘቡን ሊሰጠኝ ቀና ብሎም አላየኝ። እኔ እንደገመትኩት እሱም የሌሎቹን መምጣትና የኔን ግጥም ማንበብ ይጠብቃል።

"ካፖርቱን ሰቀለው ምን ይዞ ያስቆምሃል? በከበሬታ ወንበር ቀርቦልሃል፣ ተቀመጥ" አለኝ። ሌሎቹም ቀበል አርገው "ተቀመጥ! ተቀመጥ!..." ብለው ጋበዙኝ። እኔ ግን የሁሉንም ሁኔታ ታዝቤ አልተቀመጥኩም።

ነገሩ ገባኝ። ወንድሜ ግጥም የምትጽፍ ታናሽ ወንድም አለችኝ እያለ በጓደኞቹ ዘንድ ያነሣሣኝ ኖሯል፣ እንደ ጉራ መንዣም ሳልሆን አልቀረሁም። ለዚህ ነው ክራኒ ሁሉ ገና ስገባ ዓይኑን ኮኮብ አስመስሎ እኔ ላይ የጣለው። ይህ በዓይናፋርነት ራሴን አስደፋኝ። ያናደደኝ ግን፣ ምሥጢር ነው ብዬ የሰጠሁትን "ባላባት" የተባለውን፣ በተማሪ ቤታችን በብዛት የሚገኙትንና በኛ በተራው ሕዝብ ልጆች የሚኰሩብንን፣ የዝቅዝቅ የሚያዩንን፣ እኛ በእግራችን ስንኳትን እነሱ በመኪና የሚንሸራሸሩትን የመኳንንትና የመሳፍንት ልጆች "ባለአባቶችን" ዘርጥጬ መቀለጃ ያደረግሁበትን፣ ስብከቴን እሁድ እሁድ ለሚሰሙት ምእመናን እንኳን ያላነበብኩትን ግጥም ወንድሜ ለቢሮ ጓደኞቹ ማንበቡ፣ እነሱ ደግሞ በተራቸው ለጓደኞቻቸው መንገራቸውና ጓደኞቻቸው ለጓደኞቻቸው መድገማቸው፣ ነገሩ እንዲህ ሲል ሲል አገር ግዛት ሚኒስትሩ ጆሮ ሊደርስ መቻሉና ከዚያም እንጉሡ ጆሮ መድረሱ... ነበር።

እዚያ ሁሉ ሰው ፊት ቆሜ መሳለቂያ ከምሆን፣ ለሱ ገንዘብ ብዬ እንደ አዝማሪ ግጥም ከማንበብ ሞት ይሻላል አልኩና ካፖርቱን ትቸለት ውልቅ ብዬ ከቢሮው ወጥቼ ወደ ቤቴ መጣሁ። አባብለው ሊያስቀሩኝ የሞከሩ ብዙ ነበሩ ግን አሻፈረኝ አልኩ። ወንድሜም የኔ እምቢተኛነት፣ ለኔ መታከሚያ ገንዘብ ከማውጣት ስለገላገለው እንደ ሌሎቹ ሊጋብዘኝ አልሞከረም። "ገንዘብ ካልፈለገ ተውት ይሂድ" ነው ያለው። የታላቁ ታላቅ በመሆኑ የኔን ደረቅነትና ቆራጥነት አያውቅም ነበር። እቤት ተመልሼ እናቴ በንዴትና በብስጭት ፊቴ ተለውጦ አይታ "ምነው? ገብረክርስቶስ ገንዘቡን እስጥሃለሁ ያለውን ከለከለህ እንዴ? "አለችኝ። ደጅ ጠኚ አድርጎ፣ ካፖርቱን አስይዞ እቢሮው ድረስ ካለፋኝ በኋላ የጓደኞቹ አጫዋች ሊያደርገኝ እንደሞከረ፣ ምሥጢር ብዬ የሰጠሁትን ግጥም ለማንም እንደነዛብኝ ለእናቴ በታላቅ ምሬት ዘርዝሬ ነገርኳት።

"ቆይ ግዴለም እንዲህ አረገ? አይዞህ አትበሳጭ አንተም ትምህርትህን ጨርሰህ የመንግሥት ሥራ ስትይዝ ከሱ የበለጠ ደመወዝ



ትበላለህ። ያንጊዜ ብድሩን ትመልስለታለህ አሁን ብርድ እንዳይነካህ በቡሉኮህ ተሸፋፍነህ ተኛ" አለችኝ።

ከሰዓት በኋላ ጀምሮ ማታውን ጭምር ያዲሳባ የክረምት ዝናብ ችፍ ችፍ ሲል ስለዋለና ስላመሸ ለጤናዬ በመፍራት ከቤት ሳልወጣ ቀረሁ። ማታ ባበሻ መድሃኒት ሥርዓት እሳቱ ነዶ ደረቴን ለሱ ሰጥቼ ብዙ ጊዜ ከሞቅሁ በኋላ በቡልኮ ተሸፋፍኜ፣ በዚያ ላይ ሁለት ብርድ ልብስ እናቴ ደርባልኝ ተኛሁ። ካበሻ መድሃኒት ጋር ያለኝ ጠብ ገና ከልጅነቴ ጣልያን ሲገባ ጀምሮ "ባሊላ" ተማሪ ቤት ስማር ነበር የጀመረው። ታመምኩና ተኛሁ። ትኩሳቱ በጣም ሃይለኛ ነበር። ግን ምች ነው ሲባል፣ አንደዬ ንዳድ ነው ሲባል፣ በሽታውና ትኩሳቱ በተቅማጥ ይወጣለታል ተብሎ አንዱ የእንግሊዝ ጨው አጠጡት ሲል ሲያጠጡኝ፣ አንዱ የለም ጉሎ ዘይት ነው ፍቱን መድኃኒቱ ሲል ሲያጠጡኝ፣ አንዱ የለም ከሁሉም የሚበልጠው ያጥንቱ ያው ያገራችን ኮሶ ነው ሲል ሲያጠጡኝ፣ በማከያው ድክምክም አልኩና እሞት አፋፍ ደረስኩ። ትኩሳቱም በተቅማጥ ሳይወጣልኝ ቀረ፣ እንዲያውም ከበፊቱ ባሰ። ያቃዥኝ ጀመር። በእንቅልፍ ልቤ እነጋገር፣ እቀባጥር እለፈልፍ ጀመር። በኋላ በጣም ስለተዳከምኩ፣ ያበሻ መድኃኒቱ ሁሉ ተሞክሮ ስላልሆነ፣ አባቴ ማታ እበረንዳ ላይ ለብቻቸው ቁጭ ብለው መልክአ ጊዮርጊስን ደጋግመው ይደግሙ ነበር። እናቴ ጨንቋት የምትሆነው አጥታ አልጋዬ ሥር ተንበርክካ እኔ በቅዠት ስቀባጥር ዓይን ዓይኔን ታይ ነበር።

"ምን ላርግልህ? እንዲያው ምን ላርግልህ?" ትለኛለች። እኔ በቅዠትና በህልም ልቤ ከቤቴ ወጥቼ ወደ ዱሮው፣ ወደ ታላቁ፣ ወደነ ሙሴ አንቶን ሐኪም ቤት በመሄድ ላይ ነኝ ይህን ስትለኝ። "እናንተ ካልወሰዳችሁኝ እኔ ራሴ በገዛ እግሬ ወደ ታላቁ ሐኪም ቤት መሄዴ ነው" ብዬ ኖሯል ከቀባጠርኩት መሀከል። ይህ ለሷ ጥያቄ ሖልስ አልነበረም። በቅዠት ውስጥ ሳለሁ የማንንም ቃል በትክክል አልሰማም ነበርና እሷንም ከልብ አልሰማኋትም። እሷ ግን ለጥያቄዋ መልሱን ከኔ እንደሰማች አርጋ ተረጎመችው። "መሞቱ ላይቀር ሐኪም ቤት ውሰጂኝ ሲለኝ ሳልወስደው ቢሞት በኋላ ፀፀቱን አልችለውም አለችና ሐኪም ቤት ልትወስደኝ ቆርጣ ሌሊቱን ካጠገቤ ሳትለይ አደረች። አባቴም ሌሊቱን በሙሉ አንድዬ" መልክ እየሱስን"፣ አንደዬ" መልክማርያምን"፣ "መልክ አቡነ አሮን" ሳይቀራቸው ሲደግሙ አደሩ። ይህ ሁሉ እኔን ከሞት አፋፍ ለመመለስ ነው፣ ግን እሳቸውም ተስፋ ቆርጠው ነበር።

ጧት ወፍ ሲንጫጫ እናቴ ተነሣችና እኔን ለአይከሬ አሣዝላ፣ ጣይ መቶኝ ምችው እንዳያገረሽብኝ ጣይ ሳትወጣ አደሬ ግምብ ውስጥ ከመድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን አልፎ ካለው" ከጆግላ" ሀኪም ቤት ይዛኝ ሔደች። እኔ በቅዠት ትልቁን ሐኪም ቤት ያነሣሁት ከጣልያን በፊት የነሙሴ አንቶን የሚሲዮን ሐኪም ቤት የነበረውን ነው። እሱን ግን ጣልያኖች የነጭ ብቻ መታከሚያ ስላደረጉት የጥቁር መታከሚያው የጆግላ ነበርና ለዚህ ነው። ሐኪሙ ጆግላ ገና ሲያየኝ ሁለት መርፌ ወጋኝና ለምን እንዲያ እስከሆን ድረስ ወደሱ እንዳላመጡኝ ጠየቀ። እናቴም "ያበሻ መዳኒት ይሻላል ብለን ነው" አለችው። ወዲያው ክፍል ተያዘልኝና ተኛሁ። ሌሊት በእንቅልፍ ልቤ መለፍለፍ ብቻ ሳይሆን ተነሥቼ ልሂድ እያልኩ አስቸግር ስለነበር ሶስቱም ታላቅ ወንድሞቼ በየተራ ያድሩልኝ ነበር። የሆነ ሆኖ አንድ ሶስት ሳምንት ከተኛሁ በኋላ ከህመሜ ድኜ ግን አጥንት ብቻ ሆኜ ወደቤት ተመለስኩ። ከሞት አፋፍ ነው የተመለስኩት። ከዚያ ያደረሰኝ ያበሻ መድኃኒት ነው። የመለሰኝ የፈረንጅ ሀኪምና የፈረንጅ መድኃኒት ነው። በዚህ ምክንያት ነው የብርድ በሽታ ደረቴን ቢመታኝ እፈረንጅ ሐኪም ዘንድ ካልሄድኩና ሂጄም ያዘዘልኝ መድሃኒት ተገዝቶልኝ መርፌውን ካልተወጋሁ ብዬ ድርቅ ያልኩትና ወድሞቼን ገንዘብ አምጡ ብዬ ወጥሬ የያዝኳቸው። ምን ያረጋል ገንዘብ ሳይገኝ ቀረ፣ እኔም እናቴን አምጪ ማለቱን ጠልቼ በቡልኮ ተሸፋፍኜ ቅቤ ያጥለቀለቀው ቅንጬ እየበላሁ በብስጭት ተኮራምቼ ቁጭ አልኩ። እቤት ዋልኩ። ነገር ግን ባጋጣሚ ከእናቴ ቀላድ ከሱሉልታ፣ ከሣር ይሁን ከእህል ሽያጭ የተገኘ ገንዘብ ቡሎ ወርዶፉ ይዞላት ስለመጣ እናቴ አርባ አራቱን ብር ሰጠችኝና "ሂደህ ታከም እነሱን ወንድሞችህን ተዋቸው። እነሱ እምቢ ቢሉህ እኔ እናትህ አሳክምሀለሁ" አለች- በነሱ ሁኔታ ተናዳ። "ዱሮውኑስ እነሱን ትተህ እኔን እናትህን ነበር መጠየቅ፣ ከምንም ብዬ አገኝልህ ነበር። ምን ያርጉ? አልወለዱህ" አለች።

መድኃኒቱ ተገዛ፣ መርፌውን ተወጋሁ፣ ደረቴን የጨመደደኝ በሽታም ጥሎኝ ሄደ ዳንኩ። ብድንም የወንድሞቼ ሁኔታ ስለ ዘመድና ስለ ዝምድና ብዙ አመራምሮኝ ነበርና ስሜቴን በግጥም እንድጽፍ አስገደደኝ። ግጥሙን ተማሪቤት በመስከረም ሲከፈት ለኔ ምእመናን አነበብኩላቸው። "ዘመድ" ነበር አርዕስቱ:-

ዝም ያለው ዘመዴ እኔ ሳጣጥር፣
ዝም ያለው ወንድሜ እኔ ሳጣጥር፣
ሞተ ቢሉት መጣ አልቅሶ ሊቀብር።
የልቤን እንዳደርስ የእዚአብሔር ፈቃዱ፣



ሆኖ ተነሥቼ፣ እነ እሱ ሲያረግዱ።
እንዲህ አልኩት ዘመድ የተባለውን፣
እንዲህ አልኩት ወንድም የተባለውን፣
ታምሜ ነበረ ሳጣጥር ማዘን።
አሁን "ክንዴ ክንዴ ቀኝ እጄ" ቢሉኝ፣
አሁን "የናቴ ልጅ ወንድሜ" ቢሉኝ፣
ከሞትኩኝ በኋላ ምንም አይገባኝ፣
ይልቅ ልተኛበት አታደንቁረኝ።
ይህን ተናግሬ የልቤን አድርሼ፣
ወደ መጣሁበት ሄድኩኝ ተመልሼ።

የብርዱ በሽታ አሞኝ እቤት በዋልኩበት ሰሞን ብዙ ጨዋታዎች ከአባቴ አፍ እየሰማሁ በማስታወሻ ይዤ ስለነበር ከዚያ በኋላ የተረትና የታሪክ ችግር አልነበረብኝም። አባቴ እኔም ልነግራቸው አልደፈርኩም። እንዲያውም እንዳይሰሙብኝ እንዳያውቁብኝ ነበር የምፈራው። ቢሰሙ ኖሮ በማይረባ ዋዛ ፈዛዛ ጊዜዬን በማባከኔ እንደሚቆጡ አይጠረጠርም። ለሳቸው ግጥም ማለት በግእዝ የሚገጠመው መልክአ ነው። ከፍ ሲል ደሞ ደረጃው ግጥም ማለት የግዕዙ ቅኔ ነው። ያማርኛውን እምብዛም ከጉዳይ አይጥፉትም። ሆኖም በየጊዜው የምጽፋቸው ግጥሞች ቁጥር እየበረከተ ሄደ። በደረጃቸው ግን ሁሉም እኩል አልነበሩም። አንዳንዶቹ ወደ ፍሬ ከርስኪነቱ የሚያዘነብሉም ነበሩ። ቢሆንም የግጥም መፃፊያ ደብተሬ በየጊዜው እየተጫረበት አበጥ እያለ ሄዶ ነበር።

ከዚህ ደረጃ እንደደረስኩ የለንደን ዩኒቨርስቲ መግቢያ "ማትሪኩሌሽን" የሚባል፣ ከዚያ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ፈተና ከእንግሊዝ አገር በብሪቲሽ ካውንስል በኩል መጣና በሚስተር ሊትለር ፈታኝነት ተፈትነን ፈተናውን ስላለፍኩ ወደ እንግሊዝ አገር እንድሄድ መንግሥት ፈቀደ። የምሄድበት አንጉል ጊዜ በፈረንጆች ዓመት መጀመሪያ፣ በኛ በጥር ወር ነበርና የፈረንጅ የሱፍ ልብስና ወፍራም ካፖርት በልካችን ተሰፋልን፣ ባርኔጣ ተገዛልን። ኮፍ ጫማ ዓይኑን አፍጦ መጣ። እኔ ግን ልብሱንም ጫማውንም ሞክሬ አስቀመጥኩት እንጂ በአውሮፕላን መሣፈሪያዬ ቀን እስኪደርስ አልለበስኩትም። በዚያን ሰሞን አራት ኪሎ በቅድስት ሥላሴ ግቢ ስለ አማርኛ ፊደል መሻሻል የተጧጧፈ ክርክር ሲቀልጥ ወደ እንግሊዝና ወደ አሜሪካ የምንላከው ልጆች ክርክሩን እንድንሰማ በትምህርት ሚኒስቴር

ተጋብዘን ነበር። ከጉባዔው የገባነው ከኔ ሌላ ምናሴ ኃይሌ*፣ ኃይለ ማርያም ከበደና ሌሎችም ነበሩ። ወደ ጉባኤው ስንገባ አዳራሹ ከዳር እዳር ጢም ብሎ ሞልቶ መድረኩ ላይ ሁለቱ ተከራካሪዎች አቶ አበበ ረታና ** ብላታ መርስዔ ሃዘን ወልደቂርቆስ*** ተፋጠዋል። ሊቀመንበሩ ብላታ ዘውዴ በላይነህ እነሱን ግራና እቀኝ አድርገው እመሀከል ከፍ ባለ ቦታ በግርማ ተቀምጠዋል። ኮሎኔል ታምራት ይገዙ የራስ እምሩን ሃሣብ ይዞ መጥቶ ተመልካቹ ህዝብ ከሚቀመጥበት በግምባር ቀደም በመጀመሪያ ረድፍ ተቀምጧል። አቶ ብርሃኑ ድንቄም**** ከሱ በኋላ በሶስተኛው ነው በአራተኛው ረድፍ ተቀምጧል። ለኛ ለወጣቶቹ የተያዘልን ቦታ አዳራሹ መሀከል ላይ በስተቀኝ ሲል ነበር።

ገብተን ቦታችንን የያዝነው በላቲን ሥርዓት፣ በላቲን ፊደል አንፃፍ የሚለው የብላታ መርስዔ ሐዘን ሃሣብ ወደ መሸነፉ አጋድሎ፣ የኛን ፊደል ቅጥሉን አንድ ዓይነት አድርገን አሻሽለን በሱ እንሥራ የሚለው የአቶ አበበ ረታ ሃሣብ ሳያሸንፍ ክርክሩን የሚያዳምጠው ሕዝብ ያቶ አበበን እንቀበለው አንቀበለው ብሎ ተጨንቆ በሚያመናታበት ደቂቃ ላይ ነበር። የተከራካሪዎቹ ሃሣብ መቼም ቀደም ብሎ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ተጋግሎ ነበርና እፊታችን ቁጭ ብለው ያየናቸው አቶ ብርሃኑ ድንቄ የጥንታዊው የሐገራችን ፊደል ጠበቃ ሆነው፣ አይነካ አይቀነስ፣ አይለወጥ ብለው በጋዜጣው ላይ ሽንጣቸውን ገትረው በመከራከራቸው፣ የማደንቃቸውና በሐሳብም የምደግፋቸው ነበሩ። እኔም በተማሪነት አቅሜ የአባታችን፣ የቅድመ አያታችን፣ ታሪካችንና ሃይማኖታችን የተፃፉበት ፊደል አይነካ የምል ስለነበርኩ አቶ ብርሃኑ ድንቄን በመደገፍ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅ ለብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ በወዳጃቸው በምናሴ ኃይሌ እጅ ከፍ ያለ መጣጥፍ እንዲያትሙልኝ ልኬ ነበር። እሳቸው ግን ያን ጊዜ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበሩትን ቀንደኛ ተከራካሪና የብርሃኑ ድንቄ ተቃዋሚ የሆኑትን አቶ አበበ ረታን ፈርተው የኔን ጽሑፍ ሊያትሙልኝ ካሉ በኋላ ሳያትሙ በዚያው በምናሴ በኩል መልሰውልኛል። በዚያን ጊዜ የአማርኛ ፊደል ይሻሻል የሚባልበት

---

* በ1950ዎቹ መጨረሻና በ 1960ዎቹ መጀመሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት። /አርታኢው/

** የእርሻ ሚኒስትር፣ በኋላም የጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበሩት።

*** የመጀመሪያው የብርሃንና ሰላም፣ ጋዜጣ ጋዜጠኛ፣ በተፈሪ መኮንን ትምቤት የግዕዝና የአማርኛ አስተማሪ የነበሩ፣ የሰዋሰው መማሪያና "ሄሮዶቱስ" የተባሉት መፅሐፍት ደራሲነታቸው የታወቁ (አርታ)

**** በአሜሪካ አምባሣደር የነበሩትና በደራሲነትም የሚታወቁት ። /አርታ/



ዋናው ምክንያት ለታይፕራይተር አያመችም መባሉ ነበር። እኔ በበኩሌ ለታይፕራይተር አሳምሮ እንደሚመች ለብላታ ወልደጊዮርጊስ በላኩት ጽሑፍ ደህና አድርጌ አሳይቼ ነበር። ያን ጊዜ የአማርኛ ታይፕራይተር ገና አልተሰራም ነበርና፣ ክርክሩ በዚያ ላይ አተኩሮ ነበር። በተመልካችነት ተጋብዘን የተገኘንበት ጉባኤ ግን ሚኒስትሮችና ታላላቅ ሰዎች የሚከራከሩበት፣ ስንትና ስንት ሰው ጢቅ ብሎ የሞላበት፣ የሰው ዓይን ብቻ እንደኔ ያለውን ዓይን አፋር ወጣት የሚገድል የሚመስልበት ጉባኤ ስለነበር፣ ከኔ ከራሴ የሃይማኖት ስብከተ ጉባኤ በጣም የተለየ ሆኖ ታየኝ። ስለዚህ ምንም እንኳን ቱርክ ፈረንጅ ሆናለችና እኛም ፈረንጅ እንሁን የሚለው የመርስኤ ሐዘን ሐሳብ መረታቱ ቢሰማኝ፣ " አልሸሹም ገለል አሉ" የሆነው የራስ እምሩ ሐሳብ ወድቆ አይቀርም ብዬ ደስ ቢለኝ፣ ከሁለቱም ይብሱን አደገኛ የሆነው የአቶ አበበ ረቂቅ የማባበያ ሐሳብ አልወድቅም ብሎ ሲንገዳገድ፣ አንዳንዴም የመርስኤ ሐዘንንም የራስ እምሩንም ማየቴ፣ የኔንም የጥንታዊ ፊደል ጠበቃነት - ወኔዬን ነሸጥ አድርጎት ነበር። ግን ማንደፍሮ በዚያ ሁሉ ሕዝብ መሐከል? ኧሳቱ፣ መብረቁ አቶ ብርሃኑ ድንቄ እንኳን ትዕግሥቱን ሰጥቷቸው በተቀመጡበት መቁነጥነጥ እንጂ መናገር ባልፈለጉበት ጉባኤ እኔን ምን ጥልቅ አደረገኝ? ብዬ አርፌ ተቀምጬ፣ የመርስኤ ሐዘንን መብገን፣ የአቶ አበበ ረታን በሳቸው ላይ መጀነን በምጸት ዓይን እመለከታለሁ።

እዚህ ላይ ምናሴ ኃይሌና ኃይለ ማርያም ከበደ ከኋላዬ ተቀምጠው ሲንሾካሾኩ ነበርና ምናሴ ካጠገቤ ተነስቶ ሄደ። የጉባኤውን አስተናባሪ ያን ጊዜ የትምህርት ሚኒስቴር ዋና ጸሐፊ የነበሩትን አቶ መኮንን ዘውዴን ደፍሮ በጆሮዋቸው ምናምን ሲነግራቸውና፣ እሳቸውም "እሺ፣ በጄ" እንደማለት ራሳቸውን ላይ ታች ሲወዘውዙ አየሁ። ግን የግል ጉዳይ ይኖረዋል ብዬ ነገሩን ከምንም አልጣፍኩትም። ወዲያው ድንክዬው ሊቀመንበር፣ "ሌላ ተከራካሪ፣ ሌላ ተናጋሪ ያለ አይመስልምና እንግዴህ ሐሳቡ የሁሉም ተሰምቷል" አሉ።

"የለም ጌታዬ ክቡር ሊቀመንበር፣ ተናጋሪ አላለቀም ገና አንድ አለ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ውጭ አገር መንግሥት የሚልካቸው ወጣቶች ክርክሩን እንዲያዳምጡ በትምህርት ሚኒስቴር ተጋብዘው እዚህ እመሀላችን ይገኛሉ። እነሱ የሚሉት 'በዚህ ታላቅ ጉባኤ ላይ ከኛም ወገን የምናቀርበው ሐሳብ ስላለን፣ ሐሳባችንን ከኛው መሐከል የሚያቀርብልን ሰው ስለመረጥንና እሱም እዚሁ እመሀከላችን ስላለ እንዲናገር ጉባኤው ይፍቀድልን' ነው

የሚሉት፣ " አሉ አስተናባሪው። ይህ ሲሰማ ሕዝቡ በሹክሹክታ ሲንቻቻ ቤት እንደሚለውጥ የንብ ሠራዊት ያስገመግም ጀመር።

"ይህ አዲስ ነገር ነው የሚፈቀድ አይመስለኝም። የጉባኤውን ሥነ ሥርዓት ያፈርሳል። የሚናገር ሰው እንዳለ ስሙን አስቀድሞ እንዲያስመዘግብ ጠይቀን፣ የተመዘገቡት ተናግረዋል አሁን አዲስ ተናጋሪ መቀበል አንችልም፣ " አሉ ሊቀመንበሩ።

"ወጣቶቹ የመጡት ከኮተቤ ድረስ ነው። በመኪና መታጣት ምክንያት ነው የዘገዩት" አሉ አስተናባሪው።

ሊቀ መንበሩ ወጣቶቹን እምቢ ብለው ወጣቶቹ እንዲጠሏቸው አልፈለጉም። ስለዚህ በግራና በቀኛቸው ያሉትን ሁለቱን ተከራካሪዎች በየተራ ጠየቋቸው። መርስኤ ሐዘን መሸነፋቸው የማይቀር መሆኑ ግልፅ ጉዳይ ስለሆነ፣ ሐሳብ አለኝ የሚል ሁሉ ቢናገር አይከፋም የሚል ሃሳብ አቀረቡ። ይህ ብልጠት ነው። ተናጋሪው ሲበዛ ንግግሩ ይበዛል፣ ረጅም ጊዜ ይወስዳል፣ በመካያው ሰዓቱ ያልፍና መሸብኝ ብሎ ሰው ሁሉ ወደየቤቱ ይሄዳል፣ ውሳኔው በይደር ይተላለፋል፣ አቶ አበበም "ተረታ" ባይሆኑ ለጊዜው" ረታ" መሆናቸው ይቀራል። አቶ አበበ ደግሞ ይህንን በደንብ ተረድተዋልና፣ የስብሰባው ሥነ ሥርዓት መከበር እንዳለበት፣ አስቀድሞ ያልተመዘገበ አዲስ ተናጋሪ እንዲናገር ከተፈቀደ ነገሩ ምን ጊዜም እንደማይቆረጥ በማለት ለመርስኤ መልስ ሰጡ። ግን እሳቸውም ቢሆኑ አዲሱን የተማረ ወጣት ትውልድ ሊያስቀይሙ ስላልፈለጉ፣ "ቢሆንም ከወጣቱ ወገን ያለውን አስተሳሰብም ብንሰማ ክፉ አይደለምና ከነሱ ከወጣቶቹ አንድ ብቻ ተናጋሪ ቢፈቀድ በበኩሌ አልቃወምም፣ ከሱ ሌላ ተጨማሪ ተናጋሪ ግን አልቀበልም" አሉ። መርስኤ ሐዘንም ወዲያው በመለጠቅ "እኔም ወጣቶቹን እደግፋለሁ" አሉ። እነ ምናሴና ኃይለ ማርያም በድንገት ጭብጨባቸውን ለቀቁት። ሕዝቡም የነሱን አርአያ ተከትሎ አጨበጨበ። ጭብጨባው ሲበርድ ሊቀመንበሩ" የወጣቶቹ ተናጋሪ ታዲያ የታል? ማነው? ይጠራ፣ ይቅረብ። አለ የለም?... አቶ መኮንን ስሙን ይዘኸዋል?" አሉ። አስተናባሪው፣ " ስሙ እዚህ አለ፣ " አሉና የያዙትን የስም ዝርዝር አየት ካረጉ በኋላ የአዲሱን ትውልድ ተወካይ ወጣት ተናጋሪ ስም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ጠሩ። አንባቢ ሆይ፣ ይህ ተናጋሪነቱን እስከዚያች ደቂቃ፣ እስከዚያች ሴኮንድ ድረስ ያላወቀው የአዲሱ ትውልድ ተወካይ ማ ይመስልሃል?



"መንግሥቱ ለማ! መንግሥቱ ለማ የሚባል ተማሪ ይውጣና ይናገር" አሉ አስተናባሪው። በድንጋጤ የምይዘውን አጣሁት። በግራና ቀኝ፣ ከፊትም ከኋላም የተቀመጡት የዘመኑ ወጣት ተማሪ ጓደኞቼ ሁሉ ነገሩ በጣም አስቆአቸው "ተነስ! ተነስ! ተነስ! "እያሉ ይጎተጉቱኝ ጀመር።

"መንግሥቱ ለማ የሚባለው ተማሪ የታል?" አሉ አስተናባሪው" "ይጠበቃል እኮ! ጊዜ የለንም"... እኔ ግን አስተናባሪው እንዳያዩኝ ከወንበር ወርጄ እመሬት ተደብቄአለሁ። "የታለ፣ የለም እንዴ?" አሉ አስተናባሪው መልሰው። እኔ በዚያች ደቂቃ ያለሁበት የመንፈስ ሁኔታ በድንጋጤው ላይ የዓይን አፋርነት ጭንቀትን፣ በዚያ ላይ ደግሞ ንዴትን ያደባለቀ ነበር። ንዴቱና ቁጣው በምናሴ ኃይሌና በኃይለ ማርያም ከበደ በኒያ በሁለቱ ተንኮለኞችና ቀልደኞች ነበር። ቢሆንም ምናሴ ተነሥቶ ለአስተናባሪው መለሰላቸው፣ " መንግሥቱ ለማ አለ ይኸው እዚህ ነው..." አለና ከኃይለ ማርያምና ከሌሎቹ ባለጡንቻዎች ጋር ተጋግዘው ከተወሸቅሁበት ጎትተው አወጡኝ። የግድ በጉልበታቸው በዚያ በጉባኤ መሀከል አቆሙኝ።

እኔ በሥራቸው ጭስስ ብዬ ከግልፍታዬ ኃይለኝነት የተነሣ አፌ ተሣስሮ "ቆይ አንተ ምናሴ! ቆይ! ይህን ያደረግኸኝ አንተ መሆንህን እስከሞት ድረስ አልረሳውም!... ቆይ እንተያያለን!" እያልኩ ዛትኩበት፣ ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ እያለ።

"ምን አሁን እዚህ ትደበቃለህ?" አለ ኃይለ ማርያም የምናሴ ቢጤው። "ምና ይወሽቅሀል? ፊደላችን አይለወጥ እያልክ እተማሪ ቤት አሰልችተኸናል፣ እዶርሚተሪ ሌሊት አላስተኛን ብለሃል። አሁን ይኸውልህ ወንድነትሀን ማሳየት ነው!" አለ በፌዝ እየሳቀ። ምናሴም ቀበል አድርጎ "ይውጣልህ ብለን ነው እኔና ኃይለ ማርያም ስምህን ለአቶ መኮንን ያስመዘገብነው! ምን ታመናታለህ? ሂድ!" አለና ወደ መተላለፊያው ኮሪደር በኃይል ገፋኝ። ከዚያ ሌሎቹ ተማሪዎች ተቀባበሉኝና ከነሱ መሀከል አስወጥተው በጉባኤው ሕዝብ መሀከል ብቻዬን አቆሙኝ። የተሰበሰበው ሕዝብ በውነት ተማሪ መሆኔን ከአለባበሴ አይቶ በጭብጨባ አበረታታኝ። እኔም ካይናፋርነት የተነሣ ሳልገለማመጥ መሬት መሬቱን ብቻ እያየሁ መተላለፊያውን ተጉዤ የመድረኩን ደረጃ ራሴን ደፍቼ ወጣሁ።

በፊደል መሻሻል ጉባኤው ላይ ከዚያ ሁሉ ሰው ፊት ቆሞ፣ ከሚኒስትሮችና ከታላላቅ ባለሥልጣኖች መሀከል ቆሞ መናገር ልክ

በልጅነት ያበሻ ኮሶ እንደመጠጣት ሆኖ ታየኝ። ጭብጨባው እንደናቱ ሙገሣ ነበር። ኮሶው ደሞ ዲስኩር ማድረጉ ነበር። ሁኔታው ሞት ነበር የመሰለኝ-ሲያስፈራ። አለመናገሩ ግን፣ እምቢ ብሎ ይቅርታ መጠየቁ ግን፣ በተማሪ ቤታችንና በጓደኞቼ አይን የሞት ሞት ስለሆነ በነፍሴ ቆርጬ ልናገር ተሰናዳሁ። "ቆራጥና ጭስ መውጫ አያጣም" የሚለው ያባቶቻችን ምሳሌ ድንገት ሳላስበው ከህሊናዬ ድቅን አለ።

“መንግስቱ ለማ የተባለው ወጣት ይኸ ነው?" አሉና ሊቀመንበሩ የሥራ ሚኒስትር ከእግር እስከራሴ የዝቅዝቅ ተመለከቱኝ። ልብሴ ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የተረፈ የካናዳ ፈረሰኛ ወታደሮች የካኪ ዩኒፎርም ሲሆን ለኢትዮጵያ በርዳታ የተሰጠ ነበር። ለክቡር ዘበኞች ስላጠራቸውና ስለጠበባቸው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንዲለብሱት የተደረገ ነው። ሱሬው ረዝሞብኝ እባት ላይ የሚውለው ጥልፍ ወርዶ እቁርጭምጭሚቴ ላይ ተዘፍዝፎ፣ እግሬ ላይ መሆኑን ሚኒስትሩ አይተው፣ እሳቸው ፊት በዚህ በታላቅ ጉባኤ መድረክ ላይ እንደኔ ያለ አስጠያፊ ፍጡር በመገኘቱ በጣም ቅር ያላቸው መሆኑን በገጻቸው ሳስተያያቸው፣ በቃል አጣጣላቸው አስረዱኝ። ይህ እልክ አስገባኝ "ቆይ አንቺ ድንክዬ" አልኩኝ በልቤ። "እቶ ዛፍ! ዛሬ ባላሳይሽ እኔ አይደለሁም!" አልኩ በእልክ ድፍረት። ዓይንአፋርነቱ በአንዴ ተገፈፈልኝ። ድምጼን ከፍ አድርጌ ንግግሬን ጀመርኩት። በተማሪ ቤታችን እሁድ እሁድ ማታ ከሁለት ዓመት በላይ ሃይማኖት መስበኬ ለካ ሳላውቀው ዲስኩር መናገር አስተምሮኝ ኖሯል። ንግግሩን ገና ስጀምር፣ በኔ አስተያየት የቆየው ታሪካችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው፣ ከኦሪት ጀምሮ ወንጌልን ይዞ የቀሩት መጽሐፍት ቅዱሳት የተጻፉበት ያገራችን ፊደል ከፈረንጅ ፊደል ምንም የሚያንስበት፣ ያገራችን ፊደል ከፈረንጅ ፊደል ምንም የሚያንስበትና የሚበዛበት ስለሌለ ይለወጥ ወይም ይሻሻል የሚለውን ሐሳብ በፍጹም የምቃወም መሆኔን ስገልጥ ጭብጨባው ከዳር እስከ ዳር አስተጋባ። አቶ ብርሃኑ ድንቄ በተለይ ከሩቅ ሳያቸው ፈንጥዘውም አላባሩ። እነ ምናሴም እኔን ማጋፈጣቸው በዚያ በታላቅ መድረክ ላይ አንድ ዓይነት ቴአትር ማየታቸውን ጨዋታውን ስለሆነ የፈለጉት ፊደል ይለወጥ አይለወጥ የሚለውን ሃሳብ ከቁጥር ስለማያገቡት፣ እንደሚወዱትና ሱስ እንደሆነባቸው የፋትቦል ኳስ ጨዋታ የነሱ ቡድን ተጫዋች ደህና አመታት ስለመታ ብቻ ተደስተው ነበር ጭብጨባውን የጀመሩት። ሌላው ሰው ካቆመም በኋላ ለጥቂት ሴኮንዶች ቀጠሉበት። እኔ ያን ጊዜ እንደገመትኩት ሕዝቡ ገና ከመጀመሪያው ቀጥዬ ምን እንደምል ሳያውቅ፣ ለኔ እንዲያ አድርጎ ያጨበጨበው የልቡን ስለነገርኩት ነበር። ከተሰበሰበው ከመቶ ዘጠና አምስት እጅ በፊደላችን የሚኮራ፣ ፊደላችን እንዳይነካ የሚመኝ፣ ለፊደሉ ሙት ቢሉት



የሚሞት ነበር። የላቲን ፊደል እንቀበል የሚለውን ሀሳብማ ጣልያን ተመልሶ ይግዛን እንደማለት ነበር የቆጠረው። ግን ከሕዝብ ውስጥ ይህን ሐሳቡን ደፍሮ በጉባኤው ላይ የሚናገር አንድ እንኳን አልነበረም። ባለሥልጣኖቹን ይፈራል፣ ምን ይደረግ? አበበ ረታ፣ ዘውዴ በላይነህ የመንግሥት ሚኒስትሮች ናቸው። መርስኤ ሀዘንም ወደዚያው ናቸው፣ አስተናባሪው አቶ መኮንን እንኳን የትምህርት ሚኒስትር ዋና ጸሐፊ ናቸው። ኮሌኔል ታምራትም የደጃች ይገዙ ልጅ፣ ታላቅ መኳንንት ናቸው።

የባሰ ይባስ ታምራት ይገዙ ይዘው የቀረቡት የራስ እምሩን ፊደላችን ይለወጥና በፈረንጅ መንገድ ይሥራ የሚለውን ሀሳብ ነው። ራስ እምሩ የደጃች ኃይለሥላሴ ልጅ ናቸው። ደጃች ኃይለሥላሴ ዓባይ ደግሞ ከራሳቸው መኳንንትነት ሌላ የንጉሡ ነገሥቱን እክስት አግብተው እምሩን የወለዱ ናቸው። ስለዚህ በህዝቡ አይፈረድም። እርግጥ በህዝቡ መሀከል የፊደላችን ጠበቃና አርበኛ አቶ ብርሃኑ ድንቄ ተገኝተዋል። እሳቸውም ቢሆኑ በዝምታ ሁኔታውን አንጀታቸው እያረረ ይመለከቱት ነበር እንጂ ለመናገር አልፈለጉም። በጋዜጣ ላይ አቶ አበበ ረታን ተሟግተዋል፣ በክርክሩ ስላልተቻሉ የባለሥልጣን ተጽእኖ ወድቆባቸው የሳቸው የክርክር ጽሑፍ በጋዜጣ እንዳይታተም ታግዶባቸዋል። እሳቸውንም ሆነ ሌላውንም ሕዝብ ከልብ ያስፈነደቀው ከዘመኑ የተማሩ ወጣት አንዱ ያውም ወደ ውጭ አገር እንዲሄድ የታጨ የአዲሱ ትውልድ አባል የሆነ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ፊደላችን ከማንም ፊደል አያንስምና አይለወጥም ማለቱ ነበር። ተከራካሪዎቹን ሁለት ባለሥልጣኖች፣ ሊቀ መንበር የሆኑትን ሚኒስትርና ኮሎኔል ታምራትን ጭምር ይህ ያልታሰበ አዲስ ሁኔታ በመጀመሪያ አስገርሟቸዋል፣ ቀጥሎ ደግሞ አስደስቷቸዋል። ቀጥሎ አስቆጥቷቸዋል። ግን ሁሉንም እኩል አልነበረም ነካ ያደረጋቸው።

ፊደላችን አይለወጥ፣ ከብዙው ይሻላል፣ ከማንም አያንስም የሚለው ሐሳብ ከተማረው፣ ከአዲሱ ትውልድ አንዱ ከሆንኩት ከኔ አፍ መውጣቱ ያስገረማቸው ሁሉንም ነው። ውስጥ ውስጡን ያስደሰታቸው የለውጥ ሐሳባቸው ውድቅ በመሆኑ መሸነፍ የተሰማቸውን መርስኤ ሐዘንንና ታምራትን ነው። ያስቆጣቸው ደግሞ ሐሳባቸው ሊረታና ሊያሸንፍ አፋፍ ላይ ከደረሰ በኋላ በኔ ምክንያት ሊጨናገፍባቸው የሆነውን አበበ ረታን ነበር። ስለዚህ ዋናው ተከራካሪ አቶ አበበ ረታ ሆኑና ሌሎቹ በመንፈስ የኔ ደጋፊ ሆኑ። ድጋፍ የሰጡኝ እኔን ወይም ሐሳቤን ወደው ሳይሆን የነሱ ወድቆ ያቶ አበበ ከሚያሸንፍ የሶስቱም አንድነት ውድቅ ቢሆን ይሻላል በሚል በ "እኔ ከሞትኩ

ሥርዶ አይብቀል" ስሜት መሆኑ ቀስ በቀስ በሙግቱ ላይ ተገለጸልኝ። በበኩሌ ፊደላችን አይለወጥም ብዬ ስከራከር፣ መርስኤ ኃዘን "ቱርክ የጥንት ፊደሎቿን ትታ ለዘመኑ ሥልጣኔ አሠራር የሚያመቻችትን የላቲን ፊደል ተቀብላለች "ብለው ላቀረቡት ክርክር "ቱርክ ታዲያ የራሷን ፊደል ጥላ በሥልጣኔ እርምጃ የት ደረሰች? ከዚያው ዱሮ ከነበረችበት ጥቂት እንኳን ፈቀቅ አላለችም። ጃፓን ግን ከኛ ፊደል መቶ ጊዜ፣ ሺ ጊዜ የሚያስቸግረውን የራሷን ፊደል ይዛ በሥልጣኔ እርምጃዋ ያለ መጠን በእጥፍ በድርብ በማደግ በመመንደግ፣ በጦርነት እንኳን ድሮ መስኮብን ቀጥሎም ስምንት መቶ ሚሊዮን ሕዝብ ያለውን ቻይናን አሸንፋለች። በአቶሚክ ብትሸነፍም ወደፊት ባጭር ጊዜ ውስጥ ያቶሚክ ቦምብ ትሠራለች። ይህ የሚያሳየው ያንድን አገር የሥልጣኔ እርምጃ ወደ ኋላ የሚያስቀረው ሌላ ሌላ ነገር ነው እንጂ ፊደሉ አለመሆኑን ነው። "ይህን ስል አንጀቱ የራሰው፣ የጉባኤውን አዳራሽ ጢም ብሎ ካፍ እስከገደፉ የሞላው ሕዝብ አጨበጨበ። ቀጥዬ አቶ አበበ ረታ ፊደላችን ለእጅ መኪና ጽሕፈት አይመችም ላሉት ስመልስ" የፈረንጁ የፊደል ገበታ ሃያ ስድስት ፊደላት ብቻ ነው ያሉት ቢባልም በፈረንጁ ታይፕራይተር መኪና ላይ የሰፈረው ሁለት የተለያየ የፊደል ገበታ/ ትልቅና ትንሽ - Small & Capital letters/ መሆኑን፣ ስለዚህ የፈረንጁ ፊደል ጠቅላላው ቁጥር ሃያ ስድስት ሳይሆን ሃምሳ ሁለት መሆኑን፣ የእኛም ቅጥሎቹን ከፊደላቱ ለይተን በመኪናው ላይ ብናሰፍራቸው ቅጥላቸው ተለይቶ ለብቻው ቢሰፍር፣ የማይቻለውን ፊደላት እንዳለ ብናስቀምጣቸው እንዲሁም እነ ቸ.ጀ.ዥ.ጹ.ቷ.ኅ. ... ወዘተን በዋና ፊደላቸው ብቻ ብንተካቸውና ተጨማሪውን ምልክት ለብቻው ብናሰፍረው ለጽሕፈት መኪና የማያስቸግሩ መሆናቸውን በብላክቦርድ (ጥቁር ሰሌዳ) ላይ በጠመኔ እየጻፍኩ አሳየሁኝ።

አቶ አበበ ረታ ቱግ ብለው ልዩ ልዩ ጥያቄ በከበሬታ ወረወሩብኝ። እኔ ግን ያለ ፍርሐት መለስኩላቸው። ሕዝቡ አጨበጨበ። በተጨማሪ "የአማርኛ ፊደል ለጽሕፈት መሣሪያ ይመቻል አይመችም ብሎ ለመናገር የሚችል የዚህ ዓይነት ጥበብ ባለሟያ የሆነ ሜካኒካል ኢንጂነር መሆኑን አስረድቼ ሳበቃ፣ እዚህ ከተሰበሰብነው ተከራካሪዎች መሀከል ሜካኒካል ኢንጂነር የሆነ ሰው ስለሌለ፣ የፅህፈት መኪናውን ነገር አንስቶ መናገር መከራከር እኛን አያገባንም" አልኩ። የኔ ንግግር በዚያ ማብቃቱን ለሊቀ መንበሩ አስታውቄ ከመድረኩ ወርጄ ወደ ቀድሞው መቀመጫዬ ሳመራ የህዝቡ ጭብጨባ ቀለጠ። ወዲያው ትርምስ ሆነ። ሊቀመንበሩ ሕዝቡን መቆጣጠር አቃታቸው። ዘወር ብዬ ባይ መርስኤ ኀዘን ይስቃሉ። አቶ አበበ ረታ ግን ተከትለውኝ ኮቴን ጎትተው አቆሙኝና በጩኸት፣ በዓይን ፍጥጫና በቁጣ በታጀበ ክርክር ገትረው ያዙኝ። ጥያቄያቸውን በንዴት



አወረዱት፣ በተቻለኝ ረጋ ብዬ መለስኩ። እንዲያ ተቸግሬ ሳለ ምናሴና ኃይለማርያም በነፍሴ ደርሰው አቶ አበበን በክርክር ተጋጠሙልኝ። በነሱ ቤት በክርክሩ ግልቢያ የነሱ ፈረስ አሸንፎላቸው ፈንጥዘው ሲያጨበጭቡ፣ አቶ አበበ ረታ መሸነፌን አላምንም ብለው እንቅፋት ሆነውባቸዋል። ስለዚህ ጩኸታቸውን በበለጠ ጩኸት፣ ቁጣቸውን በሳቅ ለመርታት ቆርጠው አቶ አበበን ተጋተሩልኝ። በተለይ ኃይለማሪያም ከበደ ጮሆ በማይገባው ነገር በመከራከር በተማሪ ቤትም የታወቀ አዋኪ ፍጡር ስለነበር አቶ አበበ ይህን አያውቁ ከሱ ጋር ተከራክሬ እሱን እረታለሁ ብለው ልባቸውን ሲያወልቁ፣ በተመልካች ዓይን አይቼ እሳቸው ሳያዩኝ ሹልክ ብዬ ወደ ቤት አመራሁ። ስሄድ በመንገድ ላይ ለሐገራችን ጥንታዊ ፊደል ሽንጤን ገትሬ ተከራክሬ ለዘለቄታው እንኳን ባይሆን ለጊዜው ጠላቶቼን አፋቸውን በማስያዜ በልቤ ሳልደሰትና በዚያ ሁሉ ሕዝብ መሀከል ዓይናፋርነቴን ገፎ እንደቡቴን የፈታልኝን አምላክ ተመስገን ሳልል አልቀረሁም።

በበነጋው ምሳ ተበልቶ አባቴ በዚያ በጎሽ ዋንጫቸው ጠላ ሲጎነጩ፣ ለኔም የምበላው እንዲቀርብልኝ አዘው ምሳዬን በልቼ ከጨረስኩ በኋላ ዋንጫቸውን አንስተው "ና፣ እንካ!" አሉኝ። እጅ ነስቼ ተቀበልኩና እቦታዬ ተመልሼ ተቀመጥኩ። ዋንጫቸውን አጋምሰው አባቴ ለሰው ሲሰጡ መቼም ምልክት ነው፣ ያ ሰው አንድ እሳቸውን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርቷል ማለት ነው። እኔም፣ ምን አርጌ ይሆን ይህ ክብር የደረሰኝ? እያልኩ ባሰላስልም ለጊዜው ምክንያት አልታየኝም ነበር። ምን አርጌ ነው? ብሎ መጠየቅ ድፍረት ይሆናል፣ ስለዚህ እሳቸው እስኪያመጡት ዝም ብዬ ከዋንጫው ፉት ፉት እያልኩ ጠበቅሁ።

"ሰማሁ፣ ተባረክ፣ ይባርክህ። እንዲህ ነው የለማ ልጅ ማለት፣ እንዲህ ነው። ለምሳ ከመንፈሳዊ ጉባኤ ስመጣ አንድ የማላውቀው ሰው እመንገድ ላይ አቁሞ 'ጎበዝ ልጅ ወልደዋል ዛሬ የሰራው ሥራ እንዲህ አይምሰልዎ' አለኝ። 'ምንድነው የሠራው? ብለው' ያባቶቻችንን የኢትዮጵያ ፊደል በፈረንጅ ይለወጥ የሚሉትን ተኩላዎች በክርክር ደህና አድርጎ ደብድቧቸዋል፣ ረቷቸዋል። እኛን ደስ እንዳለን እርስዎንም ደስ እንዲልዎ ይገባል' ብሎኝ ትከሻና ትከሻዬን ስሞኝ መንገዱን ቀጠለ። እርግጥ ይህን አርገሃል?" አሉ።
ሳልወድ በግድ እነ ምናሴ ኃይሌ እጄን ጎትተው አውጥተው ነው እክርክር ውስጥ ያገቡኝ፣ አልኳቸው።

"እንዲያ ነው! ሆኖም ለማ ቀድሞሃል" አሉ።

"በምኑ?" አልኳቸው።

"በዚሁ በፊደሉ ክርክር ነዋ! በዚያ ሰሞን ይኸው ነገር ለመንፈሳዊ ጉባኤ ሊቃውንቱ ይነጋገሩበት ተብሎ መርስኤ ሐዘን ራሱ አልመጣም እዚያው እኛው መሀከል ያሉ የሱ ቢጤዎች ናቸው ነገሩን የቀሰቀሱት፣ አንዱ 'ይለወጥ' ሲል አሥሩ 'አይለወጥም' ሲል፣ አንዱ 'ምን አለበት ቢለወጥ ይጠቅማል እንጂ አይጎዳ' ሲል፣ አሥራ አምስቱ 'እንዴት ተብሎ! እንዴት ታስቦ!' ሲሉ ድብልቅልቃቸው ወጥቶ ቀኑን ሙሉ ዋሉበት። ለማ አልተናገረም ዝም ብሎ እጃቸውን ያያል። ጠና-ጠና ያልነው አልተናገርንም። ሊቀ ሊቃውንት ቀጸላ 'ስምንተኛው ሺ ሲደርስ እንዴት ነው?' አሉኝ።ታዲያ ምናለ ክርክሩ ቀጠለ። መጨጫህ ሆነ፣ 'አንተ እንዲህ ነህ፣ አንተ እንዲህ፣ አንተ እንዲህ ነህ' መባባል መጣ። በኋላ ሊቀ ሥልጣናቱ ተከራካሪዎቹን አስታግሰው 'ከዚህ በፊት ያልተናገሩ ከሽማግሌዎቹ ይናገሩ፣ እነሱም ይሰሙ' አሉ። ለማ ተነሣ። 'እንግዲህ ይህ ታሪካችን፣ መጻሕፍት ቅዱሳታችን፣ የጻድቃን የሰማእታት ገድል የተጻፈበት ያባቶቻችን ፊደል አሮጌ ነው፣ ጊዜው አልፏል፣ አይረባንም፣ እሱን እንፈልገውም አይደለም? እሱ በቃን ሰለችን አይደለም? ይለወጥልን፣ በሱ ቦታ ሌላ ፊደል ይተካልን ካላችሁ ለማ የሚጣላችሁ አይደለም? እኔ ለማ ከክርክራችሁ አልገባም። እንዲያውም በርቱ ይቅናችሁ ነው የምል። ይመስገነውና ፈጣሪዬ ጤናውን ሰጥቶ ከዚህ እድሜ አድርሶኛል፣ ሸምግያለሁ፣ ያቅሜን ተምሬአለሁ። ከዚህ በኋላ ፊደል ልቁጠር ንባብና ጥፈት ልማር አልልም። ጊዜው አልፎአል። ይመስገነው ከጣልያን ዘረፋ የተረፉት በጥንቱ በአባቶቻችን ፊደል በብራና የተጻፉት መጣፎች ከቤቴ አሉ፣ እስከ ዕድሜዬ መጨረሻ እነሱን አነባለሁ፣ በዚህ እናንተን ሳላስቸግርም ራሴን ችያለሁ። ለኔ አታስቡ ብቻ ለናንተስ አታስቡም ወይ? ለሕዝቡስ? እንደሚባለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቆጥሮ ከክርስቲያኑ እስላሙ በቁጥር ይበልጣል፣ ይበዛል ይባላል። እስላም ደግሞ ለቁርዓኑ ሙት ነው፣ ቁርዓኑ ለተጻፈበት ለዓረቡ ቋንቋ ለዓረቡ ፊደል ቀናኢ ነው። ቋንቋውም ፊደሉም ነፍሱ ነው፣ ይወደዋል ሲበዛ። ዛዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስላሙም ክርስቲያኑም ካልለመደው ባይሆን ግሚሱ የወደደው አይሻልም? ሁለቱም ቢያዝኑ ምን ይረባል? ባይሆን እንዳቸው ይደሰቱ። ፊደላችን ዓረቢኛ ይሁን! 'ብዬ ተቀመጥኩ። ጉባኤው ብጥብጥ ብሎ ተበጠበጠ። 'አለቃ ለማ የስላም ፊደል ይሁን አሉ! አሉ?- አሉ!- 'ሆነ። 'የስላም ፊደል? አዎ የአረቡ የስላም ፊደል። 'መባባል ሆነ። ጉባኤው የጨረባ ተዝካር ሆነና በዚያው ተበታተነ" አሉ።

አባቴ የቀድሞው የግብፃዊ ሊቀ ጳጳሳችን የአቡነ ቄርሎስ ወዳጅ መሆናቸውንና በኋላ በርሳቸው ቦታ የኛው አበሻ ርእሰ ሊቀ ጳጳሳት መተካቱን በጥብቅ የተቃወሙ መሆናቸውን ሲናገሩ ሰምቻቸዋለሁ።



ፊደላችን ዓረቡ ይሁን ያሉት በዚህ ሳቢያ ይሆን ብዬ ምክንያቱን ጠየቅኋቸው።

"ሞኜ! ለማ ከግእዙ ፊደላችን ዓረቢውን ይመርጣል ብለህ ነው? የለም ለማ ለብልሀቱ ነው ዓረቡ ይሁን ያለ። ለማሸበሪያ ጉባኤውን ለማፍረስ ነው። እውነትም እንደ ተመኘሁት እንዳሰብኩት ሆነልኝ። ቀናኝ። 'የእስላም ፊደል! የስላም ፊደል? የስላም ፊደል?... 'እያለ ያ ባለቆብ፣ ባለ ካባና ባለ ጥምጥም ሁሉ ተደናግጦ ተበታተነ። ከዚያ ቀን ወዲያ በመንፈሳዊ ጉባኤ የፊደል መለወጥ ነገር አልተነሳም። ያ መርስኤ ኀዘንም ዝር አላለ። ዛሬስ በጉባኤው ነበር?" አሉ።

"ነበሩ፣ ተናገሩ ግን ሕዝቡ ሃሳባቸውን አልተቀበላቸውም። ከሳቸው በቀር የራስ እምሩንም፣ ያበበ ረታንም ሕዝቡ አልተቀበለውም። ለኔ ነው ያጨበጨበው!" አልኳቸውና እንደ ቀልድ አርጌ የሆነውን ሁሉ በዝርዝር አወጋኋቸው።

"ተመስገን ፈጣሪዬ፣ ተመስገን። ቸርነትህ ማለቂያ የለው።" አሉ ለመደምደሚያ።" ፊደላችን ሊተርፍልን ነው መሰል።"

ለዩኒቨርስቲ ትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር እንድሄድ ከመንግሥት መፈቀዱን /ከጃንሆይ መታዘዙን/ አባቴ በሰሙ ጊዜ አልተደሰቱም።" አይሆንም አትሄድም" እንዳይሉ፣ የራሳቸው የሃይማኖት አበው ትርጓሜ ሥራ ገና አላለቀም። ስለዚህ ሐዲስ ሊያስጀምሩኝ አልቻሉም። በዚያ ላይ የጃንሆይ ትዕዛዝ ነው ስለተባለ ለንጉሡ ፍቅር ሲሉ አልተቃወሙም። በዚያ ላይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴም በጣም በርትቼ ባንድ ዓመት ሶስት ክፍል ዘልዬ ባራተኛው ክፍል የተማርኩ ከመሆኔ ሌላ በዓመቱ የመጨረሻ ተርም ፈተናም አንደኛ በመውጣት የአምሀ አፀራን ሞኖፖል ሰብሬ ከንጉሡ እጅ ልዩ ሽልማት ተቀብዬ ተመስግኜባቸዋለሁ። በዚህ ሳቢያ በጊዜው የተነገረ ጨዋታ አለ። እቴጌ መነን የአባቴ ልዩ ወዳጅ ነበሩ፣ የመቄትም ተወላጅ ናቸው። እኔ በተሸለምኩ ጊዜ ከንጉሡ ጎን ነበሩ። ሰነባብተው አባቴ እጅ ሊነሡ ሲሄዱ እቴጌይቱ ሳቅ ብለው፣

"አለቃ ለማ፣ ያን ትንሹን ልጅዎን ምን ቢያቀምሱት ነው እንዲህ በትምህርቱ የበረታው?" ብለው ቢጠይቋቸው፣

"ቅኔይቱን አስቀርጥሜዋለሁ" አሏቸው ይባላል። ለአባቴ የኔ በፈተና ሁል ጊዜ አንደኛ መሆን ያስረዳቸው የኔን አእምሮ ብሩህነት ሳይሆን ከፍተኛ ግምት የሚሰጡትን የቅኔ ትምህርትን ታላቅና ጽኑ

መሠረትነት ነበር። ባገር ፊት፣ በንጉሡ ፊት ያስመሰከራቸውም ይኸው ነው። በዚህ አንጀታቸው ርሷል። ቢሆንም እንግሊዝ አገር መሄዴ በሌላ በኩል ቅር ያሰኛቸው፣ በሳቸው አስተያየት እንግሊዞች በጀግንነትና በጨዋነት ከጣሊያን ካቶሊኮች ቢበልጡም፣ በሃይማኖት፣ "ብሩስታንት" (ጸረ ማርያም) መሆናቸውን ያውቁ ነበርና፣ በመሀከላቸው በመዋል እኔም ወደነሱ እንዳልሳብባቸው በመሥጋታቸው ነበር። ለዚህ መድሃኒቱ ውዳሴ ማርያምን ጧት ጧት አዘውትሮ መድገም መሆኑን ደጋግመው ነግረውኝ። ያባቶቼን የለውጤ ኃይሉን፣ የለውጤ ገብረ መድኅንን፣ የወልደ መለኮትን፣ የአቡነ አሮንን ሃይማኖት እንድጠብቅ፣ ከመነሣቴ በፊት ደግመው ደጋግመው ነግረውኛል።

በአውሮፕላን ተሳፍሬ ወደ እንግሊዝ አገር መንገዴን የምጀምርበት ቀን እንደ ነገ ሊሆን እንደዛሬ አባቴንም እናቴንም ልሰናበታቸው ከኩተቤ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። ወደ አውሮፓ መሄዴን ራሴን እንደ መቻል፣ ጎጆ እንደመውጣት ስለነበረ ያየሁት የሌሎች ልጆች አባትና እናቶች እንደሚያደርጉት እነሱም አውሮፕላን ማረፊያ ባውቶሞቢል መጥተው እንዲሸኙኝ ደፍሬ ጠየቅኋቸው። አውቶሞቢሉን ከተማሪ ቤት ጓደኞቼና ዘመዶቼ እፈልጋለሁ አልኩ። እናቴ "እኔ አይሆንልኝም፣ እዚሁ እንሰናበት፣ እዚያ አውሮፕላን ማረፊያ ሄጄ ባውሮፕላን ተሳፍረህ አውሮፕላኑ እንደወፍ፣ እንደ አሞራ በሮ ሲጠፋ አይቼ፣ ተመልሰህ ትመጣለህ ብዬ ማመን አልችልም። ተሳፍረህ ስትሄድ ሳላይህ ወዲያው ባውሮፕላን እንግሊዝ አገር ሄደ ሲባል መስማቱ ይሻለኛል" ብላ አልሸኝህም አለች። አባቴ ላለመሸኘት የሰጡት ምክንያት ግን ከእናቴ ያውሮፕላን ፍርሃት ለየት ያለ ፍርሐት ነው። እሳቸው የፈሩት የመጨረሻ ልጃቸውን በስተርጅና ስለወለዱትና በብዙ ነገር እሳቸውን መስሎ የወጣ እየመሰላቸው በምሥጢር ከሁሉ አስበልጠው የሚወዱትን ልጃቸውን በሰው መሀከል ሲሸኙ፣ ከኒያ ምን ሰው ቢሞት እንባ ከማይወጣቸው ብረት በስተርጅና እንባ ካይናቸው ሲወጣ የታየ እንደሆን ብለው ራሳቸውን ከመፍራትና ከመጠርጠር ነበር። ስለዚህ እንደመሳቅ ብለው "እኔ ለማ፣ መንግሥቱ ለማን ስሸኝ አልገኝም" ብለው እምቢ አሉ። ወዲያው ተነስተው ቆሙ፣ እኔም ቆምኩ። "በስመ አብ" ብለው ጸሎተ ኃይማኖትን፣ ቀዳማሁ ቃለ ውእቱን፣ አ ፍጡነ ረድኤትን ባጭር ባጭሩ ከደገሙ በኋላ በጸሎተ እግዚአብሔርና ማርያም ደመደሙና፣ በደህና እንዲያደርሰኝ፣ በደህና እንዲመልሰኝ፣ ላገሬ እንዲያበቃኝ የተለመደውን ምርቃት ከመረረቁኝ በኋላ እኔም ጫማቸውን ስሜ ተቀመጡ።



"ተቀመጥ፣ "አሉኝ ተቀመጥኩ። "ወይዘሮ አበበች፣ ለመንግሥቱ ጠላ" አሉ። ወዲያው ትርፌ መጀመሪያ ለሳቸው በዋንጫ፣ ለኔ በድንጋይ ብርጭቆ ጠላ አቀረበችልኝ።

"በድሮ ጊዜ በሸዋ አማራና ጋላ መቼም እንደተጣላ እንደተፋጀ" ነው አሉ። አንድዬ አንዱ ወገን አንዱን ይወጋል፣ ይዘርፋል። ይማርካል፣ ይገድላል። ሌላ ጊዜ ያኛው አዘናግቶ ብድሩን ይመልሳል። እንዲህ ሲሉ ነበር ኑሮአቸው። አንድ ቀን አማራ ገና ይሁን ፋሲካ፣ ልደት ይሁን ስቅለት ወይ ትንሣኤ ብሎ ተዝናንቶ ሳለ ድንገት የጋላ ጦር ይመጣና ጨራርሶት፣ ፈጅቶት ይሄዳል። ያን ቀን በጋላ ሰፈር ሰው ባንድ አዳራሽ ተሰባስቦ ድግስ ሆኗል። 'ዛሬ ነው ድሌ' ይባላል፣ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ይሸለላል፣ ይፎከራል። በዚያን ቀን የገደለ ሁሉ ግዳይ ይጥላል፣ 'ይህን ገዳይ፣ ይህን ገዳይ' ይላል። 'የገደለ ወታደር ገዳይ! ገበሬ ገዳይ! መነኩሴ ገዳይ! ቄስ ገዳይ! ዲያቆን ገዳይ! ጎረምሳ ገዳይ! ጎልማሳ ገዳይ! አሮጌ ገዳይ! 'ይላል። ሣቅ ነው፣ ጨዋታ ነው። ታዲያ አንዱ አዝማሪ ገድሎ ኖሮ አይፎክር፣ አይሸልል ወይ አያቅራራ፣ እንዲያው ቁጭ ብሎ በትካዜ ጠላውን እየጠጣ ሌሎቹን ያስተውላል። መግደሉን ያወቀ፣ ያየው አንዱ ይመጣና 'ምነው አያ አከሌ? ምነው የማታቅራራ፣ የማትፎክር፣ የማትደነፋ? አንተም ገድለህ የለ?' ይለዋል። አዝማሪ ገዳዩ' ተወኝ እባክህ' ይለዋል። 'እኔ የምፎክርበት ቀን ገና አልመጣም፣ አዝማሪ ነው እንጂ መቸ ሰው ገደልኩ!' ብሎ መለሰ" አሉ።

ዝም ዝም ሆነ። እሳቸውም ታሪኩን፣ ጨዋታውን ብቻ ተናግረው አቆሙ እንጂ ታሪኩ የምን ምሳሌ እንደሆነ አልተናገሩም። እኔም እሳቸው በጨዋታ፣ በተረት መልክ የሚናገሩት ነገር እንዲያው በቁም ጨዋታ አለመሆኑ፣ ሲያገላብጡት አንድ ሚስጢር፣ አንድ አይነት ምክር፣ አንድ አይነት ትምህርት እንደሚሰጥ ደህና አድርጌ አውቅ ነበርና ባወጣው ባወርደው፣ ባገላብጠው ለትምህርት ውጭ አገር ለመሄድ ልሠናበት ከመጣሁበት ጉዳይ ጋር ያለው ግንኙነት አልታይ አለኝ። ስለዚህ እሳቸው ራሳቸው ይፍቱት፣ ይተርጉሙት ብዬ ተውኩላቸው እሳቸውም ሚስጥሩን እንዳልደረስኩበት እንዳላገኘሁት አውቀው፣ "ቋንቋ ብቻ መማር አይረባም። አፍ መፍቻ ነው ቋንቋ ብቻ" አሉ።

እንግሊዝ አገር ሄጄ በሎንዶን ከተማ ቆይቼ ወደ አገሬ የመመለስ ነገር ሳሰላስል በነበረበት ጊዜ "አገሬ" የተባለውን ግጥም ስጽፍ ትዝ ያለኝ ይህ ከላይ የጠቀስኩት የናትና ያባቴ ሁኔታ ነበር።

የዛሬ አሥር ዓመት ከአገሬ ስወጣ
ትምህርትን ስመገብ ዕውቀትን ስጠጣ
ፈረንጅ አገር ሄዶ ሥልጣኔ ሊያመጣ
እናቱ አልቻለችም ልትሸኘው ልትመጣ።
ሳይሆን ለምንግዴ ወይም ለስንፍና
እናት ምንም ብትሆን ያው እናት ናትና
አይለው አይደለ ጥሬ ድንቁርና።
አሻፈረኝ ብላ ሊጋባኸ አቅታ
ከቤቷ መቅረቷ.....

አባቴ ግን፣ በግጥሙ ውስጥ አለቃ ለማ ኃይሉ መሆናቸው ቀርቶ ፊታውራሪ ባልቻን ሆነው ነበር

መማርስ መሥራት ነው ታንኩን ከብረት
መማርስ መሥራት ነው መድፉን ከብረት
መማርስ መሥራት ነው አውሮፕላኑን
ብለውት ነበረ ሲሰናበቱት፣
ፊታውራሪ ባልቻ መራገፉ ተኳሹ
ኀበዝ ያልተባሉ በዚህ ጊዜ ሸሹ።
አፍ ብቻ መሆን ነው መማር ቋንቋ ብቻ
ብለው ነበርና ፊታውራሪ ባልቻ።
እሱም ብሎ ነበር" አሜን በአሜን"
ለይኩን፣ ለይኩን፣ - ፈቃድህ ይሁን
የዛሬ አሥር አመት ካገሩ ሲወጣ...



# ባህር ማዶ

## ሀ

ለንደን እንደገባሁ አገሩን፣ አየሩን፣ ሰውን፣ መኪናውን፣ ሞተሩን፣ ጭሱን ወዘተ... በጠቅላላ የፈረንጅን የሥልጣኔ ኑሮ ከነጓዙ፣ ከነኮተቱ፣ ከነግሣንግሡ መለማመድ ነበረብኝ። በተለይ ትምህርቱ ከዚያ ቀደም ባላየሁት ዓይነት በእንግሊዝ አፍ የሚነገር በመሆኑ መከታተሉ ብዙ የሚያደክም ስለነበረ ግጥም ለመጻፍ መንፈሴና ሐሳቤ አልተረጋጋም። ግን እየዋልኩ እያደርኩ ማናቸውንም መለማመዴ አልቀረምና በእንግሊዝ አገር ከሚማሩ ቀደም ብለው ከሄዱ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከወንዶቹም ከሴቶቹም ተዋወቅሁ። ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ገባሁ። በተርም መጨረሻ ዩኒቨርስቲ ሲዘጋ ማህበራችን ስብሰባ ያደርግና ወንዶቹም ሴቶቹም በምንሰበሰብበት አንዳንዴ አምባሳደሩን፣ አንዳንዴ እንደ ሲልቪያ ፓንክረስት ያሉትን ታዋቂ ሰዎች ይጋብዛል። የተርምስና ጊዜ ነው። የፈረንጁ ዓይነት፣ የአዲሱ ሥልጣኔ ዓይነት ፍቅር አየሩን አውዶታል፣ ሲኒማ ቤቱን ሞልቶታል፣ ዳንስ ቤቱን ሞልቶታል፣ ልብ ወለዱን፣ ኮሌጁን፣ ፓርኩን- አዳርሶታል-በያለበት ፍቅር ነው። ሮማንቲክ የሚባለው የወንድና የሴት፣ የወጣትና የወጣት፣ የጎልማሳና የልጃገረድ፣ ከዚያም አልፎ ይሄዳል። በዚህም በዚያም ያለው ፍቅር ነው!

እኔም ምንም እንኳ ባስተዳደጌ ካህን፣ በዝንባሌየ መንፈሳዊ ደብተራ መሳይ ብሆንም ከዚህ መሬቱንም፣ ሰማዩንም፣ ውሀውንም፣ አየሩንም ከሞላው ኃይል ነፃ ልሆን አልቻልኩምና ከተማሪዎች ማኅበር ስብሰባችን ባንዱ ካንዷ ኢትዮጵያዊት ተማሪ ጋር ተዋወቅሁ። የስልክ ቁጥራችንን ተለዋወጥን፣ ፈረንጆቹ ሲያደርጉ እንደምናየው አልፎ አልፎ አብረን መውጣት፣ ምሳ ወይ ራት አብረን መብላት፣ ሲኒማ መግባት፣ ቴአትር ማየት ወዘተ... ጀመርን። በግል ታሪኬ ፍቅር የሚይዘው ምእራፍ ረጅም ስለሚሆን፣ እዚህ ላይ ከሱ ዝርዝር መግባትን ለዋናው ለምጽፈው መጽሐፌ ትቼ ወደ ግጥም መጻፍ መነሾ ብተላለፍ ይሻላል። እና በየጊዜው ከወጣቷ ጋር ተያይዘን ሲኒማ አይተን ራት ከበላን በኋላ ፈረንጆቹ ሲያደርጉት እንዳየሁት ልጅቷን የምድር ውስጥ ባቡር ጣቢያ ድረስ በታክሲ ወስጄ መሸኘት ብቻ ሳይሆን እጅቤ እመኖሪያዋ ቤት ደጃፍ ድረስ አድርሼ፣ "ደህና እደር፣ ደህና እደሪ" ተባብለን፣ እንደገና ባቡር ተሳፍሬ ታክሲ ተከራይቼ እራሴ መኖሪያ ስደርስ፣ አንዳንዴ ስድስት ሰዓት፣ አንዳንዴ ሰባት ሰዓት፣ አንዳንዴም ስምንት ሰዓት፣ ከሌሊቱ ይሆን ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን የልብ ልብ በቅቶኝ ደፍሬ፣ በጓደኞቼ ምክርና ተግሳጽ ተገፋፍቼ፣ ስፈራ ስቸር፣ ሌሊት እመኖሪያዋ ሆስቴል ላይ አፏን ልስም ስሞክር ከእቅፌ አምልጣ በቁጣና በመዓት በሩን እፊቴ ላይ አናግታ ዘጋችብኝ። ስለደረሰብኝ አደጋ ለጓደኞቼ የልቤን አወጋኋቸው። እነርሱም በተቻላቸው አጽናኑኝ። ልጅቱ ገና ያልሰለጠነች፣ ከጫካ ከወጣች ሳምንት ያልሞላት አውሬ ብትሆን ነው። በእንግሊዝ ደንብ ልሳምሽ ስትባል አሻፈረኝ ብላ በሩን መዝጋቷ። እኔም እርግጥ ይኸው ቢሆን ነው በሽታዋ ብዬ በሙሉ ልቤ ተስማማሁ። ግን ወሬ አንዴ ከተተነፈሰ፣ ከመቅጽበት ለተማሪው ሁሉ መዳረሱ የማይቀር ከመሆኑ ሌላ ተመልሶ ወደኔ ሲመጣ መልኩን ለውጦ" መንግቱ ለማ፣ ያ ቄስ ደብተራ ሜሪ ታደሰን ካልሳምኩና ሌላም ነገር ካልፈጸምኩ ብሎ፣ ኀበዟ በጥፊ ጆሮ ግንዱን ብላ አባረረችው" የሚል ሆኖ ደረሰኝ። እኔም የተማሪ መሳቂያ መሳለቂያ ሆንኩ። ይባስ ብሎ አንዱ ኤምባሲ እየሠራ በትርፍ ጊዜው የሚማር ተማሪ ዝናዬ ከኤምባሲው ሠራተኞች አልፎ ከክቡር አምባሳደሩ ጆሮ ሳይደርስ እንዳልቀረ ነገረኝ። "ለካ እንዲያ ያለ ሮማንቲክ ኖሯል፣ ቄስ መስሎ ሳይታወቅበት" አለች የአምባሳደሩ ልጅ አለኝ ። ይህ ወሬ በጣም ነው ያስደነገጠኝ። ያምባሳደሩ ልጅ እንዲያ ካለች አምባሳደሩም ሰምተዋል ማለት ነው። እሳቸው ከሰሙ ደሞ ትምህርት ሚኒስቴር ሰማ ማለት ነው። እኔም ምንም እንኳ በየጊዜው በሚደርስብኝ በደል ሆነ አደጋ ወይም ሌላ መጥፎ አጋጣሚ የመቀለድና በራሴም የመሳቅን ታላቅ ስጦታ ስለሰጠኝ እግዚአብሔርን በየጊዜው የማመሰግን ብሆንም፣ መንፈሳዊ ደብተራ ነኝ የምለው ሰው በሮማንቲክ ፍቅር ማቢያ አንዷ ሐበሻ በጥፊ አጮለችው መባሉን፣ ምንም እንኳን ያልሆነ ልብ ወለድ ታሪክ ቢሆንም፣ አሥር ጊዜ በሲኒማ ያየሁት የፈረንጅ ፍቅረኞች ባህል ቢሆንም ቅሉ በአበሻነቴ በጣም የሚያሳፍርና የሚያናድድ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ስለዚህ ብድሬን በምን አኳኋን እንደምመልስላት ሌት ተቀን እሰላስል ጀመር። ውሸት ነው፣ የጠላት ወሬ ነው፣ የምቀኛ ወሬ ነው፣ ልጅቷ ራሷ እሱ ቀድሞ ያወራብኛል ብላ የፈጠረችው ተረት ነው ብል፣ እንዴት አንድ ኢትዮጵያዊ ቢማር፣ ምን ቢመራመርና ምን ቢሰለጥን ሴት በጥፊ ስታጮለው እንደ ፈረንጅ ጉንጬን አሻሽቶ "ይቅርታ!" ብሎ ይሄዳል? መልሶ ያጠናፍራታል እንጂ! ብል፣ የሰሙኝ ሁሉ ወንዶችም ሴቶቹም በውስጥ ዓዋቂ ሳቅ ያዘኑልኝ ፈገግ እያሉ ያሳዘኑልኝ እየተንከተከቱ፣ "የምትለው ሁሉ እውነት ነው! እንዴት ተደርጎ!" ይሉኝ ነበር። መሳቃቸው መንከትከታቸው ግን አልቀረም። አንዳንዶቹማ በተለይ የመኳንንቱ ልጆች እነ እንዳልካቸው ገና በሩቅ ሲያዩኝ ነበር በሳቅ የሚፈነዱት።



ውሸት ነው ብሎ ማስተባበሉ፤ ሊሆን የማይችልበትን ማስረጃ መደርደሩ መሳቂያነቴን አባባሰው እንጂ ለምንም አልጠቀመ። ስለዚህ ታክቲኬን ለወጥሁና ያዘኑልኝ መስለው በርህራሄ ወይም በቀጥታ ተንኮለኛነት ነገሩን ለሚያነሱብኝ ሁሉ እንድቀድሞው መካዴን ትቼ" እርግጥ ነው በጥፊ ተመትቻለሁ" ብዬ አምንላቸው ጀመር። ካመንኩ፣ ከተረታሁኝ፣ ዕውነት ነው ካልኩኝ እነሱም የሚከራከሩበት በማጣታቸው በምን መንገድ እንደሚያናድዱኝ መላ ሲፈልጉ መሳቃቸውና መሳለቃቸው ቀስ በቀስ እየተቀነሰ ሄደ። እኔም ይህን ተመልክቼ ተጽናናሁ፣ አልፌ ተደፋፈርኩ። ራሴን በኩራት ቀና አድርጌ መሄድ ጀመርኩ፣ ግን ደረት ከመገልበጥ ገና አልደረስኩም ነበር። ደረቴን በኩራት የገለበጥኩት በትምህርት ዓመት መጨረሻ የማኅበራችን አጠቃላይ ስብሰባ ሆኖ፣ ማህበሩ አንዱን ለእረፍት የተዘጋ የሴት ልጆች ኮሌጅ ለሳምንት ተከራይቶ፣ እዚያ ወንዶችም ሴቶችም ተከማችተን፣ ለምሳ ግብዣ ክቡር አምባሳደሩን አቶ አበበ ረታን በክብር እንግዳነት ጋብዘን ንግግር ባደረጉልን ጊዜ ነበር። ምሳ ከተበላ በኋላ ከጠረጴዛው ገበታ ላይ እንዳለን የማህበራችን ፕሬዚዳንት ንግግር አሰማ። ክቡር አምባሳደሩ ግብዣችንን አክብረው በመሀከላችን ስለተገኙ ወዘተ... ለግርማዊ አባታችን ያለንን የልጅ ፍቅርና ታማኝነት ወዘተ... እናት አገራችንን ለማገልገል ያለንን ምኞትና ወዘተ ከዘረዘረ በኋላ ክቡር አምባሳደሩ አባታዊ ምክር የተሞላበት ንግግራቸውን እንዲያሰሙ በታላቅ ትህትና ጠየቀ። ክቡር አምባሳደሩም በዚያ በታወቀው ቁጭን የደብተራ ድምጻቸው ስለ ነፃነት፣ አገርን ስለመውደድ፣ ንጉሠ ነገስትን ስለማፍቀር፣ የሐገርን ታሪክና ባህል ስላለመልቀቅ፣ በባእድ አስተሳሰብና ፍልስፍና ስላለመበከል፤ ወዘተ ወዘተ... ወዘተ... ከመርዘም አልፎ ወደ መንዛዛት ያዘነበለ ዲስኩር ደሰኮሩልን። ዲስኩራቸው ሲያስቀን በደስታ አጨበጨብንላቸው፤ እሳቸውም በአባታዊ ፈገግታ ነበር የጭብጨባችንን ነዶ፣ በረከታችንን መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ የተቀበሉት። የሚቀጥለው ፕሮግራም የግጥም ንባብ እንደሚሆን፣ ግጥሙንም የሚያሰማው መንግቱ ለማ እንደሚሆን ከፕሬዚዳንቱና ከኔ ከራሴ በቀር አስቀድሞ ያወቀ አልነበረም። ከክቡር አምባሳደሩ አበበ ረታ ንግግር ቀጥሎ እኔ ግጥም እንዳነብ እንዲፈቀድልኝ ፕሬዚዳንቱን የጠየቅሁት ራሴው ነኝ ግን አላስነበበኩትም። ይህን ያደረግነው፣ ተማሪው ቀጥሎ የሚመጣለት ምን እንደሆን ባለማወቁ፣ ዘፈን ወይም እስክስታ ይሆን? አጭር ልብ ወለድ ተረት ይሆን? እያለ እንዲታመስና፣ ሰዓቱ ሲደርስ ያላሰበውን ግጥም ስናሰማው መደሰትን ከመገረም የቀላቀለ ስሜት እንዲሰማው፣ ልክ እንግሊዞቹ እንደሚሉት "ፕሌዛንት ሠርፕራይዝ" አስደሳች ድንጋጤ እንዲሆንለት በቴአትር ጥበብ የተደገፈ ብልሃታችን ነበር።

ከዚያ በፊት በስብሰባችን የግጥም ንባብ ተሰምቶ ስለማያውቅ በዛሬው ስብሰባ ግጥም ይኖራል ብሎ ያሰበ ተማሪ አልነበረም።

ለአምባሳደሩ ዲስኩር የተሰጠው ጭብጨባ ሲያከትም አምባሳደሩ ተመልሰው ከተቀመጡ በኋላ፣ የሚቀጥለው ፕሮግራም የግጥም ንባብ መሆኑንና አንባቢውም የታወቀው ደብተራችን መንግስቱ ለማ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አስታወቀ። ቀጥሎም በሁለት እጆቹ በፈረንጅ ደንብ ወደኔ አመልክቶ እንድነሳና እንድናገር ጋበዘኝ። ስነሳ ምድረ ተማሪ ጭብጨባውን አቀለጠው። እኔም በኮቴቤ የሃይማኖት ሰባኪ በነበርኩበት ጊዜ የሠለጠንኩበትን አነጋገርና የግጥም አነባብ ዘዬ ብቅ አደረግሁትና "ዛሬ በዚች በተቀደሰችዋ ቀን" በማለት ጀምሬ በዚያ የምግብ አዳራሽ ለተሰበሰቡት ክቡራንና ክቡራት የማነበው የፍቅር ግጥም መሆኑን በቁም ነገር አስታወቅሁ። ተሜ ሆዬ በፍቅር ምክንያት "እቴ ባንቺ ሰበብ ባንቺ የተነሳ፣ ዲቁናውም ቀረ ዳዊቱም ተረሳ" የሚለው የጥንቱ ባህላዊ ግጥም ትንቢት በመንግስቱ ለማ ተፈፀመ ብሎ የሚያምን ስለነበረ፣ በሳቅ ይንከተከትና አንዳንዱም ይንፈራፈር ጀመር። ሳቁም ጭብጨባውም ብዙ ጊዜ ቆየ። ወዲያው ግን ክቡር አምባሳደሩ ባሉበት እንዲህ መዝናናት የክቡርነታቸውን ክብር ከመድፈር ሊቆጠር እንደሚችል፣ የክቡርነታቸውን አለመሳቅና አለማጨብጨብ፣ እንዲያውም የግምባራቸውን መቋጠር በማየታቸው ባለፈንጠዝያዎቹ ደነገጡና ጫጫታቸውን አቋረጡ። በዚያ ፈንታ ዝምታና ፀጥታ ተተካ። ይህን ጊዜ እኔ "ዛሬ በዚች በተቀደሰችዋ ቀን የማነበው አጭር የፍቅር ግጥም ነው" አልኩና፣ "ግጥሚ በዚሁ ሰሞን አዲስ የተደረሰች ናት አርእስቷ 'በጠራ ጨረቃ' ነው" ስል ጭብጨባው አገረሸና በክቡር አምባሳደሩ ዝምታ ምክንያት ወዲያውኑ በረደ። "በጠራ ጨረቃ" አልኩና ጀመርኩ፣

> በጠራ ጨረቃ በእኩለ ሌሊት፣
> ዓይኖቿ እያበሩ እንደ ከዋክብት፣
> "ሳማት! ሳማት!" አሉት፣
> "እቀፍ! እቀፋት!። "
> አላወላወለም ወጣቱ ታዘዘ፣
> ወገቧን አንገቷን፣ እጇን በእጁ ያዘ።
> ምንም እንኳ ጡቷ እንደሾህ ቢዋጋ፣
> ጣቷ በመሆኑ የጉማሬ አለንጋ
> ጆሮ ግንዱን ሰማው በጥፊ ሲናጋ።

እዚህ ላይ ምድረ ተሜ በሳቅ ሆዱን እስኪያመው ተንከተከተ።

> ዋ ጀማሪ መሆን ! ዋ ተማሪነት፣
> ዋ ትዕዛዝ መፈፀም ዋ ምክር መስማት!
> በጠራ ጨረቃ በኩለ ሌሊት።



ተሜ ጭብጨባውን ለቀቀው፤ "ብራቮ! ብራቮ መንግስቱ ለማ!" እስ፤ መንግስቱ ለማም እጅ ነስቶ ከተቀመጠ በኋላ ሁለት ጊዜ ያህል እየቆመ ደጋግሞ እጅ በመንሳት የጭብጨባውን በረከት ተቀበለ። ክቡርነታቸው ሳይቀሩ አጨብጭበዋል። ግን የሳቸው ዝግ ያለ ከመሆኑ በላይ ድምጹ የማይሰማ ጭብጨባ ነበር። ምናለ ከዚያ በኋላ የተማሪው ሁሉ ሳቅና ስላቅ ወደ ትግርምት ወደ አድናቆት፣ ባንድ አፍታ ተለወጠ። በመካያው ዓይን ያወጣ አፍቅሮትና አክብሮት ሆነ። እኔም ከልቤ "ዛሬ ነው ድሌ!" ብዬ ጨፈርኩ። መሳቂያ መሳለቂያነቱ ከኔ ተገፎ ተነስቶ በዚያች "በጥፊ ባጮለችኝ" ቆንጆ ላይ እንደማይለቅ የሙጫ ጭቃ ተለጠፈ። ቆንጂቷ በምሳው ላይ እጓደኞቿ መሃከል ተቀምጣ በልብሷ ሆነ በወሬና በጨዋታ እንደ አጥቢያ ኮከብ ተንፀባርቃ ስለነበረ፤ የተማሪው ዓይን ሁሉ ሲያርፍባት ጊዜ በድንገት ከድል አድራጊነት ተራራ ወደ ዓይን አፋርነት ኮረብታና ከዚያም ወደ እፍረትና ሐፍረት ሸለቆ ስታዝቀዝቅ፣ እዚያው በዚያው ዓይን ባይን ታየችኝ። እኔም ነገሩ ሁሉ ተዘዋውሮ መሳቅያና መሳለቂያዋ እሷ በመሆኗ አንጀቴ ነበር የራሰው።

ክቡር አምባሳደሩ ግን ያ ሁሉ ሰው ሲስቅ እሳቸው ፍንክችም አላሉ፣ ሳቅ የሚሉት አልዞረባቸውም። እመኪናቸው ድረስ ልንሸኝ አጅበን ተከተልናቸው። ከግብር ቤቱ ሲወጡ ሳለ ቆም አሉና እኔን ጠሩኝ። ጠጋ ስል "አንተ መንግስቱ ለማ የምትባለው የኮተቤ ተማሪ የነበርከው አይደለህም?" አሉ። "ነኝ" አልኳቸው" አዎ፣ የሰው ፊት አልረሳም፣ አስታውሳለሁ። ያን ጊዜ ፊደል ይሻሻላል ብለን ስንከራከር ሳለ ሳይገባህ ነው ያስቸገርከው። ኤምባሲ ናና ከዚያ እንከራከርና አስረዳሃለሁ" አሉኝ። እጅ ነሳሁ። በዚያ በታላቁ ጉባኤ ላይ ክርክሩ ተጧጡፎ ሳለ ሳይታሰብ ከክርክሩ ጥልቅ ብዬ ገብቼ ሐሳባቸውን ውድቅ በማድረጌ ቂም ሳይዙብኝ ሊያስጠጉኝ፣ ሊያስተምሩኝ፣ ሊያስረዱኝ ክቡር ፈቃዳቸው መሆኑ እንድወዳቸው አደረገኝ። እሳቸው ግን "በጠራ ጨረቃ"ን አልወደዱልኝም። "ያሰማኸው ግጥም ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚሰጥ አልገባኝም" ብለውኝ ከዘነጠ መኪናቸው ገብተው ወደ ሎንደናቸው ተመለሱ። ለኔ ግን በዚህ የፍቅር ጥፊ ሳቢያ ከደረሰብኝ ሁሉ የተማርኩት አንድ ትምህርት ነበረ፣ ያም ትምህርት በሐሰት ስምን ለሚያጠፉ፣ መሳቂያ መሳለቂያ ለሚያረግና ለሚያናድድ ተንኮለኛ ሁሉ መድኃኒቱ እውነቱን ይዞ ነጋ ጠባ መጋተር ሳይሆን፤ ሐሰት መሆኑን እያወቁ" አዎ እርግጥ ነው፣ እውነት ነው" ብሎ በማመንና መስማማት፣ ከሱ ጋር አብሮ በራስ መሳቅ መፍለቅለቅ ነበር። ችግሩ ሁላችንም በሌላ ሰው መሳቅን ስንወድ፣ በገዛ ራሳችን የመሳቅ ስጦታና ችሎታ ያለን ግን በጣም ጥቂቶች መሆናችን ነው። እኔ በዚህ ረገድ ከተፈጥሮ የታደልኩ መሆኔ ገና ከልጅነቴ ጀምሮ

ቢሰማኝም በጉልህ ዋጋው የታወቀኝና ስለዚህም ስጦታ እግዚአብሔርን ያመሰገንኩት "በጠራ ጨረቃ"ን በፃፍኩበት ጊዜ ነበር። ይኸው ስጦታ፣ በእንግሊዝኛ" ሴንስ ኦቭ ሀዩመር" የሚባለው የሕይወትን አስቂኝ ገጽታ ለማየትና ለማሳየት የሚያስለችው ስጦታ ይበልጡኑ ያገለገለኝ በኃይለኛ በሽታ ታምሜ አንድ ጥቁር ሐበሻ በሃምሳ ነጭ በሽተኛ መሀከል፣ በአንድ በተንጣለለ የእንግሊዝ ሆስፒታል ክፍል ከለንደን ከተማ ውጪ፣ ወዳጅ ጓደኛ በሌለበት፣ ባንዲት "እስኮት" በምትባል በፈረስ እሽቅድምድም መጋለቢያነቷ በታወቀች የገጠር ከተማ በተገኘሁ ጊዜ ነበር።

ነገሩ የመጀረው ገና ከለንደን ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ገብቼ እንደተኛሁ ነበር። ሲስተሯ በፍፁም ከአልጋ እንዳልነሳ ታስጠነቅቀኝና ለሽንትና ለሰገራ እንኳን ብነሳና ብሄድ በኃይል ትገስፀኝ ነበር። የተኛሁት እዚያ" ጀኔራል ዎርድ" ከሚባለው በኛ አገር ሶስተኛ ክፍል ከሚባለው የመደዴ ደረጃ ነበር። የሲስተሯ ሁኔታ ያስደነቀኝ ለኔው ጤንነት፣ ለኔው ደህና መሆን ከማሰቧ የተነሳ እንዲያ ኃይለኛ ዲክቴተር ሆና መገኘቷ ነው። ስልጣኔ ለምን ተደፈረ ነው። ሁላችንንም በጣም ያረጀውን በሽተኛ ጭምር እንደ ሕፃን ልጅ ነበር የምታየን። የማዕረግ ስሟ "ሚሲስ" /ወይዘሪት/ መሆኑን "ሚስዝ" /ወይዘሮ/ አለመሆኗን ተመልክቼ እኔንም ከሌሎቹ ይበልጥ ጡጦ እንደሚጠባ ሕፃን ልጅ ያየችኝ ባል ያላገባች፣ ልጅ ያልወለደች ግን ከእድሜዋ ገፋ ያለች በመሆኗ ሳይሆን አይቀርም ብዬ ገመትኩኝ። ወዲያው ግን ኦፐራሲዬን ሆንኩና ከወገቤ አከርካሬ ስር፣ ከበጀዴ ጀርባ፣ "ባርኩሉሲል" የተባለውን ያጥንቴን ክፍል ፍቀው ካወጡልኝ በኋላ እንኳንስ ከአልጋ ልነሳ፣ በአልጋዬ ላይ እንኳን እንድገላበጥ አልፈቀደችልኝም ነበር። አሁን ግን እኔም ብሆን ከልካይነቷን ያስፈልጋል ብዬ ተቀብየዋለሁ። ቆይቶ አጠገቤ በስተግራዬ ተኝቶ የነበረው ሽምግል ያለ በሽተኛ እንደ ትናንት ሆስፒታል ገብቶ አስፈላጊው ምርመራና መድኃኒት ተደርጎለት እንደ ዛሬ፣ ብድግ ብሎ ወደ ሽንት ቤት ሄዶ ሲመለስ፣ እንደማንከስ፣ እንደ መንገዳገድ እያለ መጣና በጭንቅ አልጋው ላይ ተኝቶ ይንፈራፈር ጀመር። እኔም ሁኔታው የጤና ስላልመሰለኝ የራስጌዬን መጥሪያ ደወል ደጋግሜ ደውዬ ተረኛዋን ነርስ ጠራኋት።

"አሁን ደሞ ምን ይጠበስ ነው?!" አለችኝ ቁጣና ቀልድ ደባልቃ። የሰውየውን ሁኔታ ስታይ ግን፣ ቀልዷን ተወችና "ዶክተሩን ልጥራ" ብላ ወደ ቢሮዋ ሮጠች። ሐኪሙን በውስጥ ስልክ በድንገተኛ አደጋ ደረጃ ጠርታ ስትመለስ ሽማግሌው መንፈራፈሩንና መፈራገጡን አቁሞ ነበር። እኔ የውጋቱ ህመም አልፎለት እንቅልፍ የወሰደው ነበር



የመሰለኝ፣ ለካ ሞቷል። እዚያው አጠገቤ እያየሁት ሁለት ሜትር በማይሞላ ርቀት ተኝቶ እዚያው በዝያው ሞቷል። የሚገርመው የኔ አለመደንገጥ ነው። አጠገቤ ሰው ሲሞት ሳይ ያ በሕይወቴ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ነው። ነርሷ ግን ወዲያው ሌላ ነርሶች ጠራችና የሟቹን አልጋ ዙሪያውን በተሽከርካሪ መጋረጃ አጠረች። ሃኪሙ ጥቂት ቆይቶ ማዳመጫውን አንገቱ ላይ እንዳንጠለጠለ መጣና ለነርሶቹ ትዕዛዙን ሰጥቶ ሳይቆይ ተመልሶ ሄደ፣ ነርሶቹም እመጋረጃው አጥር ውስጥ ሆነው የሟቹን ልብስ ሲያወላልቁና ሬሳውን ሲያሰነዳዱ እንደ ሲካካ ዶሮ ያስካኩ ነበር። ይህ ነው እኔን ያስገረመኝ።

"ትናንት ማታ የት አመሸሽ?"

"ከቦይፍሬንዴ ጋር ሲኒማ ገባን፣ አንቺስ?"

"እኔ ቴአትር ነው ያየሁት ከማይክል ጋራ"

"እኔ የትም አልሄድኩም፣ ድክም ብሎ ደክሞኝ አቤት ከእማማ ጋር ስናወጋ አመሸን።"

"እኔ ዳንስ ቤት ሄጄ ነበር፣ ብቻዬን። ቡጊውን አቀለጥነው። አደርንበት፣ አነጋንበት!

የሞተ ሰውስ ሞተ። ሬሳ በእጃቸው ላይ እያለ እንዲህ ያለውን ጨዋታ ሲጫወቱ፣ ሲያስካኩ፣ ሲስቁ ሰምቼ ምርር ብዬ ነው የታዘብኳቸው። እነሱ ግን እኔንም ሌሎቹንም በሽተኞች ከጉዳይ ሳይጥፉ የሰውየውን ሬሳ በተሽከርካሪ ያስከሬን አልጋ ላይ ነጭ አንሶላ መሳይ አልብሰው እየገፉ ከክፍላችን ወጡ። አንዷ ልብሱን ይዛለች አንዷ ጫማውን አንጠልጥላለች። ሰውየው መሞቱ ከታወቀ ጀምሮ ነርሶቹ እስኪወጡ ድረስ በክፍላችን ፀጥታ ነግሶ ነበር። ጮኽ ብለው የሚጫወቱት ሕመምተኞች እንኳን ያን ሰዓት በሹክሹክታ ነበር በዝግታ የሚነጋገሩት። እኔን ያሳዘነኝ የሰውዬው ሞት አልነበረም-ሽምግል ያለ ነው። ትናንትቱን በአምቡላንስ ሲመጣም በድንገተኛ ውጋት ልቡ ተዳክሞ መሆኑንና ሕመሙም የቆየ መሆኑን፣ በእንዲህ ያለው ሕመም ሞት እንደ ሰራቂ በድንገት ሳይታሰብ የሚወስድ መሆኑን ተረድቻለሁ። ያሳዘነኝ የነርሶቹ ሳቅና ጨዋታ ነው። ምን ልበ ቢሶች ምን ግዴለሾች ምንኛ አዘንየለሽ ቢሆኑ ነው የሙት ሰው ሬሳ እያገላበጡ የሚሳሳቁት?! ይህ ነበር አልዋጥልህ ያለኝ። ከነርሶቹ መካከል በተለይ የኔ ንጽሕት ወዳጅ የሆነች አንዲት ነርስ ነበረች፤ እሷም አልቀረች ስትስቅ።

በበነጋው ተረኛ ሆና "ጉድ ሞርኒንግ ሚስተር ለማ!" ስትለኝ አኩርፌ አልመለስኩላትም። እኔን አልፋ ሌሎቹን "ጉድ ሞርኒንግ" እያለች ሁሉንም ቀንቻቸው። እነሱ ግን በፈገግታና በደስታ አልፈውን ጉድ ሞርኒንግ" እያሉ መለሱላት። እኔ ግን እንዳኮረፍኩ ሰነበትኩ።

ከሌሎቹ እስቃለሁ እጫወታለሁ፣ እሷን ግን አላናግርም፣ ብታናግረኝም አልመልስም። አንድ ቀን ያኮረፍኩበትን ምክንያት ጠየቀችኝ። የሐዘኔና የኩርፊያዬ መነሻ የዚያ የሽማግሌ ሞት መሆኑን ከልብ በመነጨ ስሜት በዝርዝር ገለጽኩላት። የታዘብኩትን ገልጬ ሳበቃ፣ በሰራችው ስራ አፍራና ተጸጽታ እኔን ስላሳዘነችኝ ማዘኗን ታሰማኛለች ብዬ ስጠብቅ ከት ብላ ሳቀች።

"ለዚህ ነው ያኮረፍከው እንዴ ሞኜ!? " ብላ ተራዋን በኔ ሁኔታ በመገረም እያረፈች ተንከትክታ ሳቀች። ሳቁ ጋብ ሲልላት "ስማኝ፣ አንተ ከተፈጠርክ ሰው ሲሞት ያየኸው ገና አሁን ነው አይደለም?"

"አዎን፣ " አልኩ።

"እኛ ነርሶች ግን ነጋ ጠባ፣ በቀን፣ በሌሊት፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ፣ ሙያችንን የምንማረውም በሞተ ሰው ሬሳ ነው። ሰው ሁሉ በሆስፒታል በሞተ ቁጥር ብናዝንና ብናለቅስ ኖሮ ሐዘኑ ብቻ እኛኑ ይገድለን ነበር። ስለዚህ ሰው በእጃችን ላይ ሲሞት ሆን ብለን እንስቃለን፣ እንቃለዳለን፤ አለበለዚያ ማበዳችን ነው። ገባህ፣ አንተ ደንቆሮ ጥቁር ኢትዮጵያዊ?!" አለችኝ። በዚያ በቀልድ አነጋገሯ። "ደሞ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆነህ፣ ያውም የለንደን እስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ፣ ይህን አለማወቅህ ይገርማል!" ብላ ካጠገቤ ተነስታ ወደ ስራዋ ሄደች። እኔም ነገሯ ከልቤ ገባና፣ ሞት የሕይወት ጎረቤት መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ በዓይኔ ልቡና ተመልክቼ ኩርፊያውን በመተው ጧት ጧት "ጎድ ሞርኒንግ ሚስተር ለማ!" ስትለኝ መልሼ "ጉድ ሞርኒንግ" እላት ጀመር። በለንደን ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እየታከምኩ አንድ ወር ያህል ከተኛሁ በኋላ ነው ወደ "እስኮት ኦርቶፔዲክ የአጥንት በሽታ ሆስፒታል" በሆስፒታሉ አምቡላንስ የወሰዱኝ።

እዚያ እንደደረስኩ አምባሣደራችን ወጪውን እከፍላለሁ ስላለ በአንደኛ ማዕረግ ለብቻዬ አንድ ክፍል ተሰጥቶኝ ተኛሁ። ግን ወዲያውኑ ሳምንት እንኳን ሳይሞላኝ በአንድ ክፍል ብቸኛነቱ ስለሰለቸኝ የሆስፒታሉ የነርሶች ጠቅላይ አለቃ ሲስተሩዋን አስከትላ እየዞረች በሽተኛ ስትጎበኝ ከአንደኛ ማዕረግ ክብር ወርጄ ሶስተኛ ማዕረግ "ጀኔራል ዎርድ" አዳራሽ ውስጥ ከሌሎች ተራ ሕዝብ በሽተኞች እንድቀላቀል አመለከትኩ። ይህን ጥያቄ ማቅረቤ አስገርሟት ምክንያቱን ብትጠይቀኝ፣ "ብቸኛነቱ እስረኛነት ነው የሆነብኝ፤ እንዳገሬ እንደዘጋ ባሕታዊ ነው የሆንኩት። የሚጠይቀኝ ዘመድ የሌለኝ የሰው አገር ሰው፣ የሚያነጋግረኝና ቀንና ሌሊት የሚያጫውተኝ



ራዲዮው ነው፣ መጽሐፍት ናቸው፣ እነሱም ሰለቹኝ "አልኳት። "የአንደኛ ደረጃ ክብር ካልወደደለት ይሂድ፣ ከሠራተኛው መደብ ይደባለቅ "ብላ በፈገግታ ትዕዛዟን ሰጠች። ወዲያው በተሽከርካሪ ቀጭን አልጋ ላይ አጋደሙና እየገፉ ከአንደኛ ወደ ሶስተኛ ክፍል ወስደው አስተኙኝ።

የዚህ ሆስፒታል ሶስተኛ ማዕረግ እስከዚያ ግዜ ካየሁት ሁሉ ይበልጥ የተንጣለለ፣ ባገራችን አንድ ራስ ግብር የሚያበሉበትን አዳራሽ የሚያህል ሰፊ አዳራሽ ክፍል ነበር። በክፍሉ መሀከል ወደ ውጪና ወደ ሌሎቹ ክፍሎች የሚወስድ መተላለፊያ አለ። ከመተላለፊያው ግራና ቀኝ ባንድ ወገን ሃምሳ አልጋ፣ ባንድ ወገን ሃምሳ አልጋ ሙሉውን የአጥንት ደዌ ያደረበት በሽተኛ ተኝቷል። አንዳንዱ እንኳንስ ከአልጋው ሊነሣ፣ ቀና ብሎ እዚያው ለመቀመጥም የማይፈቀድለት ነው። አንዳንዱ አልጋው ላይ ቁጭ ለማለትና ወደ ሠገራ ቤት በእግሩ ለመሄድ የተፈቀደለት ነው። እኔ በፍጹም ካልጋቸው ከማይወርዱትና ቀና እንኳን ብለው እንዲቀመጡ ካልተፈቀደላቸው መሀከል ነበርኩ። በተጨማሪም ከመላው በሽተኛ መሀከል ጥቁር እኔ ብቻ ነበርኩ።

የሠራተኛው መደብና የተራው ሕዝብ ወገኖች የሆኑት የእንግሊዝ ሕመምተኞች በጠቅላላው ሰው ወዳድና ተጫዋቾች ሆነው ስላገኘኋቸው ከዚያ ከአንደኛ ማዕረግ እስር ቤት ወጥቼ ከነሱ በመደባለቄ ደስ አለኝ። ያንዳንዶቹ ተጫዋችነት ግን በሌላም በሽተኛ መቀለድና ማላገጥን ስለሚጨምር ለኔ ለጥቁር ኢትዮጵያዊ አንጉል ፈተና ሆኖብኝ ነበር። ፈተናው ሲጀምረኝ እንደዚህ አርጎ ነበር። የአጥንት በሽታ ሊያዘው የፀሐይ ብርሃን ይበጃል፣ አጥንት ያለመልማል ይላሉ። ከተንጣለለው አዳራሽ ቦታዬን ይገፔ ሁለት ይሁን ሶስት ቀን እንደተኛሁ ከምሳ በኋላ ጣይ እንዲመታን ከነአልጋችን እየተገፋን እውጭ ተሰጥተን ሳለ ከተጨዋቾቹ ከቀልደኞቹ አንዱ "ስማ አንድ ጥያቄ ብጠይቅህ ትፈቅድልኛለህ?" አለኝ።

"ጠይቅ' አልኩት፣ "አትፍራ።"

" ብቻ እንዲያው እንዲህ ያለ ጥያቄ ስጠይቅህ ቅር ትሰኝ እንደሆን ብዬ ሰግቼ ነው፣ ቅር ካለህ ይቅር" አለ።

"ጥያቄው ምን እንደሆን ሳላውቅ አስቀድሜ እንደምን ቅር ይበለኝ አይበለኝ አውቃለሁ?" አልኩት። ሌሎቹ የሁለታችንን ንግግር ሆን ብለው ይሰሙ ነበርና፣ "ጠይቀው! ጠይቀው! ቅር አይለኝም ብሏል ምን አስፈራህ?" አሉና አደፋፈሩት።

"ጥያቄዬ አጭር ነው፣ እንደዚህ ነው..."

"ተናገረው እንጂ" አልኩት።

"ጥያቄው፣ ልብስ የለበስከው መቼ ነው? የትነው? ለንደን ኤርፖርት /አውሮፕላን ማረፊያ/ ስትደርስ ነው? ወይስ ገና ካውሮፕላን ስትሳፈር?"

ጥያቄው ስላልገባኝ ምናልባት ከቋንቋው እንግዳነት እንደሆነ ብዬ" እስቲ ጥያቄውን ድገመው፣ ምን ለማለት እንደፈለግህ አላወቅሁም" አልኩት። በቀና ልቡና። አዳማቂዎቹ አዳማጮች" ሆዋ! "ብለው በሳቅ ተንከተከቱ። አንዳንድ የሚንፈራፈሩም ነበሩ። ጠያቂውም የራሱን ድርሻ በሳቅ ከፈነደቀ በኋላ ያንኑ ጥያቄውን መልሶ ጠየቀኝ።

"ልብስ? ምን ዓይነት ልብስ? የፈረንጅ ልብስ ማለትህ ነው? የሱፍ ኮትና ሱሪ፣ ሸሚዝና ክራቫት?" ስል መልሼ ጠየቅሁ።

"የለም፣ እንዲያው ልብስ የተባለ ነው ያልኩት፣ እንዲያው ጨርቅ በገላህ ላይ ያረፈብህ መቼ ነው?" አለ፣ ሳቁን አቁሞ ከምር። እዚህ ላይ አጠገቤ በስተግራዬ የተኛው ሸማግሌ ጎረቤቴ የሚያነበውን መጽሐፍ እጠፍ አደረገና መነጽሩን አውልቆ በመገረም ረጋ ብሎ፣ "እዚህ አገር ኢንግላንድ ከመምጣትህ በፊት በአገርህ በአፍሪካ ራቁትህን፣ መለመላህን ነበር ወይ? የምትሄደው? ማለቱ ነው" አለኝ።

"አዎን !" አለ ካዳማቂዎቹ አዳማጮች አንዱ። "አዎን መቼ ነበር ከዛፍ የወረድከው?"

"ጥቁር ባገሩ እንደ ዝንጀሮ ነው የሚኖረው፣ የሰው ልብስ የሚለብሰውና ሰው የሚሆነው እዚህ አገር ኢንግላንድ ሲመጣ ነው ማለታቸው ነው።" አለ ሸማግሌው ጎረቤቴ።

ምን ብዬ ልመልስ? ከየት ይጀምራል ታሪክን ማስተማር? እኛ ኢትዮጵያውያን የሶስት ሺ ዓመት ታሪክ እንዳለን፣ ክርስትና ከሀገራችን የገባው ከነሱ በፊት ገና ገና በሶስተኛው መቶ ዓመተ ምህረት መጨረሻ ላይ መሆኑን፣ እኛ የአክሱምን ሀውልት ስንሰራ እነሱ "ዋድ" የሚባለውን የጭቃ ቀለም እየተለቀለቁ ራቁታቸውን በጫካ እየተዘዋወሩ ይኖሩ እንደነበረ፣ የንግስተ ሳባን ነገር፣ የንጉስ ላሊበላን፣ የዘርዓ ያቆብን፣ ያቡነ ተክለሃይማኖትን፣ የያሬድን፣ የክፍለ ዮሐንስን፣ የራስ ወልደ ገብርኤልን፣ የቴዎድሮስን፣ የምኒሊክን፣ የአሊቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክን... ስንቱን ልናገረው? ይኸ ሁሉ መጥቶ ከገዛ ሕሊናዬ ተደቀነብኝ። የጠያቂው ድፍረትና ብልግና



በንዴት አጨሰኝ። ጨዋ የምንላቸው እንግሊዞች ለካ እንዲህ ያሉ ናቸው!?" አልኩኝ በልቤ።

"ካንተ በፊት ጆኒ ጋባ የሚባል ጋናዊ እዚህ ከኛ ክፍል ተኝቶ ነበር። እንዲሁ እየቀለዱበት ስቃዩን ሲያሳዩት ቆይተው አምላክ አዝኖለት በአራት ወሩ ድኖ ከዚህ ሆስፒታል ባይወጣ ኖሮ፣ እነዚህ ባለጌ ፊዘኛ እንግሊዞች ያሳብዱት ነበር።" አለኝ ሸማግሌው ጎረቤት። ለካ እሱ የአየርላንድ ተወላጅ "አይሪሽ" ኖሯል። ለዚህ ነው" እንግሊዞች፣ እንግሊዞች" የሚለው። ይህ የተገለፀልኝ ኋላ ነው።

"ጥያቄ ተጠይቀሃል ካልመለስክ አምነሃል ማለት ነው የልብሱንም የዛፉንም" አለኝ ጠያቂው። አዳማቂዎቹም" ሆዋ! ሚስተር ለማ፣ በክርክሩ ተረታ ሚስተር ለማ፣ " ብለው እየሣቁ አጨበጨቡ።

እዚህ ላይ ያ "የጠራ ጨረቃ" ነገር ትዝ አለኝ። ሰውን ሆን ብለው ለማብሸቅ፣ በሐሰት እያወቁ በሰው ለሚቀልዱና ለሚያፌዙ ተንኮለኞች መድሃኒታቸው፣ እነሱ የሚሰነዝሩትን ክስና ውንጀላ ወይም ነቀፋ የታሪካችንና የባህላችንን ጥንታዊነት ማስረጃ በመጥቀስ ለማስተባበል መሞከር ምንም ፋይዳ እንደሌለው፣ የሚያዋጣው ሐሰቱን፣ ውሸቱን እውነታችሁን ነው ብሎ፣ ለኔም እውነት ነው ብሎ መቀበሉ ነው አፋቸውን የሚያሲዛቸው። ባሁኑ አስቸጋሪ አጋጣሚም" በጠራ ጨረቃ" ያገለገለችኝን፣ ያንኑ የሰራሁበትን ብልሃቴን ብቅ ላደርግ ወዲያውኑ እዚያው ወሰንኩ።

"ጥያቄያችሁ ጥሩ ጥያቄ ነው" አልኳቸው፣ አጨበጨቡ። "ግን ከባድ ጥያቄ ስለሆነ ብዙ የሚያሳስብ ሆኖ ነው ያገኘሁት። "አልኳቸው በውነትም ቀላል አልነበረም ጥያቄው።" ስለዚህ አሁኑኑ፣ ዛሬ ልመልስ ስላልቻልኩ ነገ እንድመልስላችሁ ቀጠሮ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፣ "አልኩ፣ ተንጫጩ። አንዳንዶቹ" ተሸንፏል፣ አጉራህ ጠናኝ ብሏል "አሉ። ሌሎቹ መልሴን ለመስማት ከመቸኮላቸው የተነሳ እዚያው በዚያው መልሴን እንድሰጥ ወጥረው ያዙኝ።" እኔ ግን ነገ ካልሆነ ዛሬ መልሴን አልሰጥም" ብዬ አልበገርም አልኩ። ይህንን ማድረጌ ወደ ጎሬ- ኢሉባቡር አካባቢ እግዜር እንደፈጠራቸው መለመላቸውን የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን ባይኔ ባላይም በጆሮዬ ሰለሰማሁ ነው። ሸማግሌው አይሪሽ ገላጋይ ሆነና "ነገ እመልሳለሁ ብሏል፣ አታሰቃዩት ጆኒ ጋባን ልታሳብዱት ነበር። ሚስተር ለማ እንደ ጆኒ ጋባ ልማታ፣ በቦክስ ይዋጣልን ባለማለቱ ተናዶ አጉል ስድብ ባለመሳደቡ ልታመሰግኑት ይገባል። ነገ ሳይመልስ ቢቀር ነው ተረታ የሚባለው

እንደኔ ክርክሩ በቀጠሮ ቢያድር ይሻላል" አለ። ብዙዎቹ ቅር እያላቸው እያቅማሙ በሐሳቡ ተስማሙ። ነገሩን የጀመረው ጠያቂ ግን አሁንም አልለቀቀኝም።

"ነገ በስንት ሰዓት? ቁርጥ አድርጎ ይንገረን" አለ።

"ነገ እፀሐይ ለመሰጣት ስንወጣ፣ ከምሳ በኋላ በስምንት ሰዓት ነዋ!" አለ አይሪሹ ሽማግሌ። "ሚስተር ለማ ትስማማ የለም?"

"እስማማለሁ። ነገ በስምንት ሰዓት" አልኩ። ከቀጠሮው ሰዓት በፊት ሌላ ጥያቄ እንዳይጠይቁኝና እንዳያናድዱኝ ሽማግሌው ጠያቂውንና አጫፋሪዎቹን ቲፎዞዎች ቃል አስገባልኝ። በዚሁ ለጊዜው ተደመደመ።

በማግስቱ የቀጠሮው ሰዓት ከመድረሱ በፊት እንዴት አድርጌ እንደምቋቋማቸው አወጣ አወርድ ጀመር። በመሠረቱ ለጥያቄያቸው የምሰጠው መልስ እውነት መሆን እንደሚኖርበትና ክደት የማያዋጣ መሆኑን ቀደም ሲል ተገንዝቤ ወስኛለሁኝ። ስለዚህ "አዎን" ሊሆን ነው መልሱ። "አዎን እኛ ኢትዮጵያውያን፣ ሁላችንም እንደ ጅንጀሮ፣ እንደ ጉሬዛ በዛፍ ላይ ነው የምንኖረው። ልብስ የምንለብሰው ወደ እንግሊዝ አገር ልንመጣ አውሮፕላን ልንሳፈር ስንል፣ በዚያን ጊዜ ነው።" ብየ ልመልስ ነው። መልሱ ከታወቀ አቀራረቡ ነበር የሚያስፈራ። በሚመስል በሚታመን መልክ ማቅረቡ ነበር ቁም ነገሩ። ለዚህ የረዳኝ፣ አንደኛ ድሮ በስደተኞች ትምህርት ቤት፣ ከዚያም በኋላ በኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለሁ የጻፍኳቸው ግጥሞች በሙሉ ልብ ወለድ፣ ተረት መሆናቸው ነው። ሁለተኛ ሰሚዎቼና ጠያቂዎቼ አብዛኞቹ የሠራተኛው /ፕሮሊታሪያት/ ወገኖች፣ አለዚያም ዝቅተኛ የቢሮ ሠራተኞች በመሆናቸው፣ የትምህርታቸው ደረጃም ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ካገራቸው ውጪ ሌላ አገር አይተው የማያውቁ፣ በተለይ ስለ ኢትዮጵያ ምንም የማያውቁ በመሆናቸው ነው። አንዳንዶቹ በዕድሜ ጠና ጠና ያሉት ኢትዮጵያ ሲሏቸው "ኃላሚዬ" እና "ሙሶሊኒ" የሚሉ አልፎ አልፎ አልጠፉም። ግን በዚያ በሙቶ አልጋ ውስጥ አንድ ቢበዛ ሁለት ቢገኝ ነው። የቀሩት ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ሰምተው የማያውቁ ናቸው። እንኳን ኢትዮጵያን፣ አቢሲኒያን አያውቁም። በዚያን ዘመን ቴሌቪዥን ለተራው ሕዝብ አልተዳረሰም ነበርና ይህ ሁኔታ ለድርሰት ኩሸት አመቺ መሆኑን ለኔም በግልጽ ታየኝና፤ የመልሱን አቀራረብ በልብ ወለድ ኩሸት መልክ ማድረግ ይሻላል ብዬ ወሰንኩ።



ቀጠሮው ከምሳ በኋላ ጣይ ለመሞቅ በረንዳ ከወጣን በኋላ፣ በስምንት ሰዓት ነበር ብያለሁ። ሰዓቱ ሲደርስ ዋናው አላጋጭ ጠያቂና አጫፋሪዎቹ፣ አዳማቂዎቹ በአልጋዬ ዙሪያ ተሰበሰቡ። አንዳንዶቹ እንክል እንክል እያሉ መጡ፣ አንዳንዶቹ በተሽከርካሪ ወንበር፣ አንዳንዶቹ በአንድ ወይም በሁለት ማንከሻ መቋሚያ እያነከሱ መጡ። ሁሉም የአጥንት በሽታ ህመምተኞች ናቸው፣ አብዛኞቹ አመትም ሁለት ዓመትም ከዚያው ሆስፒታል ያልወጡ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ እንደኔው እንኳንስ ከአልጋቸው ሊወርዱና ከናካቴው ከወገባቸውም እንኳን ቀና እንዳይሉ የተከለከሉ ስለሆኑ፣ ነገር ግን አልጋቸው ልክ እንደኔው የተሽከርካሪ ወንበር የመሠለ አራት የሕፃናት ብስክሌት ዓይነት የላስቲክ እግር ያለው ስለሆነ ነርሷን ጠርተው እየተነዱ ወደኔ ጠጋ ጠጋ አሉ። ሌሎች እዚያው በአልጋቸው ላይ ተኝተው የምለውን ለመስማት ተዘጋጅተው ነበር። ሁሉም ከጠቅላላ አኳኋናቸው ይታያል።

"መልስህን አዘጋጅተሃል፣ ሚስተር ለማ?" አለኝ ሽማግሌው አየርላንዳዊ፣ እንደ ዳኛም እንደ ሊቀ ጉባኤም ሆኖ። እሱም ካልጋቸው ከማይነሱት አንዱ ነው።

"አዎን፣ አዘጋጅቻለሁ" አልኩ። ቀላጆቹ የማላገጥ ጭብጨባቸውን አቀለጡት።

"እንግዲህ እናንተ፣ እናንተ አላጋጮች ጫጫታችሁን አቁሙ፣ "አላቸው ሽማግሌው።

"ሚስተር ለማ የፈለገውን ያህል ጊዜ ፈጅቶ መልሱን ራሱ በሚያስበው ዓይነት ይስጥ፤ እናንተ፣ እኛ ሁላችንም በጸጥታ እስኪጨርስ መስማት ነው። ጥያቄ የሚፈቀደው ከመልሱ በኋላ ነው፤ በዚህ ተስማመተናል?"አለ።

"አዎዎ!..." አሉ።

"ቀጥል ሚስተር ለማ፣ " አለኝ። እኔም ጀመርኩ፣ የልብ ወለድ ድርሰቴን።

"ከሁሉ አስቀድሞ የኛ አገር ሙቀት አለው፣ ፀሐይ አለው፤ ሰማዩ ሁል ጊዜ ቀለሙ ሰማያዊ ነው፤ እንዲህ እንደናንተ አገር የብርድና የጭጋግ፣ የዝናብና የበረዶ አገር አይደለም። በበጋ ከዝናብ ለመጠለያ እንደናንተ ጃንጥላ ይዘን አንበርም፤ ጃንጥላ አያስፈልገንም፣ ልከኛ ነው መካከለኛ። ስለዚህ ብርድ ልብስ አያስፈልገንም፣ ባጣቃላይም ልብስ አያስፈልገንም፤ ምክንያቱም እግዜር በስራው አካላታችን ስለማናፍርበት ስለምንኮራበት ሰው እንዳያየው በጨርቅ አንሸፍነውም። ስለዚህ መራቆት ከነውር አይቆጠርም። በኛ አገር እንዲያውም ከተፈጥሮ ውበት ጋር የምንዋሀድበት የምንቀራረብበት አንዱ መንገድ ነው ብለን እናምናለን።

ከአየሩ፣ ከአፈሩ፣ ከውሃው፣ ከዛፍ ከቅጠሉ፣ ከሳሩ፣ ካድባሩ ካውጋሩ፣ ከወንዙ ከወንዛወንዙ፣ ከእፅዋቱ ከእንስሳቱ፣ ከአእዋፉ፣ ከዓሳው... እነዚህ ሁሉ ጥጥ ፈትለው፣ ከጨርቅ ልብስ ሠርተው አይለብሱም፣ እዝጌር እንደፈጠራቸው ነው መለመላቸውን ተደስተው የሚኖሩት። "እዚህ ላይ ቆም አልኩኝ፣ በደንብ እንዲያጤኑት ብዬ።

"ለመሆኑ ይቺ ኢትዮጵያ የሚባለው አገር የሚገኘው በደቡብ አፍሪካ ነው?" አለ አንዱ ጠያቂ።

"የለም፣ " አልኩት፣ " የለም ከደቡብ አሜሪካ ጥቂት ወደ ምስራቅ ሲል ወዲህ ነው ያለው"

"ታዲያ የጨርቅ ልብስ ካለበሳችሁ ምን ትለብሳላችሁ? ቆዳ?" አለ የተራቀቀ ጠያቂ።

"የለም፣ ጨርቅም ቆዳም አንለብስም። በደረቅ መሬት ላይ ካለን ልብሳችን ዙሪያችን ያለው ንጹህ አየር ነው፣ በወንዝ ወይም በባህር ውስጥ፣ በዋና ጊዜ ስንገኝ ጥሩ ውሃ ነው" አልኩት። ጠያቂው መልሴ በጣም ስለተራቀቀበት ራሱን ወዘወዘ። ቀጥሎ አንዱ፣ "ልብስስ አይኑራችሁ፤ ምግባችሁ ምንድነው?"

"ጥሬ ስጋ እንበላለን።"

"ሳይጠበስ? ሳይቀቀል? እንዲያው ጥሬውን?!" አለ አንዱ በመገረም።

"እንዲያው፣ እንዳለ እዝጌር እንደፈጠረው። ሲበሉት ሲጥም እንዲህ አይምሰላችሁ። እንዳይበላሽ፣ ለስንቅ ለማስቀመጥ ስንፈልግ ደሞ በሰላ ባልጩት እንዘለዝልና ከዛፍና ከዛፍ ቅርንጫፍ መሃከል በማድረግ ሐረግ ቢጤ እንዘረጋና፣ እዚያ ላይ እንሰቅለዋለን። ያገራችን ፀሐይ ወዲያው ያደርቀዋል። እሱ ቋንጣ ይባላል። ቋንጣ ሲቆረጥሙት ሲጥም እንዲህ አይምሰላችሁ" አልኩ።

"ፍራፍሬስ ትበላላችሁ?" አለ አንዱ።

"ፍሬማ ሞልቶ! ዛፍ ቅጠሉ ፍሬ ነው። ያገራችን ፍሬ እንዳፈር ነው፣ ፍሬ ከዚያው ከዛፉ ላይ ነው ተቆርጦ ትኩሱን የሚበላው። ብርቱካንም ማንጎም፣ ትርንጎም፣ ወይንም፣ መንደሪንም፣ ሎሚ እንኳን ሳይቀር የሚበላው እዚያው ከዛፉ እየተቆረጠ ነው እንጂ ተቆርጦ ውሎ ካደረ ይጣላል።"



"ለምን? እኛ ከጃማይካ የመጣ ሙዝ ነው የምንበላው "አለ ሌላው። "ምንም መጥፎ ነገር የለበትም፣ አይበላሽም፣ በማብረጃ ከቀዘቀዘ..."

"የለም በመበላሸቱ አይደለም የማንበላው። ሃይማኖታችን ያደረ ፍሬ መብላትን ስለሚከለክል ነው። ተቆርጦ ያደረ ፍሬን ርኩስ መንፈስ ስለሚለክፈው። ያንን የተለከፈውን የበላ ልክፋት ይይዘዋልና ስለዚህ ነው"

"ምን ዓይነት ሃይማኖት ነው ያደረ ፍሬ አትብሉ የሚለው? የእስላም ነው የክርስቲያን?" ብሎ አንዱ ሲጠይቅ፣ አንዱ አውቃለሁ ባይ፣

'የእስላምም የክርስቲያንም አይደለም፣ የሂንዱዎች ሃይማኖት ነው - ስሙ 'ቡዲዝም' ይባላል" አለ።

"የለም ሁለታችሁም ተሳስታችኋል፣ "አልኳቸው። "የኛ ሃይማኖት ከሶስቱም የተለየ ነው በናንተ ቋንቋ 'አኒሚዝም' ይባላል። ይኸውም መንፈስን ማምለክ ነው። መንፈስ በማናቸውም ነገር ያድራል። መንፈሱን ስናመልክ ማደሪያውን ለመነጠል ስለማይቻል እሱንም እናመልካለን። ለምሳሌ አንዱ ዓይነት መንፈስ በዛፍ፣ አንዱ በቋጥኝ፣ አንዱ በወንዝ፣ አንዱ በተራራ፣ አንዱ በጅግራ፣ አንዱ በቆቅ፣ አንዱ በሜዳ አህያ ያድራል። ስለዚህ እኛም እንደ የአካባቢው እንደየ አቅራቢያችን ከዚህ አንዱን ወይ ሁለቱን እናመልካለን። እንሰግዳለን፣ እጣን እናጨሳለን፣ ዶሮና ፍየል መስዋዕት እናቀርባለን፣ ማህደሩን የተነጠረ ለጋ ቅቤ እንቀባለን፣ ዳቦና ቆሎ እናቀርባለን፣ ለሱ ደስ የሚለውን እሱ የሚወደውን ጨሌ ባንገታችን እናስራለን። አንዳንዱ መንፈስ አልፎ አልፎ በሰው ላይም ያድራል፤ ያን ጊዜ ያደረበትን ሰው ወንድም ይሁን ሴት እሱን እናመልካለን።"

"ሰውስ?! ሰው ታመልካላችሁ?" አለ ሸማግሌው አይሪሽ ነገሩ በጣም አስገርሞት። ጠንካራ የካቶሊክ ሃይማኖት ያለው ነውና።

"እንጨት፣ ዋርካ፣ ዛፍና ወንዝ፣ ተራራ ካመለክን፣ ሰውን የማናመልክበት ምክንያት የለም" አልኩት።

" ሰው ፍጡር ነው፣ "አለ ሌላው።

"ዋርካም፣ ወንዝም ፍጡር ነው" አልኩት።

"ታዲያ ፍጡሩ ተመልሶ ፈጣሪ ከሆነ፣ ፈጣሪና ፍጥረት በምን ይለያል?" አለ።

"እናንተ ኢየሱስ እያላችሁ የምታመልኩትም ሰው ነበር" አልኩት።

"ያ ሌላ፣ ይኸ አንተ የምትለው ሌላ" አለ ሽማግሌው። " ይኸንን ብንተወው ይሻላል ልጆች፣ የሃይማኖት ነገር ነው። ሌላ ሌላ ጥያቄ እንዳላችሁ ጠይቁት።"

"ፍራፍሬ የምንበላው እዚያው ከዛፍ እየተቆረጠ ትኩሱን ነው ብለሃል፣ አንዳንዱ ዓይነት ፍሬ በጋዜጣ ስዕል እንዳየሁት እንጨቱ ረጅም ዛፍ ነው። ለምሳሌ እንደ ኮኮናት፣ እንደ ፓፓዬ ያለውን እንጨት እንዴት ብላችሁ ቆርጣችሁ ታወርዱታላችሁ ታዲያ?" አለ አንዱ እስካሁን ዝም ብሎ ቆይቶ።

"ይኸ ቀላል ነገር ነው። ዝንጀሮዎች አሉን፤ አሽከራችን ተላላኪያችን እነሱ ናቸው። አንዱን ገመሬ ዝንጀሮ 'ቡቺ ! ቡቺ' ብለን ጠርተን ሙዝም ሆነ ፓፓዬ ወይ ኮኮናት ቆርጦ እንዲያመጣልን ትዕዛዝ መስጠት ነው፤ ከመቅጽበት ይዞልን ከተፍ ይላል። ካንዱ ቅርንጫፍ ወዳንዱ ቅርንጫፍ እየዘለለ፣ ሲያስፈልገው በወፍራም ሐረግ እንደ ጅውጅው ጨዋታ ካንዱ ዛፍ አንዱ ዛፍ እየተዘዋወረ ወዲያው እንዲያመጣ የታዘዘውን ፍሬ ቆርጦ ያመጣል።"

"ይኸማ ልክ እንደ 'ታርዛን' ማለት ነው!" አለ አንዱ የተገረመ።

"ይቅርታህን፣ 'ታርዛን' የሚባል ነገር አላውቅም" አልኩት እያወቅሁ።

"ታርዛንን በኋላ እናስረዳሃለን፣ አሁን ቀጥል... ጥሞኛል "አለ ሁለተኛው

"በኛ አገር ዝንጀሮና ጦጣ እንዲህ እንደናንተ አገር በብረት ቁልፍ ተቆልፈው፣ የእድሜ ልክ እስረኛ ሆነው የልጅና ያዋቂ መጫወቻ አይደረጉም። እኛ አገር ነፃነት አላቸው፣ የተፈጥሮ ነፃነት። የጫካ፣ የዱር፣ ነፃነት። ኑሮአቸውም እንደ ውሻ፣ እንደ ድመት፣ እንደ ላም፣ እንደ በሬ፣ እንደ በግ፣ እንደ ፍየል፣ እንደ ግመልም፣ ከሰው አጠገብ፣ ከሰው አካባቢ፣ ከሰው ጋር ነው። አንዳንዴ አየሩ ቀዝቀዝ ባለበት ሌሊት በጎፈራቸው ሙቀት እንዲሰጡን ብለን ጠርተናቸው አብረናቸው ጎን ለጎን እንተኛለን፣ ልክ እንደወንድማማችና እትማማቾች ወንዱ ከወንድ፣ ሴቷ ከሴት ጋር።"



"ይገርማል!" አለ አንዱ ፈላስፋ መሳይ። "ይኸውላችሁ፣ ይህ ነው የተፈጥሮ ሕይወት መኖር ማለት። አዳምና ሄዋን በገነት ሲኖሩ ልክ እንደዚህ ያለ ኑሮ ነበር የሚኖሩት። እኛ ልጆቻቸው ነን ስልጣኔ ብለን በፋብሪካ ጭስና በባቡር፣ ባውሮፕላን፣ በአቶሞቢል፣ በሞተር፣ በመኪና ጩኸትና ግማት ሕይወትን ያበሸናት። እድሜ ልካችንን በሱፍ ልብስ ታጅለን፣ እንደነ ሚስተር ለማ የአፍሪቃ ፀሐይ ገላችንን አይነካው ይኸው አጥንታችን እየዛለ፣ እየተፍረከረከ፣ እየተሸረሸረ በ'ቲዩበርክሎሲስ' እየተበላ እዚህ ሆስፒታል ዓመት፣ ሁለት ዓመት፣ ሶስት ዓመት ተኝተን ገና ፈጽመን ያልዳንን አለን። እኔ ይኸው ሁለተኛ ዓመቴን? ጨርሼ ሶስተኛውን መጀመሬ ነው።"

"ያልከው ትክክል፣ እርግጥ ነው" አልኩት። "እኔም ይኸ የአጥንት ነቀርሳ በሽታ የያዘኝ እዚህ እናንተ አገር ከመጣሁና በሱፍ ልብስ መታጀል ከጀመርኩ በኋላ ነው። ባገራችን ያጥንት በሽታ የሚባል ነገር የለም፤ በዘጠና ዓመታቸው አንዲት ጥርስ ያልወለቀችባቸው ሽማግሌዎች አውቃለሁ።"

"እሺ" አለ አንደኛው። "ጋብቻችሁስ እንዴት ነው? ማለቴ ስትድሩ፣ ስታገቡ፣ ስትጋቡ፣ ?"

"ስንት ሚስት ታገባላችሁ?" አለ ሌላው በመቁነጥነጥ መዳፎቹን እያሻኮተ። ሰውየው ያገባ ነው፣ በግራ እጁ ጣት ላይ ያሰረው ቀለበት እንደሚያሳየው።

"ስንት ሚስት?" አልኩና እንደ ማስላት፣ እንደ ማሰላሰል ለጥቂት ሴኮንዶች በሐሳብ ተመስጬ ዝም ብዬ የእጆቼን ጣት እቆጥር ጀመር። ያን ግዜ ሁሉም ጭጭ እርጭ ብለው ሲያዳምጡ ከአፌ የሚወድቀውን ቁጥር ለመቅለብ በከፍተኛ ንቃትና በታላቅ ጉጉት እንደሚጠባበቁ ታወቀኝ፣ ተሰማኝ።" ስንት ሚስት አላችሁ?" አልኩኝ መልሼ።

"አዎን!!" አሉ በሕብረት። "አዎን ስንት ሚስት ታገባላችሁ?"

"ስንት ልበላችሁ? ለመልስ ያስቸግራል..." አልኩኝ ልባቸው ይብሱን እንዲንጠለጠል ብዬ።

"ምናልባት ከጥያቄያችን አቀራረብ ይሆናል ለመልሱ ያስቸገረው፣ "አለ አንዱ ፈላስፋ መሳይ ተመራማሪ። "ሚስተር ለማ፣ ፍቀድልኝና ያንተን የራስህን ልጠይቅህ። አንተ ራስህ ስንት ሚስት አለህ?"

"እኔ? እኔማ ገና ተማሪ ነኝ፣ ቤት ንብረት በደንብ አላደራጀሁም። እኔ ያለኝ ሚስት አራት ብቻ ነው። ጀማሪ ነኝ ..."አልኩ

"አራት!? አራት ሚስት? አራት ሚስት አለኝ አለ።" አራት ሚስት... አራት "ቻቻታ፣ ድብልቅልቅ ሆነ፣ እዚህ ላይ ሽማግሌው በዳኛነቱ ሁኔታውን ለማረጋጋት ሞከረ፣

"እስቲ እባካችሁ ዝም በሉ ላንዳፍታ፤ ሚስተር ለማ አራት ሚስት አለኝ ብሎ ሲናገር እኔ ራሴ አልሰማሁም። እውን ሚስተር ለማ፣ በውነት አራት ሚስት አለኝ ብለሃል?" አለ ጆሮውን ጠርጥሮ።

"አዎ ያሳዝናል፣ "አልኩት። "ሌሎቹ ባልንጀሮቼ አገር ቤት ያሉት፣ እንደኔ የፈረንጅ እውቀት ፍለጋ ካገራቸው ያልወጡት፣ አምስት- ስድስት- ሰባት- ስምንት- ዘጠኝ ሚስት አግብተዋል። እኔ ብቻ ነኝ እማራለሁ ብዬ በአራት ሚስት የተወሰንኩት። አራቱም አገሬ ነው ያሉት፣ "ብዬ ተከዝ አልኩ- ላመሌ። ይኸ በቀላጆቹ አዳማጮቼ ያሳደረው ትግርምት አንድ ትልቅ ቦምብ ከአየር ሳይታሰብ ወርዶ ባጠገባቸው እንደፈነዳ ያህል ነበር። ዝም ጭጭ አሉ። እኔን አስተያየታቸውና አመለካከታቸውም የመናቅና የማላገጥ መሆኑ ቀረና መፍራት፣ ብሎም ያድናቆትና ያክብሮት ሲሆን ለውጡ እዚያው በዚያው በገሃድ ታየኝ። በውስጤ ኩራት መሳይ ተሰማኝና ውስጣዊ ደረቴን ነፋሁ። ትግርምቱና ድንጋጤው ጋብ ሲልላቸው እኒያ እኔን ያንጓጥጡና በእኔ ያላግጡ የነበሩ የእንግሊዝ መደዴዎች፣ እንደ ደቀመዛሙርት ሆኑና፣ እኔን እንደ አንድ ዓይነት መምህር አይተው፣ ጥያቄያቸውን በከበሬታ ሆነ የሚያቀርቡት።

"ሚስተር ለማ፣ አንተ ገና ተማሪ- ጀማሪ በመሆንህ ትዳርህ ስላልደረጀ አራት ሚስት ብቻ ነው ያለኝ ብለህ አስረድተኸናል። ታላላቅ ከበርቴ ነጋዴዎችና ታላላቅ መኳንንት ስንት ሚስት ቢኖራቸው ነው?" አለ ያ ፈላስፋ መሳዩ።

"ታላላቁ? መኳንንቱ?" አልኩት መልሼ። "እነሱማ መቼ ሁለት፣ መች ሦስት! እስከ ሶስት መቶም ያላቸው" አሉ። "ስለው በውነትም የውጋዴን ሶማሌ ባላባቶች ትዝ አሉኝና፣ "ስለዚህ ልጆቻቸው ብቻ አገር ናቸው፣ አገር ይሞላሉ። የሚስቱን ብዛት ባገራችን የሚወስነው የሰውዬው ሀብትና ንብረት መጠን ነው እንጂ



እንዲህ እንደናንተ በአንድ ሚስት ብቻ ተወስነህ እድሜህን ሙሉ ኑር የሚል የክርስቲያን ሃይማኖት ወይም ጥቂት ሻል ሲል በማናቸውም ጊዜ ከአራት ሚስት በላይ እንዳይኖርህ ብሎ አልሸሹም ገለል አሉ የሆነ የእስላም ሃይማኖት ባገራችን የለም። ይኸውም ተመስገን ነው፣" አልኩኝ። ትርምስ፣ ድብልቅልቅ ሆነ። ክርክሩ ከኔ ጋር መሆኑ ቀርቶ እርስበራሳቸው ሆነ። የገረመኝ ጥቂቶቹ እነ አባደፋር በመጠኑም ቢሆን የኔን ሃሳብ መደገፋቸው ነበር። መጀመሪያ በጥያቄ የለከፈኝ ጎልማሳም ቁጥሩ ከነ አባደፋር ሆኖ መገኘቱ በልቤ አስቆኛል። ቢሆንም የነሱው የርስበርስ ክርክርና ውዝግብ እስኪያከትምና እስኪልኩን ድረስ ተራዬን ታዛቢና ተመልካች ሆኜ እመለከት ጀመር። ክርክሩ አራት ሚስት የሚለው "ሂንዱይዝም" ነው "ቡዲዝም" ነው። የለም እስላም ብቻ ነው ወዘተ... ነበር። ሽማግሌው አይሪሽ በዳኝነቱ እጁን አጨብጭቦ ተንታራኪዎቹን ጎልማሶች ለጊዜው ጸጥ አረጋቸው።

"ስሙ" እለ፤ "እናንተ የምትነታረኩት በማታውቁት፣ በማይገባችሁ ነገር ነው። የእስላም ሃይማኖት አማኙን በአራት ሚስት ቢወስነውም አራቱንም እኩል አድርገህ ውደዳቸው፣ አንዱን ካንዱ ሳታበላልጥ ይላል ማለትን አሁን ትዝ አይለኝም እንጂ አንድ ቦታ ባንድ ጋዜጣ ውስጥ አንብቤአለሁ። ከአራት ሚስት በላይ ያልተፈቀደው ያንድ ሰው ፍቅር በብዙ ሚስቶች መሀከል ቢከፋፈል ለያንዳንዷ የሚደርሳት በጣም ትንሽ ይሆናል በማለት ይመስለኛል" ብሎ ደመደመ።

"ሶስት መቶ ሲሆኑ፣ ለያንዳንዷ በረከቱ፣ ጠበሉ የሚደርሳት ከመቶ አንድ ቀን ብቻ ነው ማለት ነው! አንድ ቀን ብቻ? አስቡት፣ እዝጌር ያሳያችሁ "አለ አቶ ፈላስፋ። "አንድ ቀን ምንድነች? ናፍቆቱ ብቻ ይገድላታል!" በዚህ አባባል ሳቁ፣ ተሳሳቁ። ሳቁ ሲበርድ አንዱ፣ ያ የጋብቻ ቀለበት ያጠለቀው ጥያቄውን ወደኔ አዞረው።

"በምር ግን ሚስተር ለማ፣ ቀልዱ ይቅርና አንተ ራስህ እዚህ አገር ድረስ ለትምህርት መጥተህ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነህ። በውነት አንተ ይኸን ሁሉ ያውሮፓ ስልጣኔ ካየህ በኋላ ላንድ ወንድ ካንድ ሚስት በላይ ያስፈልገዋል ትላለህ? እውነቱን ተናገር" አለኝ። በቁም ነገር።

"እስቲ አንተ ራስህ አስበው?" አልኩት። "በግራ እጅህ ጣት ቀለበት አጥልቀሃል፣ ይህም ያገባ ወይም ሊያገባ ያጨ ሰው ምልክት

መሆኑን እዚህ አገር በቆየሁበት ጊዜ ለመረዳት ችያለሁ። ስለዚህ አንተ ወይ ያጨህ ወይ ያገባህ ነህ። ከሁለቱ የቱን ነህ አንተ?" አልኩት።

"ያገባ ነው፤ ያገባ ነው..." አሉ በሕብረት። "ሚስቱ ብቻ እንደሚገባት ያህል እየመጣች አትጠይቀውም።" አለ አንዱ ቀልደኛ። ባለሚስቱ እንደመናደድ አለና፤ "አንተ አርፌህ ተቀመጥ፤ አድብ ብዬሃለሁ፤ ወጥመድ አፍህን ዝጋ። ሚስቴን ከዚህ የሚያገባት የለም፤ ስራህ አይደለም። ሚስተር ለማን ነው በቁም ነገር የጠየቅሁት። ታዲያስ፤ ሚስተር ለማ ምን ትላለህ አንተ?" ለወዲያው ሳልመልስለት በማሰላሰልና በማስላት ጥቂት ሴኮንድ ካሳለፍኩ በኋላ መልሼ ጠየቅሁት።

"እስቲ አንተ ራስህ አስበው፤ አታስበውም?" አልኩት" አንተ አንድ ሚስት አለህ? የለህም?"

"አለኝ፤ "አለ

"አንድ ሚስትህን ትወዳታለህ፤ ታፈቅራታለህ። እሷም በማናቸውም ነገር ታረካሃለች፤ ታስደስትሃለች።"

"ያለ ጥርጥር!" አለ።

"ስለዚህ አንድ ሚስት ጥሩ ነው ማለት ነው፤ አንተው እንደመሰከርከው።"

"ጥሩ፤ ጥሩ ነው።"

"ስለዚህ አንድ ጥሩ ከሆነ ሁለት ከአንድ ይበልጣል፤ ሶስት ከሁለት ይበልጣል፤ አራት ከሶስት ይበልጣል- የደስታ መጨረሻ ድንበር ነው!" አልኩኝ አከታትዬ። አዳማጮቼ አጨበጨቡ፤ ባቀረብኩት ማቲማቲክሳዊ ሎጂክ ተደስተው። ቀጠል አደረግሁና "እናንተ የእንግሊዝ አገር ሰዎች፤ አዝንላችኋለሁ። እኛ የሚስት ፍቅር እንዳይሰለቸን በወር አራት ጊዜ ያልጋ ደባላችንን ለመቀየር ስንችል፤ እናንተ ምስኪን እንግሊዞች ግን አንድ ይዛችሁ ከሷ ጋር ብቻ ስትንገታገቱ እለተ ሞታችሁ ይደርስባችኋል። ምስኪኖች ናችሁ፤ አሳዛኞች..." አልኩኝ ድምጼን ከፍ አድርጌ- በዲስኩር አነጋገር። ሁሉም" ኋዋዋዋ!" ብለው ተንከትክተው ሳቁ። ሳቁን ሰምተው ነው መሰለኝ ወዲያው የወንድ አስታማሚ ነርሶቻችን መጡና" ፀሐይ መሞቂ ይበቃችኋል፤ ለዕለቱ የሚበቃ የፀሐይ ብርሃን አግኝታችኋል፤ መምሸቱ ነው ይበርዳችኋል" ብለው ተሽከርካሪ አልጋችንን እየገፉ ወደ አዳራሻችን መመለስ ጀመሩ። ስንነዳ ሳለ አንዱ ያልበቃው፤

"ሚስተር ለማ!" አለ። "ሚስተር ለማ የመጨረሻ ጥያቄ- አንዲት ብቻ ... አራቱ ሚስቶችህ አገሬ ነው ያሉት ብለሃል፤ አይናፍቁህም? ናፍቆቱን እንዴት ትችለዋለህ?"



"አልቻልኩትም፤ ተስፋ የማደርገው እዚህ አገር አንድ ቆንጆ የእንግሊዝ ቆንጆ ተዋውቄ፤ በናንተ ደንብ አግብቼ፤ አምስተኛ ሚስት ለመጨመር ነው። ባንዳንዶቹ ቆንጃጅት ነርሶች፤ አስተዋውቁኝ እንደሆን፤ ዓይኔን አልፎ አልፎ ጣል የማደርገው ለዚህ ብቻ ነው" አልኩ።

"የቷ ነች? የቷ ነች?... "የሚል የጥያቄ ናዳ አወረዱብኝ።

"አይ ይህ ታላቅ ምስጢር ነው፤ ለሰው አይነገርም። ከሶስት ነርሶች የተኛዋ እንደምትሆን ገና አልወሰንኩም፤ በማመዛዘን ላይ ነኝ... "በማለት ላይ እንዳለሁ፤ አስታማሚው አልጋዬን እያሽከረከረ እየነዳ ወደ ቤት አግብቶ ወስዶ እቦታዬ ሽማግሌው አይረሽ አጠገብ አቆመኝ። ወሬው በሆስፒታሉ ተነዛ ዝናዬም በየመኝታ አዳራሹ ተዳረሰ።

አዎ ዝናዬ በሆስፒታሉ ተነዛ። "ሚስተር ለማ የሚባል አንድ አፍሪቃዊ ተማሪ ገና በልጅነቱ አራት ሚስት አለው! ተባለ። ሃይማኖት የለውም፤ ፍጹም አረመኔ ነው፤ ዋርካ ዛፍና ታላላቅ ተራራ፤ ታላላቅ ወንዝና ታላላቅ ቋጥኝ ድንጋይ ነው የሚያመልከው፤ ክርስቲያንም አይደለም፤ እስላምም አይደለም፤ ሂንድም አይደለ፤ ቡዲስትም አይደለ፤ ሺንቶም አይደለ እንደጃፓኖቹ፤ እልም ያለው ሃይማኖት የለሽ አረመኔ ነው!" ተባለ። የባሰው ይባስ ብሎ ደግሞ "ለዚህ ለሰይጣናዊ ለዲያብሎሳዊ እምነቱ ሽንጡን ገትሮ ይከራከራል ይባላል" ተባለ። ይህን የሚሉት መቼም ከመደዶው የእንግሊዝ ሠራዊት መሀከል ምስጢረ ሃይማኖትን አውቀናል፤ ብሉይና ሀዲስን አንብበናል የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው እንጂ ሁሉም አልነበሩም። አብዛኞቹ ስለ ነብር ሃይማኖት በዚያም ሆነ በዚያ፤ ስባሪ ሳንቲም ቁራጭ ዕውቀት አልነበራቸውም።

አዎ፤ ዝናዬ ተጫማመረበትና ተጋነነ። ወሬውን ማመን እያስቸገራት የሰማችውን ሁሉ እያመጣች የምትነግረኝ ያቺ የኔ ልዩ ወዳጅ የነበረችው ነርስ ነች። "ሚስተር ለማ፤ አሁን ባገሩ በሉ ስም ያሉት ሚስቶች አራት ብቻ ቢሆኑም፤ ያገባው ግን አስር ሚስት ነው። ሰላሳ ዓመት እንኳን ሳይሞላው፤ ጉድ- ጉድ! "ተባለ" ሚስተር ለማ ዛሬ ያደረገውን ሰምታችኋልን? ሜትረኑዋ ረፈድ ሲል እየዞረች በሽተኞች ስታነጋገር ሳለች ማመልከቻ ጽፎላት ኖሮ እሱ አልጋ አጠገብ ስትደርስ ሰጣት። ምን ብሎ እንደሰጣት ታውቃላችሁ?! 'እኔ እንደሌሎቼ ነጭ በሽተኞች ሻይ ደረቁን ሆን ሻይ በወተት መጠጣት አልቻልኩም፤ ባገሬ

ከፋ የሚባል አገር አለ፣ ጣሊያኖችና ፈረንሳዮች "ካፌ" የሚሉት፣ እናንተ "ኮፊ" የምትሉት ቡና መጀመሪያ የበቀለውና የተገኘው ከዚያ ነው፤ አሁንም ሰው ሳይተክለው እንዲሁ በተፈጥሮ የከፋ ጫካው ዛፍ ቅጠሉ ቡና ነው። እኛ ቡና አንተክልም። ጊዜው ሲደርስ ሲንዠረገግ ብቻ ሄደን ከዛፍ ላይ መሸምጠጥ ነው። ወይም ፍሬው በስሎ እመሬት ሲወድቅ ማፈስ ነው። ስለዚህ እድሜ ልኬን ሙሉ ከተወለድኩ ጀምሮ የምጠጣው ቡና ብቻ ስለሆነ፣ እዚህ እንግሊዝ አገር "ቡና" እየተባለ በቡና ስም የሚፈላው አተላ "ሻይ" ከተባለው የቻይና ቡና ይሻላልና፣ የቡና ቅራሪም ቢሆን እንድታፈሉልኝና ከሻይ እንድትገላግሉኝ በማክበርና በታላቅ ትህትና አመለክታለሁ' ይላል!"

"ወይ ጉድ! ታዲያ ሜትሮኗ ምን መለሰች. ?"

"ሜትሮኗም 'ይህ የማይቻል ነው' አለችው። በዚያ በመኝታ አዳራሽ የሚገኘው አንድ መቶው በሽተኛ በሙሉ ሻይ ሲጠጣ፣ ላንድ ለሱ ተብሎ በተለይ ቡና ለማፍላት በፍጹም የማይታሰብ መሆኑን ነገረችው።"

"ምን አለ?"

"የሜትሮን መልስ ይህ ከሆነ፣ ማመልከቻው በይግባኝ ለበላይ ይተላለፍልኝ" አላት። እሷም' ደግ ነው ለዋናው ሐኪም፣ ለሆስፒታሉ ዲሬክተር አስተላልፍልሃለሁ' አለችው።" ነገሩ ግን ገርሚትም አስቂትም ነበር። እውነትም ሜትሮኗ በቸርነቷ ማመልከቻዬን የሆስፒታሉ ዲሬክተር ለሆነው ለዋናው፣ ለታላቁ ሐኪም አድርሳልኝ ኖሮ፤ ሰሞኑን እሱም ተራውን የሆስፒታሉን የመኝታ አዳራሽ አንድ ባንድ ሲጎበኝ ሜትሮኗና ሌሎቹም ሲስተሮች አጅበውት ነበር። እኛ አዳራሽ ደርሶ አንዳንድ የጠናባቸውን፣ ብዙ ጊዜ የተኙትን በሽተኞች ቆም ቆም እያለ ሲያጽናና፣ የኔን አልጋ አልፎ ሊሄድ ነበር። ግን ከዚያ ሁሉ ሰው አንድ ጥቁር እኔ መሆኔን አይቶ መለስ ብሎ ወደኔ መጣ።

"ታዲያስ፣ አንተ ወጣት? ተስማምቶሃል ቤታችን? የለንደን' እስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ' ተማሪ ነህ ማለትን ሰምቻለሁ፣ " አለና፤ "የሕመሙ ሁኔታ እንዴት ነው?" ብሎ ሜትረንን ጠየቃት። "የመዳን እርምጃ እያሳየ ነው ልጁ?"

"በጣም እየተሻለው ነው። ከሱ በፊት የጋናው ሰው ጆኒ ጋባ ታሞ መጥቶ ተኝቶ ነበር። በስድስት ወር ብቻ ድኖ ሄደ፤ ዶክተር ያስታውሳሉ?" አለች ሜትሮኗ።



"አዎ ትዝ ይለኛል። የአጥንት ነቀርሳ 'ቲበርኩሎሲስ' በሽታ አፍሪቃውያንን ሲጀምር በሃይል ያማቸዋል፣ ሲድኑም በኃይል ነው፣ ባጭር ጊዜ ነው የሚለቃቸው። የኛን ሰዎች ሁለት ሶስት ዓመት አንዳንዶቹም አራት ዓመት የሚያጋድማቸው፣ እነሱን ከአራት ወር፣ ቢበዛ ከመንፈቅ ይበልጥ አያስተኛቸውም ይህ የሚገርም ነው። ደንበኛ ጥናትና ምርምር ተደርጎ አፍሪቃውያኑ ያላቸው፣ የኛ ሰዎች የሌላቸው የተፈጥሮ መከላከያ ምን እንደሆነ መታወቅ አለበት።" አለ ዋናው ዶክተር። ሁሉም ነገሩን በታላቅ ከበሬታ አዳምጠው ዝምዝም አሉ። ዶክተሩ እኔን ጠጋ ብሎ አየት አድርጎ መንገዱን ሊቀጥል ሲል "ጌታዬ፣ አንድ ጉዳይ ነበረኝ፣ ማመልከቻ፣ አቤቱታ" አልኩት፤ ቆም አለ። "በሜትረን እጅ ይገኛል" አልኩኝ።

"የጻፈውን ማመልከቻ ለርስዎ አላቀረብኩትም። ሻይ እንደሌላው በሽተኛ አልጠጣም፣ በተለይ ቡና ይፈላልኝ ነው የሚለው። ይህ የማይቻል መሆኑን ያውቃል ነግሬዋለሁ..." አለች።

"አንተ ወጣት-ኢትዮጵያዊ ነህ አሉ? በምን፣ ምክንያት ነው ቡና ካልሆነ ሻይ አልጠጣም ያልከና ሻዩን እምቢ ያልከው?" አለኝ በፈገግታ ገጽ።

"ጌታዬ፣ ያለሁበትን ሁኔታ ያዩታል። አንድ ጥቁር በአንድ መቶ ነጭ መሀከል፣ በነጭ ባህር ሰጥሜያለሁ። ጥቁር ቡና ካልጠጣሁ ከናካቴው ጥቁር ቀለሜ ጥሎኝ ሄዶ ነጭ እንዳልሆን በጣም ሠግቻለሁ። ለዚህ ነው..." አልኩት። ዶክተሩም አጃቢዎቹም ከልብ ሳቁ በጨዋታዬ።

"ምን ይደረግ፣ ሜትረን? ይኸ ወጣት ኢትዮጵያዊ ጥቁርነቱን ይወዳል፣ ነጭነትን ይጠላል። ሳይፈልግ ያለፈቃዱ ነጭ እንግሊዛዊ ሁን ማለት ደግሞ አንችልም፣ ፍርድ አይደለም የቸገረ ነገር ነው። ቢሆንም እኔ መፍትሄ አለኝ። በዚህ ሆስፒታል ቡና የምጠጣ ቡና የሚፈላልኝ እኔ ብቻ ነኝ፣ ሌሎቹ ሐኪሞች ከኔ ይበልጥ የጠሩ የነጠሩ እንግሊዞች መሆናቸውን ለማስመስከር ነው መሰለኝ ቡና አይጠጡም። የሻይ ሱሰኞች ናቸው። ስለዚህ ለኔ ሲፈላ አንድ ትልቅ ሲኒ ቡና ለሚስተር ለማ እንዲቀርብለት አዝዣለሁ..." ብሎ ፊቱን አዙሮ ጉዞውን ቀጠለ።

"ታንክዩ ቬሪ ቬሪ ማች ሠር!" አልኩት ጮክ ብዬ። እዝጌር ይስጥዎ ነው፣ አመሰግናለሁ።

የቡናው ነገር በዚህ አለቀልኝ ጥቂት ችግር የፈጠረው የሃይማኖቴ፣ እነሱ እንደሚሉት የአረመኔነቴ፣ ነገር ነበር። ሃይማኖት ያንጓጥጣል፣ በሃይማኖታውያኑና በቀሳውስቱ ለሚቀልዱት አላጋጮች በሃይማኖት ላይ የሚተኩሱት ደህና ደህና ጥይት አቀብሏቸዋል፣ ስለዚህ፣ ይህ ሳይውል ሳያድር መታረም አለበት፤ የማረሙና ቢቻልም አረመኔውን ኢትዮጵያዊ ወደ እውነተኛው የፕሮቴስታንትም ሆነ የካቶሊክ ሃይማኖት እምነት መመለሱ የሌላ የውጭ ሰው ሳይሆን፣ እዚያው እሆስፒታሉ በሚገኙትና ለዚሁ ሥራ በተመደቡት ቄሶች መሆን አለበት ተብሎ ታስቦ ኖሯል። ከነዚያው ከቀሳውስቱ መካከል፣ እኔ የተመከረብኝን ሳላውቀው በሚስቶቼና በአማልክቶቼ ብዛት እየኮራሁ፣ አንድ ሚስት ብቻ፣ አንድ አምላክ ብቻ ያላቸው ወይም ከናካቴው ከሁለቱ ያጣ ጎመን በሆኑት የእንግሊዝ መደዴ ሠራተኛ ነጮች ላይ ተራየን ቱልቱላዬን እየነፋሁ፣ ልቤ እስኪወልቅ ድረስ ለራሴ ስቄ ሌሎቹንም በማሳቄ፣ በዚህ ያልወደደኝ በሽተኛ ቢኖር አንድ መቁጠሪያ ይዞ ጧትና ማታ የሚጸልይ ካቶሊክና አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ከራስጌው የማይለየው ፕሮቴስታንት ብቻ ነበሩ። ሌሎቹ ከኔው ጋር ናቸው፣ ባንድ ሚስት እድሜ ልክን በሰንሰለት ከመታሰር፣ እንደኔ ባንዴዩ አራት በማግባት በወሩ ውስጥ አንዷን ሳምንት ከንዷ ጋር፣ አንዷን ሳምንት ከሌላዋ ጋር መተኛትን መልካም ባህል ነው ብለው በሐሳብ የተቀበሉ ናቸው። ጥቂት ቢያዳግታቸውም፣ አራት አምስት አማልክት የማምለኩ ነገር ነበር። በክርስቲያን ሃይማኖትም ሶስቱ ሥላሴዎች የሚባሉ ሶስት አማልክት አሉ የሚመለኩ ብዬ ላስረዳቸው ብሞክርም ሶስቱ አንድ ናቸው አንዱ ሶስት ነው እያሉ የማይገባኝን ነገር፣ በቀላል ሂሳብ /አሪትሜቲክ/ ሊተባበል በሚችል አንጉል የጭፍን እምነታቸው መጽናታቸው እኔን በጣም ነበር በአረመኔነቴ ያስገረመኝ። ቢሆንም እኔም እነሱም በሃይማኖት ነፃነት የምናምን ስለሆነ የሃይማኖት ልዩነታችንን አብረን፣ ተከባብረን፣ በወዳጅነት በሳቅ በጨዋታ፣ አንዳንዴም የአራቱ የአምስቱ ሚስት ነገር ሲነሣ በፌንጠዚያ ነበር የምንኖረው። ይህ ሁኔታ ግን፣ ምንም ለኛ አዳራሽ ጎልማሳ በሽተኞች በጣም ደስ የሚያሰኝ ቢሆንላቸውም እሁድ እሁድ ረፊድ ሲል እየመጣ ወንጌል ለሚሰብከን የ"ቸርች ኦፍ ኢንግላድ" ፕሮቴስታንት ቄስ አደገኛ መስሎ ነበር የታየው።

በሱ አስተያየት ሰይጣን መቼም ጥቁር ነውና በጥቁር ኢትዮጵያዊ ተመስሎ እሆስፒታል ገብቶ ተኝቶ ነጮቹን የእንግሊዝ በጎች ሊሰርቅና ወደ አምልኮ ጣኦት ሊመልስ በኛ የመኝታ አዳራሽ የሸመቀ መስሎ ነው የሚታየው ብዬ መገመቴ፣ ከእውነቴ ብዙም አልራቀ። ስለዚህ ቄሱ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ አንድ እሁድ ወንጌልን



ሊሰብክልን መጣ። ስብከቱ ረፈድ ሲል ከቁርስ በኋላ ነበር የተጀመረው ቄሱ ረዘም ያለ ሽበት እንደ መውረር ያረገው፣ በልብሰ ተክህኖ ውስጥ በቅድስና የሚምነሸነሽ ዓይነት መስሎ ታየኝ። አነጋገሩም፣ ምንም ቋንቋው እንግሊዝኛ ቢሆን፣ ለዛና ቃናው ከኛው የሐበሻ ቄሶች ቅላጼ እምብዛም የተለየ አልመሰለኝም። ቄሱ እንደ መቅድምና እንደ መደምደሚያ የሚያስገባውን በጸሎት ጀመረና ወዲያው" አቡነ ዘበሰማያት "እና" በሰላም ቅዱስ ገብርኤልን" ገድፎ በዚያ በጥንታዊ፣ "በጎንደሬ" እንግሊዝኛ አወረደልን። ከበሽተኞቹ ፕሮቴስታንት የሆኑት እሱን ተከትለው ጸሎቱን መስመር በመስመር በሐረግ ደገሙ። ዝም ያልነው እኔና ካቶሊኮቹ ነን። የኔማ ዝምታ ወደ ማኩረፉ ያደላ ነበር። ቄሱ አልፎ አልፎ .ዓይኑን ወደኔ አቅጣጫ ጣል ሲያደርግ፣ አልፎ አልፎ ዓይናችን ግጭት ሲል ለአረመኔዎች፣ በተለይም ለአፍሪቃ አረመኔዎች እምብዛም ፍቅር እንደማይሰማው፣ እንዲያውም ቢቻለው፣ ጊዜና ቦታ ቢፈቅድለት በኃይል አንገት አንገታቸውን ይዞ ከመቀኛ ግንዳ እየደፈቀ ለማጥመቅ የሚመኝ ኃይለኛ ሐዋርያ መስሎ ነበር የታየኝ።

ሆኖም ቄሱ ወደ ዕለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ አመራና ከመልእክተ ጳውሎስ ይመስለኛል አለፍ አለፍ እያለ በታላቅ ስሜት፣ አንዳንድዬ እንደማሳዘን፣ አንዳንድዬ እንደመውቀስ፣ አንዳንዴ እንደመወንጀል፣ እንደመለመንና እንደመቆጣት፣ እንደማባባልም እያደረገ የቃላቱን አጣጣል እያቀያየረ ከዚያም ከዚያም አነበበልን። ያነበበው ሁሉ የሚጠቅሰው ጣኦትንና አምልኮ ጣኦትን ብቻ መሆኑ፣ ለመጀመሪያ ግር አሰኝተው ነበር። ቀስ እያለ ግን "ጣኦት" የሚለው ቃል በተነሣ ቁጥር ፊቱን በተለይ ወደኔ መልሶ ዓይኑን ከኔ አልጋ ላይ ጣል ማድረጉን አገናዝቤ፣ መልእክቱ ለኔው ለፈረደብኝ የአፍሪቃ አረመኔ በተለይ የተዘጋጀ መሆኑን ስረዳው፣ ድንገት ሣቄ መጣና አፌን አፍኜ በዝምታ እንክተከት ጀመር። ሌሎቹም በሃይማኖትና በቄስ የሚያላግጡ ጎልማሣ በሽተኞች ቄሱ ሳያያቸው በስርቆሽ የወረቀት ብጣሽ እንደኳስ አድቦልቡለው ወደኔ እየወረወሩ፣ ወይም በእጃቸው እያመለከቱ፣ የዚያን ቀን ስብከት ለኔ ብቻ እንጂ ለነሱ አለመሆኑን ሊገልጡልኝ ሞከሩ። እኔም ይብሱን ሳቁ ባሰብኝና ቢቸገረኝ በብርድ ልብሴ ፊቱን ሸፍኜ እንቅልፍ የወሰደው ለመምሰል ሞከርኩ።

ቃለ እግዚአብሔር ሲነገር መሸፋፈኔን ቄሱ ሳያይ አልቀረም። ቢሆንም እንቅልፍ እንዳልወሰደኝ፣ እንደምሰማ አሳምሮ ስለሚያውቅ፣ ከጳውሎስ የሚጠቅሰውን አንብቦ ሲያበቃ፣ የራሱን ማብራሪያ ሐተታና እንድምት አከታትሎ፣ አቀጣጥሎ አጅጎደጎደው፤ ይህም ብዙ ጊዜ ወሰደ። ስብከቱ ሲያበቃም" ደህና ዋሉ ልጆቼ" ብሎንም አልሄደ፣

እያልጋችን ድረስ እየመጣ እያንዳንዳችንን "ልጄ ሆይ ሕመምህ ተሽሎሀልን?" ማለት ያዘ። አድራሻችንን ዙሮ እስኪያዳርስ ድረስ ደሞ ብዙ ጊዜ ወሰደ። ምክንያቱም አካሄዱ አረማመዱ ጭምር መንፈሳዊ ከመሆኑ የተነሣ፣ በጣም ዝግ ያለና የተኛ ሰው እንዳይቀሰቅስ ይፈራ ይመስል ተረከዙ ምድሩን እንዳይመታ የሚጨነቅና በቋፍ በቁንጢጥ የሚራመድ ዓይነት በመሆኑ ነበር። እኔም ሲያቀብጠኝ ተሸፋፍኜ፣ እንቅልፍ የወሰደኝ መስዬ ተከናንቤ፣ የቄሱን መውጣት ስጠብቅ ጊዜው አለቅጥ ረዘመብኝ። እንዳልገለጥ፣ ያነጋግረኝ ይሆናል ብዬ ፈራሁ። ክርክር ቢገጥመኝስ?! ቆይቶ ቆይቶ ከኔ አልጋ መጣና፣ "ልጄ ሆይ፤ አንተስ ሕመምህ ተሽሎሃልን?" አለኝ። እኔ ምኔ ሞኝ ነው፣ እንቅልፍ ወስዶኝ አኮርፍ ጀመር።

"እንቅልፍ ወስዶታልን?"ብሎ ጎረቤቴን አይሪሹን ሽማግሌ ጠየቀው። ሽማግሌው አይሪሽ በመሆኑ እንደሚኮራው ሁሉ በካቶሊክነቱ ይኮራና ፕሮቴስታንቶችን ይንቅ ስለነበር፣

"አዎን፣ እንቅልፍ ወስዶታል- ባይቀሰቅሱት ይሻላል" አለው።

ሌላ ቀን በተለይ እሱን ለመጠየቅ እመጣለሁ- ሰሞኑን። ያን ጊዜ እንቅልፍ እንዳይወስደው ተስፋ አደርጋለሁ፣" ብሎ ካዳራሹ በለሆሳስ አረማመድ ወጣና ሄደልኝ፤ እፎይ! አልኩ። ገና እግሩ እንደወጣ፣ ያ እንዳይስቅ፣ እንዳይቦርቅና እንዳይፈነድቅ በቄሱ ስብከት ታስሮና ታፍኖ የነበረው, ሰራዊት ውካታውን ለቀቀው።

"ሚስተር ለማ የዛሬው ስብከት ላንተ በተለይ የተዘጋጀ ነው!"

"አጅሬ ዝናህን ሰምቷል!"

"እንዳያጠምቅህ ተጠንቀቅ!"

"ቁርባን እንዳያቆርብህ!"

"ቁርባን አልቀረልህም፣ ምን አለ በለኝ!" ተባለ። እኔም "ከአራቱ ሚስቶችህ ተፋታ እንዳይለኝ እንጂ ሌላው ግዴለም" አልኳቸው። "ደሞ 'ጣኦት፣ ጣኦት' የሚለው ምን ለማለት ነው? እኔ በተፈጥሮ ላለው ለወንዝ፣ ተራራ፣ ለቋጥኝና ለዋርካ እሰግዳለሁ፣ እሱን አመልካለሁ እንጂ፣ በሰው እጅ ለተሠራ ምስል አመልካለሁ መቼ አልኩና?!" ጣኦት ጣኦት' ማለት ከብር፣ ከወርቅ፣ ከእንጨት ከድንጋይ በቄሱ አነጋገር ተቆጣሁ። "ያላልኩትን ነው ብሏል የሚለኝ። ይሁ ማወናበድ ይባላል። እኛ ጣኦት አናመልክም፣ ምን መስዬዋለሁ? "አልኩ በቁጣ።



"እሱ እንኳን፣ ሚስተር ለማ፣ አልሸሹም ገለል አሉ ነው፣" አለ ሽማግሌው ጎረቤቴ።

"ቢሆንም፣" አለ አንዱ የኔ ጠበቃ፣ "ቢሆንም ቄሱ የሃይማኖትን ነፃነት ሐሳብ የሚቀበል ከሆነ፣ ያንተን ካቶሊክነት እንዳይነካ እንደሚጠነቀቅ ሁሉ፣ የሚስተር ለማንም ሃይማኖት አለመንካት፣ ማክበር አለበት። ሃይማኖቱ ሃይማኖት ናት። ነጭ ጥቁር አይደል"አለ።

"እውነት ብለሃል!" አልኩት በምሥጋና ስሜት። "እንዲህ ነው! አልኩኝ፣ ከሌሎቹም አብዛኞቹ በአነጋገሩ ተስማሙ።

ከፕሮቴስታንቱ ቄስ ባይሆን ለጊዜው ተገላገልኩ ስል፣ ውሎ አድሮ የካቶሊኩ ሰባኪ መጣ። የእሱ ግን አመጣጡና አቀራረቡ ለየት ያለና የተራቀቀ ስለነበር፣ ሊያጠምደኝ የሞከረው ባልጠረጠርኩት አቅጣጫ መጥቶ ባላሰብኩት ወጥመድ አስገብቶኝ ነበር። ይኸውም እንዲህ ነው፣

ከዕለታት አንድ ቀን የጥርስ ሐኪም የበሽተኞቹን ጥርስ ሊመረመር ሰሞኑን ይመጣል ብላ ሲስተሯ አስታወቀችኝ። እኔ በጥርሴ ነገር ከአማልክቶቼ የታደልኩ አፍሪቃዊ መሆኔን አስታውሼ ገና በጎልማሳነታቸው ጥርሳቸው የሚወልቅባቸውን ነጮች ባልደረቦቼን፣" ከተፈጠርኩ ከጥርስ ሐኪም ሄጄ አላውቅም፣ ጥርሴን ሐኪም ሊነካው ቀርቶ አይቶት እንኳን አያውቅም፣ ይኸውም ጥሬ ስጋ በሚፋጅ በርበሬ ስለምንበላ ነው፣" እያልኩ አስገርማቸው ነበር። "አባቴ ሰማኒያ ዓመት አልፎአቸው ከጥርሳቸው አንድ አልጎደለም" ስል ያልታደሉት እንግሊዞች ማመን አቅቷቸው ነበር። ስለዚህ የጥርስ ሐኪሙ ጉብኝት የተጠበቀው በተለየ የጉጉት ስሜት ነበር። ጉጉታቸው የሚስተር ለማን ጥርስ ሐኪሙ ከመረመረ በኋላ ምን ዓይነት ፍርድ እንደሚሰጥ ለማየት ነበር። እርግጥ ከኔ በፊት የጋናዊው የጆኒ ጋባን ጥርስ ወተትና በረዶ እንደሚመስል አይተው በመልኩ ተደንቀዋል። ጆኒ ግን እዚያ ተኝቶ በነበረበት ጊዜ የጥርስ ሐኪም የኛን አዳራሽ አልጎበኘም ነበር። ስለዚህ ስለ አፍሪቃውያን ጥርስ ጥንካሬ የማስተባበያ ዕድላቸው አሁን ነበር የመጣላቸው።

ሐኪሙ በተባለው ቀን ልክ በሰዓቱ መጣ። ወዲያው ሥራውን በቅልጥፍና ጀመረ። የእያንዳንዱን በሽተኛ አፍ እያስከፈተ፣ አንዳንዱን አአአ በል እያለ፡ አንዳንዱን በገበያ ሊሸጥ እንደቀረበ ጊኛ ፈረስ ሊንጨጨቴን እየገለጠ፡ አንዳንዱን እያስገለፈጠ፣ የጥርስ

ምርመራውን አፋጠነ። በረዳትነት የምታገለግለው ቆንጆ ነርስ እርሳሷን አሹላ የሐኪሙን ውሳኔ በቅልጥፍና በደብተሯ ላይ ታሰፍር ነበር። ለአንዳንዱ የመጉመጥመጫ መድሃኒት ይታዘዝለታል፣ ለአንዳንዱ የተነቃነቀው ጥርሱ እንዲወልቅ ይፈረድበታል፣ ለአንዳንዱ በጥርሱ ላይ የተጋገረው ጭቅቅት በስለት እንዲፋቅለት ይፈቀድለታል፣ ለአንዳንዱ የተሸረፈውና የተቸረቸፈው ጥርሱ እንዲሞረድና እንዲከረከምለት ያዛል፣ የሐኪሙ ምርመራ ከበሽተኛ እበሽተኛ፣ ከአልጋ አልጋ በዚህ አኳኋን ተራመደ።

ሐኪምና ነርስ ከኔ አልጋ ሲደርሱ በአዳራሹ ከተኙት ቀልደኞች የሳቅና የስላቅ ድምጽ አስገመገመ። የተሳሳቁበት ምክንያት፣ ሐኪሙና ቆንጆዋ ነርስ ባይገባቸውም፣ እኔ አውቀው ስለነበረ፣ እኔም ፈገግ አልኩ። መቼም መላ ሆስፒታሉ በሙሉ እንደሚያውቀው ሚስተር ለማ ባገሩ አራት ሚስት አለው፤ ግን ቢኖረውም በዚህ በእንግሊዝ አገር አንድ እንኳን ስለሌለው፣ እንደሌሎቹ በሽተኞች የሚታዘንለት ሆኗል። ግን እሱም አልሰነፈም፣ በነገሩ አስቦበት የእንግሊዝ ተወላጅ የሆነች አምስተኛ ሚስት ድኖ ከሆስፒታሉ እንደወጣ፣ በማግስቱ ለማግባት ውሳኔ አድርጓል። ለአምስተኛ ሚስትነት የታጨችው የወትሮዋ ወዳጅ ስትሆን፣ እሷ ባታውቅና ባትጠረጥርም ቅሉ ይቺ ያሁኗ ቆንጆ ነርስ ነበረች። ሰውን ያሳቀው ይህ አጋጣሚ ነበር።

አቶ ሐኪም ሆዬ እኔ ላይ ጊዜ አላጠፋም ሌንጩጩን ገለጥ አርጎ ከአየ በኋላ ነርሷ "ለሠርጀሪ" እንድትመዘግበኝ አዘዘና ወደ ጎረቤቴ ሽማግሌ አመራ። እሱም ጥርሱ ሁሉ ወልቆ ሌሊት ሲተኛ እያወለቀ ራስጌው በብርጭቆ ከድኖ በሚያኖረው አርቴፊሻል ጥርስ ስለነበር የሚገለገለው፣ በሱም ጊዜ አላጠፋም። ወዲያው ምርመራው አለቀና፣ ሐኪሙ በፈላጭ ቆራጭነት ምድረ በሽተኛ ወደሚገባበት የ"ሠርጀሪ" ክፍል ሲያመራ ለ'ሠርጀሪ" በተመዘገቡት በሽተኞች ገጽ ላይ ድንገት የታየው የሥጋትና የጭንቀት ስሜት፣ እኔንም በማላውቀው ምክንያት ጎበኘኝ። ቢሆንም፣ በኢትዮጵያዊ ጥርሴ ጠንካራነትና ጤነኝነት ፍፁም እምነት ስለነበረኝ እንደ እንግሊዞቹ አልተሸበርኩም። የገረመኝ ቢኖር ከተመዘገቡት ሁሉ በጣም የተሸበረውና የተጨነቀው፣ እንክል እንክል እያለ የሚቁነጠነጠው፣ ያ አጓጉል የተንኮል ጥያቄ እየጠየቀ ያላግጥብኝ የነበረው ሳቂታ ጎልማሳ መሆኑ ነበር።

ነገሩን ባጭሩ ለመግታት ተራዬ ደረሰና ነርሷ አልጋዬን እያሽከረከረች ወደ "ሠርጀሪው" ወሰደችኝ። ተሽከርካሪውን ከነጭነቱ ባንድ ጎን አቁማ፣ መምጣቴን ለዶክተሩ አስታወቀች። ዶክተሩ "ጥቂት ይጠብቅ ሚስተር ለማ" አለና ሌላ ሌላ ሥራ ይዞ ሲትረከረክ ጥቂት



ደቂቃዎች አሳለፈ። በዚህ ጊዜ "የሠርጀሪውን" ክፍል ተራዬን በዓይን መመርመር ስጀምር፣ ባንድ ወገን በረጅም ነጭ የብረት ኒኬል ጠረጴዛው ላይ የተደረደረውና የተሰለፈውን የመቆንጠጫ፣ የመፋቂያ፣ የመገዝገዣ፣ የመከርከሪያ፣ የመውጊያ፣ የመቁረጫ፣ የመፍጫ፣ የማውለቂያ፣ የመጠምዘዣ፣ የመክፈቻ፣ የመሰንጠቂያ፣ የመስፊያና የመሰርሰሪያ ዓይነት፣ ቅርጽና ቁጥር ብዛት ተመልክቼ ለጥርስ ሐኪሙ የነበረኝ ንቀት ቀስ በቀስ ወደ አክብሮት፣ ከዚያም ወደ ፍርሃት ተሸጋገረ። በዚህ ላይ ሳለሁ ሐኪሙ "ሚስተር ለማን አቅርቡልኝ" በማለት ነርሷን አዘዘና አቀረበችለት። እሱም ቀደም ብሎ የጀመረውን የጥርስ ምርመራ ሊቀጥል ሲዘጋጅ ነርሷ "ከዚህ በኋላ ይፈልጉኛል ዶክተር?" አለችው።

"ለጊዜው አልፈልግሽም፣ ስጨርስ እጠራሻለሁ" አላት። ነርሷ በሩን ዘግታ ወጣች።

እውነተኛው የጥርስ ምርመራ ተጀመረ። እኔም ግን ዓይኔ ያረፈው እፊቴ እተደረደረው ጉጠትና መጣሪያ ላይ ስለነበር ስለጥርሴ የምናገረውን እምብዛም አላሰብኩበትም።

"ስላንተ ስለስራህ አንዳንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እስቲ" አለ ሐኪሙ ጥርሶቼን እየፋፋቀ፣ እየጠራረገ። "አፍሪቃዊ ነህ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነህ፣ ግን ገና በክርስቶስ አልተጠመቅህም። ይኸን ሁሉ ዝናህን በሙሉ ሰምቻለሁ። እንዲያውም ዛሬ ከራስጌህ ካሉት መጻሕፍት ውስጥ የካርል ማርክስን 'ካፒታል' አይቻለሁ። መጽሐፉን ትወደዋለህ?" አለኝና ጥርሴን መፈቅፈቁን አቆመ። ማርክስ በአስተሣሰቡ "ሃይማኖት የሕዝብ አብሾ ነው" እንደሚል ስለማውቅ፣ ይኸን "ጀስዊት" የጥርስ ሐኪም እንዳላበሳጭና በእልህ ወይም የእግዚአብሔርን ብርሃን በኃይል በኔ ባረመኔው ጭንቅላት ውስጥ ለማብራት ዓይኔን ለመግለጥ ብሎ ደህናውን ጥርሴን ያለማደንዘዣ እንዳያወልቅብኝ ብርቱ ስጋት ያዘኝ። ስለዚህ መልሴን በታላቅ ጥንቃቄ መመለስ ነበረብኝ። "የማርክስን መጽሐፍ የማነበው ኢኮኖሚክስ ስለምማርና ማንበቡ ግዴታ ስለሆነ፣ በፈተና ጊዜ ጥያቄ የሚጠየቅበት በመሆኑ ብቻ ነው እንጂ ሐሳቡን ስለምወደው አይደለም፣" አልኩት። ምን ይደረግ?

"ስለምንድነው ሐሳቡን የማትወደው?" አለኝ ጥርሴን እየጎረጎረ።

"ሃይማኖትን ስለሚቃወም ነው። ማርክስ በአማልክት አያምንም፣ የሚያምኑትንም ይቃወማል፣" አልኩት።

"ይህ እርግጥ ነው፣ ግን አንተ ሃይማኖት የለህ፤ አንተን እንዴት ይቃወምሃል?" አለ።

"ዶክተር እዚህ ላይ ተሳስተዋል። በርግጥ ሃይማኖት አለኝ፤ እንደርስዎ ፕሮቴስታንት ወይም ካቶሊክ ባልሆንም፤ እናንተ በሶስት አምላክ እንደምታምኑት እኛም ባገራችን በብዙ አማልክት እናምናለን፣ እናመልካለን። ከማርክስ የሚያጣላኝ፣ ይህ ሃይማኖት ጥሩ ነው፣ ይኸ መጥፎ ነው፣ ይኸ እውነት ይኸ ሐሰት ነው፣ ይኸ ለሰው ይጠቅማል፣ ይኸ ይጎዳል ሳይል እንዲያው በደፈናው፣ 'ሃይማኖት በተባለ ሁሉም ሕዝብን ማስከሪያና ማደንዘዣ አብሾ ነው 'በማለቱ ነው፣ " አልኩኝ በጋለ ስሜት።

"መቼም እንዳንተ ያለ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ክርስቲያን ባይሆንም፣ የክርስትናን ትምህርት ማወቁ፣ መስማቱ አይቀርምና ተጠምቄ ክርስቲያን ልሁን ብትል ለምሳሌ፣ ከካቶሊክና ከፕሮቴስታንቶች እምነት የቱን ትመርጣለህ?"አለኝ።

"አአአሃ ሃሃ ... " አልኩ።

"መልስህን አሁን ልትነግረኝ አትችል እንደሁ ንገረኝ አልልህም። ብቻ አስብበት፣ ደህና አርገህ አስብበት። ይኸ ቀላል ጥያቄ እንዳይመስልህ። ሚስተር ለማ ከባድ ጥያቄ ነው፣ በጣም ከባድ። ጊዜ አለህና ዛሬ ባይሆንልህ ነገ ትነግረኛለህ፣ " አለ።

እኔም በክፍት አፍንቴ ምራቄን እንደ ሕፃንነቴ እያዝረበረብኩ ዓመት ሙሉ የቆየሁ መሰለኝ። በመጨረሻ ሐኪሙ እንደገና መዘውሩን ዘውሮ ቀለበቷን ይሁን ዘለበቷን ካፌ አወጣልኝ። ምራቄን በማምጠጫ ጠራረገልኝ፣ መጉመጥመጫ መድሃኒት መሳይ አስጎነጨኝ፣ ነፍሴ መለስ አለች። ፍራት ግን ገና ጥሎኝ አልሄደም።

"ታዲያስ ሚስተር ለማ፣ ጥያቄዬ ገብቶሃል ወይስ ልድገምልህ? "አለኝ የጥርስ ሐኪሙ።

"ገብቶኛል፣ በፍጹም ገብቶኛል ዶክተር፣ " አልኩ። ምላሴን እያፍታታሁ።

"ታዲያስ?" አለ ሐኪሙ ታላቁን ጉጠት አንዴዬ በቀኝ፣ አንድዬ በግራ እጅ እያዘዋወረ። በስለት ሲጫወት እኔም የምሰጠውን መልስ በጥንቃቄ አዘጋጀሁት።



"እርግጥ ዶክተር እንዳሉት፣ ምንም እንኳ ክርስቲያን ባልሆንና ባልጠመቅ ስለክርስትና ሃይማኖት ጥቂት ጥቂት ሰምቻለሁ፣ ግን አውቃለሁ አልልም። እውቀቴ በጣም ትንሽ ነው፣ "አልኩ።

"በጀ... "አለ ዶክተሩ፣ " ቀጥል..."

"ስለ ክርስትና ያለኝ እውቀት ገና የጀማሪ፣ የተመሪማሪ ስለሆነ የምሰጥዎ መልስ ምናልባት ስህተት ያለበት ቢሆን ዶክተር እንዳይቀየሙኝ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ።" አልኩት፣ የያዘውን ጉጠት አስፈሪነት ሳልዘነጋ።

"የምን መቀየም ነው!? መቀየም የሚባል ነገር እዚህ መነሳት የለበትም። እኔና አንተ አሁን የያዝነው የሁለት ወዳጆች ጭውውት ነው፣ ሌላ ምንም ነገር የለበትም" አለ፣ የራሱን አርቴፊሻል ጥርስ ብልጭ አድርጎ።

"ካልተቀየሙኝ እንግዲያ፣ 'አሁን ምረጥ፣ የትኛውን ትይዛለህ?' ብለዋል። ከካቶሊኮች ሃይማኖትና ከፕሮቴስታንቶች ሃይማኖት የቱን እመርጣለሁ? አስቸጋሪ ነገር ነው። ቀልቀሎና ስልቻ..." አልኩ ሳንገራግር፣ እንዲያው ለወጉ፣ ዞሮ ዞሮ ግን አሸናፊው ባለ ጉጠቱ ዶክተር መሆኑን አውቄዋለሁ።

"ምኑ ነው የሚያስቸግረው?" አለ ዶክተሩ ግምባሩን ቋጠር አድርጎ ጋል በማለት።

"በሁለቱ መሀከል ያለው ልዩነት እንደ ቀትር ፀሐይና እንደ ውድቅት ጨለማ ግልጥ ያለ ነው። እንደ ነጭ ቀለምና እንደ ጥቁር ቀለም፣ እንደ እውነትና እንደ ሐሰት!" በሁለቱ መሀከል ያለው ልዩነት በፍጹም አይታየኝም አላልኩም። ይህ አልወጣኝም። ለምሳሌ አንድ ጉልህ የሆነ ልዩነት፣ ለክርስቶስ እናት ሁለቱ ያላቸው አስተያየት መሆኑ ግልጽ ነው። ካቶሊኮቹ የአምላካቸውን አባቱንም እናቱንም ያከብራሉ፣ ፕሮቴስታንቶቹ ግን አባቱን አክብረው እናቱን ችል እንደማለት የሚሉ ይመስለኛል። "ባልሳሳት ዶክተሩ ፊቱ እንዲያ ሲፈካ አላየሁም፣ አርቲፊሻል ጥርሱ በፈገግታው ተብለጨለጨ።

"አግኝተኸዋል ሚስተር ለማ! አንተ እንኳን አፍሪቃዊው አግኝተኸዋል!" አለ በደስታ። "ታዲያ ሚስተር ለማ፣ ታዲያ ላንተ መጽሐፍ ቅዱስን፣ ብሉይና ሐዲስን ላልመረመርከው ንጹህ አፍሪቃዊ፣ ላንተ የትኛው ትክክል ይመስልሃል? ንገረኝ፣ አትፍራ"

እዚህ ላይ አባቴ ራሳቸው በእጃቸው ሲፈርሙ የሚጽፉት፣ በማህተማቸው ላይም ያስቀረጹት ስማቸው" አለቃ ለማ ኃ.ወ.ታ" መሆኑ በድንገት ከዚህ መጣ ሳልለው ትዝ አለኝ። አለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ ማለት ነው። ኃይሉ የአባታቸው፣ ታሪክ የእናታቸው ስም ነው። "ወልደ" የእከሌ ወይም የእንትና ልጅ ማለት ነው። ስለዚህ "አለቃ ለማ ኃይሉ፣ የታሪክ ልጅ "ማለት ነው። ይህም እናታቸውን ወይዘሮ ታሪክን ምን ያህል እንደሚያከብሩና እንደሚያፈቅሩ ነው የሚያስረዳው። ሲፈርም የአባቱንም የእናቱንም ስም የሚጽፍ ሌላ ሰው ከሳቸው በቀር አይቼም ሰምቼም አላውቅ። ይህንን ጉዳይ በማሰላሰል ተመስጬ ሳለ፣ ዶክተሩ አባነነኝ።

"ታዲያስ ሚስተር ለማ?" አለኝ በፈገግታ።

"ጊዜዎን አላባክን እንደሆነ አንዲት ታሪክ ልንገርዎ" አልኩኝ። "ነገሩ ግልጽ ነው ዶክተር" አልኩ ነቃ ብዬ። "በኔ አስተያየት ፕሮቴስታንቶች ናቸው ወንጀለኞች። ካቶሊኮቹ አልተሳሳቱም። አባትን አክብረው እናትን አያዋርዱም። ይኸው በኛም አገር ባህል ተደንግጓል። ከጥንት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሃይማኖት ትዕዛዝ 'አክብር እባከ ወአማከ" ይላል፣ ግእዝ በሚባለው በጥንታዊ ቋንቋችን። ይኸ ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጉም" ለአባትህና ለእናትህ ከበሬታህን አድርግ ማለት ነው" አልኩ። ሐኪሙ ይህን ሲሰማ ፍንጥዝጥዝ አለ፤ የሚሆነውን የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጣ። የጨበጠውን ታላቅ የጥርስ መፈንቀያ ጉጠት አስቀመጠና እጄን ጨብጦ ሲወዘውዘኝ፣ አንጀቱ ርሶ ከመርካቱ የተነሳ ደስታው ጉሮሮውን አንቅቶ ካፉ ሳይወጣ ብዙ ጊዜ የቆየ መሰለኝ። በመካያው፣ በጥልቅ ስሜት በጎረነነ ድምጽ፣

"ሚስተር ለማ፣ ጥሩ ጥርሶች አሉህ... በፍጹም ጤናማ የሆኑ ጠንካራና ወተት የመሰሉ ናቸው...!" አለና መጥሪያውን ጫን ሲያደርገው የኤሌትሪክ ደወል ድምጽ ተሰማ። ነርሷ ከተፍ አለች በችኮላ።

"ነርስ፣ "አለ ሐኪሙ።" ሚስተር ለማን አሁን ልትወስጂው ትችያለሽ። ጥርሶቹን በመፋቂያ ፍቁለታለሁ፣ በቡርሽ ቦርሼለታለሁ፣ ሌላ ምንም ዓይነት ሕክምና አላስፈለገውም። ጥሩ በ[illegible]ም ጥሩ ጥርስ ነው ያለው፣" አላት። ነርሷ አልጋዬን እየነዳች ከሕክምናው ክፍል ስታወጣኝ "ደህና ይሁኑ" ዶክተር እንደማለት እጄን አውለበለብኩለት።



"ጉድ ባይ ሚስተር ለማ፣ የተነጋገርነውን አትርሣ። ደህና አዝማያሚያ ይዘሃል፣ ቀጥልበት" አለኝ። በዚሁ ተለያየን። እኔም ጥርሴን ከመውለቅ አድኜ ወደ መኝታ አዳራሽ በሰላም በመመለስ "አማልክቶቼን" አመሰገንኩ። ባልደረቦቼ ላቀረቡት ጥያቄ ሁሉ መልሱን ነርሷ ሰጠችልኝ።

## ለ

የሃይማኖት ሰባክያን ሆስፒታልን የሚያዘወትሩት በምን ምክንያት እንደሆነ ከጥርስ ሐኪሙ በኋላ ነው የተገለጠልኝ። በነሱ አስተሳሰብ የዓለም ሰው ወደ እግዚአብሔርና ወደ ሃይማኖት ሕሊናውን የሚመልሰው በህመም በተዳከመበት፣ ሆስፒታል ተኝቶ የሞትን ነገር በሚያስብበት ጊዜ ነው። ያን ጊዜ ነው ካቶሊኩም፣ ፕሮቴስታንቱም፣ ጴንጤውም ጆሆቫዊትነሱም፣ ሌላውም፣ ሌላውም ያን የፈረደበት በሽተኛ ወደየራሱ ሃይማኖት ለመሳብ የሚራወጠው። እኔማ የአረመኔነት ዝናዬ በሞላው ሆስፒታል የገነነ አፍሪቃዊ በመሆኔ ሊያሳምነኝና ለየራሱ በቀዳው የዮርዳኖስ መንፈሳዊ ውሀ ሊያጠምቀኝ የሞከረው ብዙ ነው። በዚሁ መሠረት የጆቫዊትነስ ሃይማኖት ተከታይ ከሆኑትም አንዱ እኔን ሊጠይቅ ከለንደን ድረስ መጥቶ ነበር። የሱ ግን አቀራረቡ ከፕሮቴስታንቱም ከጆሲዊቱም በፍጹም የተለየ ነበር።

ሰውየው አጠር፣ ወፈር ያለ፣ ድቡልቡል መሳይ፣ የራሱ ፀጉር አናቱ ላይ የሳሳና እመመለጥ አፋፍ የደረሰ ነበር። እድሜው ቢበዛ አርባ ቢሆን ነው። ከመኝታ አዳራሽ ጎረቤቶቼ የእንግሊዝ የሠራተኛ መደብ አባሎች የሚለየው ባርኔጣ በማድረጉ፣ በመጽሀፍቱና በልብሱ ነበር። አለዚያ፣ ሁሉም የሚያውቁት፣ አንዳንዶቹም አላጋጮቹ በወዳጅነት የሚቀልዱበት መሆኑን አንድ እሁድ ቀን በበሽተኛ መጠየቂያ ሰዓት ገና በሩን ሲገባ ነበር የተገነዘብኩት። ሰውዬው እንደሱው ደምቦጭ ያለ የቆዳ የእጅ ሻንጣ ይዟል፣ ፊቱ በላብና በፈገግታ ያብለጨልጫል። ወደ መኝታ አዳራሻችን እንደገባ ለበሽተኞቹ የያዘውን ፍራፍሬ ማደል ጀመረ። የኔም ተራ ሲደርስ፣

"ሚስተር ለማ፣ ከፍሬው ተጋግዘን...." አለና አንዱን ሙዝ በፈገግታ አበረከተልኝ። እኔ ግን የሰውየው አኳኋን ባጠቃላይ ያልተለመደ አዲስ ነገር ስለሆነብኝና ከማውቀውም የእንግሊዞች ጠባይ በጣም የተለየ ስለሆነብኝ ገጸ በረከቱን፣ መተያያውን ለመቀበል አመነታሁኝ። ጎረቤቴ ሽማግሌው አይሪሽና በቀኝ የተኛው ረጅሙ ግንበኛ መቸገሬን አይተው" ግድ የለም ሚስተር ለማ፣ ጠያቂህን እናውቀዋለን፣ ለክፋት አይደለም፣ ተቀበል" አሉኝ። ቀጥለውም እነሱም በአዲስ ገብነታቸው ጊዜ ከዚሁ ገባሬ ሠናያት እጅ ብዙ ሙዝና ብዙ ብርቱካን፣ ጥሩ ጥሩ ኬክ እንኳን ሳይቀር የተቀበሉ መሆናቸውን ገለጹልኝና ነገሩ እየከበደኝ ሰውየውን አላስቀይም ብዬ ስፈራ ስቸር ተቀበልኩ።



"ሚስተር ሮጀርስ ለአዲስ ገቦች በጣም ለጋስ ነው። ብቻ የሱ ችግር ቢራ አምጣልን ሲሉት እሺ አይልም፣ የቡርቱካን ጭማቂ ይዞ ይመጣል..." አለ ግንበኛው ጎረቤቴ።

"ቢራ ሆነ ማናቸውም የአልኮል መጠጥ በዚህ ሆስፒታል በፍጹም ክልክል መሆኑን አሳምረህ ታውቃለህ "አለና ሚስተር ሮጀርስ መጽሐፉን በቀለጠፈ ጣት ገለጥ በማድረግ፣ "ይኸውልህ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ስለስካር የሚለውን ሰምተሃል፣ አፍህን ያዝ። አለ ሚስተር ሮጀርስ። በዚህም ላይ ጉዳዩ ለአንተ አይደለም። ቃለ እግዚአብሔር ለማይገባው፣ ለሚስተር ለማ ነው" አለ እንደ ማምረር ብሎ። ግንበኛው መልስ አልሰጠውም፣ እንዲያው ብቻ በዝምታ በሳቅ ተንፈራፈረ። ይህ እኔን አስገረመኝ። ቢሆንም ሙዙን ብቀበል እንኳ፣ ተቀብዬ ከራስጌዬ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥኩት ላጥ በማድረግ እንደ እንቁልልጮ አሽሞንሙኖ ሊያጎርሰኝ ከመቀመጫው ብድግ ባለ ጊዜ፣ በሳቅ የተንከተከተው ግንበኛው ብቻ ሳይሆን ሽማግሌውም አይሪሽ ነበር። ሁኔታው አጉል ማፈሪያ ነገር መሳይ ስለሆነብኝ ጨነቀኝና ግራና ቀኝ ጎረቤቶቼን አየኋቸው።

"ተቀበል!" አለኝ ሽማግሌው።" ሞኝ አትሁን እዝጌር የላከልህን..." አለና ሳቀ። ምን ላድርግ? ጉርሻውን በአፌ ሳይሆን በእጄ ተቀበልኩና፣ እንዳመጣብኝ እገምጥ ጀመር። ሚስተር ሮጀርስን ግን በአንድ ሙዝ አልተገላገልኩትም። ሙዙን ስበላ ሳለሁ ብርቱካን ደሞ ላጠና ራስጌዬ ካለው ሳህን አደረገልኝ።

"እንዳንተ የአጥንት 'ቲቢ' ላመመው ሰው ዋናው መድሃኒቱ ፍሬ ነው። ፍሬ፣ ንጹህ አየርና፣ የጸሐይ ብርሃን ደግሞ ይኸን ሁሉ እግዜር ነው የፈጠረው። ሐኪሞቹ የሚወጉህ መርፌና የሚግቱህ መድኃኒት ፋይዳ የለውም፣ ሰው ሰራሽ ነው። ለሰው ልጅ ዘላቂውና መድኃኒቱ የሚሰጠው፣ ከሥነ ፍጥረት የሚገኘው ነው። ይህን አትጠራጠር" አለኝ።

ምን ላድርግ? ምን መልስ ልስጠው? የሰውየውን ልክ ገና አላወቅሁትምና፣ አጉል ነገር ተናግሬ ሰው እንዳላስቀይም የላጠልኝንና የፈለቀቀልኝን ብርቱካን በዝምታ እጋበዝ ጀመር። ሚስተር ሮጀርስ ያመጣልኝን ገጸ በረከት በመመገቤ የተሰማው ደስታ በፊቱ ላይ ተጽፎ ይነበብ ነበር። ግን ወደመጣበት ፍሬ ነገር ወዲያውኑ አልገሰገሰም። ቡርቱካኑን እስክጨርስ ታገሠ፣ በልቼ ስጨርስ "ሌላ ድገም" አለኝ። "ለጊዜው ይበቃኛል አመሠግናለሁ" አልኩት።

"እንግዲያ አንዳንድ ቁም ነገር ብንጨዋወትስ? ምን ይመስለሃል ሚስተር ማንጀስቱ ለማ?አለ። "ለምሳሌ ይኼን የያዝኩትን መጽሐፍ አይተሃል?" አለና መጽሐፉን ከመጀመሪያው ላይ ገልጦ ቀረብ አድርጎ አሳየኝ። በእንግሊዝኛ "ዘሆሊ ባይብል"/መጽሐፍ ቅዱስ/ የሚል ጽሁፍ አየሁ።

"ምንድነው? ስለምንድን ነው የሚያወራው?" አልኩት።

"ምን?! ምን አልክ ሚስተር ለማ?!" አለ ሮጀርስ፣ በመገረም፣ በመደነቅና በመደሰትም ጭምር- ፊቱ እንደፈንዲሻ ማሽላ ቆሎ ፈክቶ።

"ዛሬ ቀንቶሃል" አለው ግንበኛው ጎረቤቴ። "ሚስተር ለማ ዛፍና ቋጥኝ፣ ወንዝና ተራራ የሚያመልክ እልም ያለው አረመኔ ነው። እንደኛ አይደለም። አራት ሚስት አለው!" አለና ሳቅ አለ።

"አዎ፣ እንደናንተ በስም ብቻ ክርስቲያን ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስን ከተወለደ ገልጦ ከማያውቅ፣ እንደ ሚስተር ለማ ፈጽሞ ቸሩን ወሬ ያልሰማው መቶ ጊዜ ይሻላል፣ " አለ ሮጀርስ በጠንካራ ስሜት። ወዲያው ግን ፊቱን ወደኔ መለስ አደረገና፣ "ብቻ ሚስተር ለማ፣ አንድ ያልገባኝ ነገር አለ... እርግጥ ስለ አማልክቶችህና ስለ አራቱ ሚስቶችህ በሆስፒታሉ በሙሉ የገነነውን ዝናህን እኔም ሰምቻለሁ... ብቻ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆነህ ሌላው ቢቀር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ጥቂት እንኳን ሳታውቅ፣ ሳትሰማ ትቀራለህ?" አለኝ።

"ወሬውን ዝናውን ሰምቻለሁ፣ ግን እሱን ለማንበቢያ ጊዜ የለኝም። በዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮቹ አንብቡ ብለው በሚሰጡን የመጽሐፍ ዝርዝር ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የለም። ያለው የቤነሃም 'ኤኮኖሚክስ'፣ የላስኪግራማር' አፍፖሊትክስ'፣ የማርክስ'ካፒታል'፣ የፕሌቶ' ሪፐብሊክ'፣ የአንሰበርግ' ሶሲዎሎጂ'፣ የወድስዎርዝ' ሣይኮሎጂ... 'ነው። በፈተና ጊዜ ጥያቄ የሚጠይቁትም እነዚህን በመሳሰሉት መጽሐፍት ነው። ምን ላድርግ?" አልኩት።

"ይገባኛል፣ እናም ባንተ አይፈረድም..." አለ በቁም ነገር ራሱን እያወዛወዘ። "ባንተ አይፈረድም፣ በዩኒቬርሲቲው፣ በአምላክ የለሹ የምእራብ ሥልጣኔያችን ነው" አለ።

—.

"መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ ከዚያ እየጠቀሰ ሲናገር የሰማሁት አልፎ አልፎ እሁድ እሁድ እየመጣ የሚሰብከውን የ' ቸርች ኦፍ ኢንግላንድ'



ቄስ ብቻ ነው። የጥርስ ሐኪሙ ጀስዊት እንኳን እንዲያው ያለ መጽሐፍ ነው በቃሉ የሚቀባጥረው..." አልኩ።

"እነሱ? እነሱን አትስማቸው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚነግዱ ናቸው። እምነታቸው በፍጹም በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈው- በጥቁር ቀለም በነጭ ወረቀት ላይ ሰፍሮ በጉልህ ቁልጭ ብሎ ከሚታየው የእግዚአብሔር ቃል በፍጹም የተለያዩ ናቸው። "አለ በብርቱ ስሜት። "ዓይን አላቸው አያዩም፣ ጆሮ አላቸው አይሰሙም። "ሽማግሌው ጎረቤቴ ይህንሲሰማ አላስቻለውም።

"አዎ፣ " አለ። "አዎ፣ ትክክለኛውና እውነተኛው ሃይማኖት ያንተ ብቻ ነው። የ' ጆሆቫዊትኔስ' - የወፈፌዎች ሃይማኖት! ቄስ ዲያቆን የሌለው፣ ጳጳስ ሊቀ ጳጳስ የሌለው፣ ቤተ ክርስቲያን የሌለው፣ አለቃና ታዛዥ፣ መሪና ተመሪ የሌለው፣ ሁሉ ቄስ፣ ጳጳስ የሆነበት!"

"ሽማግሌ፣ አፍህን ያዝ!" አለ ሚስተር ሮጀርስ። "ንግግሬ ከሚስተር ሜንጀስቱ ለማ ነው። እንዳንተ ያሉት ከእግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገቡ በትንቢተ ዳንኤል ተጽፏል፣ "አለና ቦታውን ለማግኘት መጽሐፉን መገላለጥ ያዘ ግን ወዲያው አጠፋው። "ከነዚህ ጋር መነታረክ ትርፍ የለውም ሚስተር ለማ፣ ተዋቸው፣ አትስማቸው። አንተ ግን በርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ በጥቁርና በነጭ የተፃፈውን ከተገነዘብክ የማትጸድቅበት፣ ማለት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የማትገባበት ምንም ምክንያት የለም። እግዚአብሔር ሂትለር ወይም ሙሶሎኒ አይደለም፣ ናዚስት ወይም ፋሺስት አይደለም፣ በሱ ዘንድ የዘርና የቀለም ልዩነት የለም" አለ።

"ስንት ሰው ይጸድቃል? ንገረው ለሚስተር ለማ። በል፣ ንገረው!" አለ ሽማግሌው በማላገጥ። "ሠላሳ ሺህ ሰው ብቻ ነው በናንተ ቤት የሚጸድቀው... ሰላሳ ሺ!" ሮጀርስ ሽማግሌውን አየት አደረገና እሱን ትቶ ነገሩን ወደኔ መለሰ።

"የሚጸድቀው ሰው ቁጥር ሠላሳ ሺ ብቻ ለመሆኑ ማስረጃው በዳንኤል፣ ደሞም በራእይ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ቁልጭ ብሎ ተጽፏል። ብቻ የተፃፈው በራእያዊ ምሳሌ ስለሆነ እውነተኛ ትርጓሜው የሚገለጽላቸው ጥቂት ብቻ ናቸው። ለሌሎቹ ጥቅጥቅ ጨለማ ነው የሚሆንባቸው፣ ይህ በነቢዩ ኢሳያስ የተነገረ ነው። የራእዩ ምሳሌ ትርጉም የተገለጸው በ 1979 ዓ.ም. ለራሚልና ለረተርፎርድ ነው።

እነሱም 'የጀሆቫ ዊትነስ' ሃይማኖት መሥራቾች ናቸው። "አለና ስለ አዲሱሃይማኖት በሰፊው ሲያስረዳኝ ቆይቼ፣ በመጨረሻ በአርማጌዶን ጦርነት ደመደመ። እሱ እንደሚለው የአርማጌዶን ጦርነት ጀሆቫ በተባለው በፈጣሪና በሠራዊቱ፣ እንዲሁም በሰይጣንና በሠራዊቱ መሀከል የሚደረግ ታላቅ እልቂት የሚያስከትል የጦርነት ሁሉ መጨረሻ ጦርነት ነው። ከዚህ ጦርነት በኋላ፣ ይህች አለም ስለምታልፍ ሌላ ጦርነት አይኖርም። ስለዚህ ባንድ ወገን በናዚዎችና በፋሺስቶች፣ በሌላው ወገን በካፒታሊስቶችና በኮሙኒስቶች መሀከል የተደረገውና በቅርቡ የተፈጸመው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የጦርነት መጨረሻ አይደለም። መጨረሻው ይኸ አምላክ የለሹ ሠራዊት 'ሶስተኛው የዓለም ጦርነት' የሚለው፣ ግን በእውነት ስሙ የአርማጌዶን ጦርነት የምንለው ውጊያ ነው። በጀሆቫና በሠይጣን መሀከል የሚደረገው የአርማጌዶን ጦርነት ከዚህ በፊት በዓለም ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ጦርነት ይሆንና3 በጀሆቫህ ድል አድራጊነት ይደመደማል። ከዚያ በኋላ በጀሆቫህ መሪነት ከሠይጣን የተዋጉት የምእመናን የጦር ሠራዊቶች፣ በሕይወት ያሉት እንዳሉ፣ የሞቱት በትንሣኤ ሙታን ተነሥተው፣ በጀሆቫህ ንጉሥነት፣ በሱ መንግሥት በዚች አለም ለዘላለም ይኖራሉ። ስለዚህ ነው ጀሆቫህዊትኔሶች 'የጀሆቫህ ወታደሮች' የሚባሉት። እነሱ የሚዋጉት ለጀሆቫህ ብቻ ነው" አለና ትንፋሽ እንዲገባለት ጥቂት ቆም አለ። እኔም የሰው ሙዝና ብርቱካን እየሰለቀጥኩ፣ የሰው የቡርቱካን ጭማቂ እየጨለጥኩ፣ "እየበሉ እየጠጡ ዝም፣ የጋን ወንድም" እንዳልሆን ብዬ አንዳንድ ጥያቄ መጠየቄ አልቀረም።

"ታዲያ እንግዲህ ሌሎቹ ክርስቲያኖች እንደሚሉኝ ያለ የሰማይ ቤትና መንግሥተ ሰማያት የለም ማለት ነዋ?" አልኩት። ይኸን ሲሰማ ሚስተር ሮጀርስ ፍንጥዝጥዝ አለ።

"ልክ ነህ ሚስተር ለማ! ፍሬ ነገሩ እንዲሀ ባንድ ግዜ ይገባሃል ብዬ አልጠረጠርኩም ነበር። 'አይኪዩህ' ማለት የአእምሮ ሚዛንህ በጣም ከፍ ያለ መሆን አለበት!" አለ፣ ሁለቱን ጎረቤቶቼን በደስታና በወቀሳ ዓይን ተራ በተራ እያተኮረ እያየ። "አያችሁ? አያችሁት? ሰማችሁ ያለውን?- ምሥጢሩ ባንዳፍታ ነው የተገለጠለት... አያችሁት?!" አላቸው።

"አይተናል፣ ሰምተናል፣ ልባችንን አታውልቀው፣ አታድርቀን።" አለ ግምበኛው በንቀትና በቀልድ። ሮጀርስም እነሱን ንቆ ተወና ወደኔ ተመለሰ።



"አዎን ሚስተር ለማ፣ መንግሥተ ሰማያት የሚባል ነገር የለም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተፃፈም። ቄሶች፣ መለኩሴዎች፣ ጳጳሳትና ሊቀ ጳጳሳት ናቸው ሕዝቡን ላም አለህ በሰማይ እያሉ ለማታለያ መንግሥተ ሰማያትን በሐሰት የፈጠሩት።"

"የሰላሳ ሺዎቹ ነገር እንዴት ነው ሚስተር ሮጀርስ?" አልኩት።

"ከመመለሴ በፊት አንድ ነገር ልለምንህ" አለኝ። "ሙሉ ስሜ ጆን ሮጀርስ ነው። የቅርብ ወዳጆቼ፣ አባቴ እናቴና ሚስቴ 'ጆን' ብቻ ነው የሚሉኝ፣ 'ጆኒም ይሉኛል። ሚስተር ሮጀርስ የሚሉኝ ባእዶች ናቸው። ያገራችን የእንግሊዞች ልማድ ነው። ስለዚህ ከአንተ የተዋወቅነው ምንም እንኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ዛሬ ቢሆንም፣ ከነዚህ ሁሉ ነጮች ይበልጥ ካንተ ከጥቁር አፍሪካዊ የቀረበ የመንፈስ ግንኙነት የመሠረትኩ ነው የሚመስለኝ። ስለዚህ፣ ፈቃድህ ከሆነ፣ ከፈለግህ 'ጆን' ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ።" እኔም እያወቅሁ አላዋቂነቴን ላለማጋለጥ ስል በቀላሉ ወዲያው ተስማማሁ:-

"እሺ ምን ከፋኝ። ሮጀርስ ከምልህ ጆን ብልህ ይሻለኛል። ካልክ ይሁን፣ ለኔ ልዩነቱ ይህን ያህል አይታየኝም። ለኔ ሁለቱም ማለት 'ሚስተር ሮጀርሰ' ወይም 'ሚስተር ጆን' አንድ ነው..." አልኩ አውቄ።

"አዎ፣ ብቻ፣ በልማዳችን ሚስተር ሮጀርስ ወይም ሚስተር ጆን ሮጀርስ ይባላል እንጂ ሚስተር ጆን አይባልም... ስለዚህ ፈቃድህ ሆኖ ሚስተር የምትለዋ ቅጽል ብትቀርና እንዲያው ጆን ወይም ጆኒ ብትለኝ...?" አለ በልመና ዓይነት።

"ምን ከፋኝ?" አልኩት ደስ እንዲለው። "ግን ጆኒ ማለቱ ለጊዜው ከበድ ስለሚለኝ አንተም ፈቃድህ ሆኖ ጆን ብልህ?"

" ደስ ነው የሚለኝ! ደስታውን አልችለውም፣ ሚስተር ለማ"

" እንዲህ ከሆነማ፣ እኔንም አንተ 'ሚስተር ሌማ' ማለትህን ትተህ እንዲያው 'ሜንጀስቱ' ብትለኝ ጥሩ ይመስለኛል" አልኩት።

"በደስታ!" አለና እጄን ጨብጦ ወዘወዘው።

እዚህ ላይ የበሽተኛ ጠያቂዎች ሰዓት ስላለፈ ነርሷ "ሰዓት! ሰዓት አልቋል! .... ሰዓት ክቡራንና ክቡራት...!" እያለች ትንሽ ቃጭል እያቃጨለች አዳራሻችንን መሀል ለመሀል ሰንጥቃ ከዳር እዳር

ስላቋረጠች፣ ቤቱን የሞሉት ጠያቂዎች፣ ወዳጅ ጓደኛ፣ ዘመድ ሁላቸውም ወደ ለንደን ለመመለስ ከሕመምተኞቹ የመጨረሻ ስንብት ሲያደርጉ ቤቱ እንደ ንብ ቀፎ ያስገመግም ጀመር። ወዲያው በኔ ግራና ቀኝ… ጎረቤቶቼን ሊጠይቁ የመጡት ሁለት ሴቶች የግምቢኛው ሚስት፣ የሽማግሌው ልጅ ብድግ ብድግ አሉ። ሚስተር ሮጀርስም፣ ማለት ጆንም፣ ጊዜው እንዲህ ሳይታወቀን ፈጥኖ በማለፉ እንደ መጸጸት እያለ፣ ሊሄድ ተነሣ።

"በል እንግዲህ ወዳጄ ማንጂስቱ እኔም ልሂድ… ቤቴ ከሎንደን አንድ ሰዓት ያስኬዳል መጀመሪያ ለንደን፣ ቀጥሎ እቤቴ፣ ረጅም ጉዞ ይጠብቀኛል። የሠላሳ ሺዎቹን ጥያቄ ሳምንት ስመጣ አስረዳሀለሁ…" አለና እጄን ጨብጦ ጉድ ባይ አለኝ።

"ጉድ ባይ ጆን… አልኩት።



## ሐ

በተለያየን በሳምንቱ እሁድ በበሽተኛ መጠየቂያው ጊዜ ሚስተር ሮጀርስ ሙዝና ብርቱካን ታቅፎ መጥቶ ከሁለቱም ከለገሠን በኋላ፣ አጠገቤ ቁጭ አለ። "ጊዜ የለኝም ዛሬ" አለ። "እዚሁ ሆስፒታል ያሉ ሌሎች የምጠይቃቸው አሉኝና ወደነሱ መሄድ አለብኝ "አለ። ከመሄዱ በፊት ግን ስለ 36,000ው ጻድቃን ባጭሩ አስረዳቶኝ፣ ዝርዝሩን የሚያስረዱ ሶስት መጠነኛ መጻሕፍት ሰጠኝ። የፃድቃኑ ነገር በወንጌል የመንግሥት ሰማያት በር ጠባብ ስለሆነች፣ ብዙዎቹ ይፈልጓታል፣ ይመኟታል፣ የሚገቡባት ግን ጥቂት ናቸው። በሚለው ላይ የተመሠረተ መሰለኝ። ግን ሮጀርስ ከዚሁ አያይዞ "በክርስቶስ ዳግመኛ መምጫ ጊዜ ዓለም ያልፉል፣ ማለት በዓለም የሚገኘው ሰው ሁሉ ያልቃል፣ ግን 33,000 ብቻ ይተርፋሉ። ክርስቶስ እነሱን ብቻ ይዞ መንግሥቱን በዚሁ ዓለም እንደገና ይመሠርትና ከነዚሁ ጋር ለዘለዓለም ይነግሣል። ከነዚህ የሚጸድቁት አንዱ ለመሆን፣ የዓለም ማለፊያው ጊዜ ስለተቃረበ፣ ይኸውም ሁሉ በዳንኤል ትንቢት በልዩ ልዩ ምእራፎችና ቁጥሮች ስለተላለፈ- የጅሆቫህ ዊትነስን ሃይማኖት መያዝ ነው መድሃኒቱ። ዓለም የሚያልፈውም በእቶም ቦምብ በሶስተኛው የዓለም ጦርነት ነው። ይኸውም በትንቢተ ዳንኤል ቁልጭ ብሎ ተጽፏል። ዓለም ሊያልፍ የቀረው ሶስት ዓመት ብቻ ነው። ስለዚህ በርትቶ እውነተኛውን ሃይማኖት መጨበጥ ነው" አለኝ ሮጀርስ። እኔም የሰው ሙዝና ብርቱካን እየገመጥኩ ተጠራጣሪ መስዬ መታየት ውለታቢስነት ስለመሰለኝ፣ ሮጀርስን ስለአሰበልኝ አመሰግኜ ያመጣቸውን መጽሐፍት በጥንቃቄ እንደማነባቸው ቃል ገብቼ ስንሰነባባት ነርሷ ስትጣደፍ መጣች። እንደመደነገጥ ያለች ይመስላል። ያ ፈረንጅ ጉንጭዋ ከንጣት ወደ ሳምባ ቅላት ያዘነበለ መስሎ ታየኝ።

"ሚስተር ሮጀርስ፣ ያንተ የሃይማኖት ስብከት ለሌላ ጊዜ ይሁን። ሚስተር ለማ አሁን ሌሎች ጠያቂዎች ስለመጡበት፣ ወንበሩን ልቀቅ" አለችው ከፌዝ በተቀላቀለ ንቀት። ሮጀርስም ሳይከራከር ብድግ አለ። "አንቺም ባትይኝ እኔም መሄዴ ነበር! ሚስተር ለማ አንተ ግን እነዚህ ነጮቹ የሚሉትን አትስማ፣ እነሱ በዳግማዊ ምጸአት ጊዜ ሞተው ከማይነሱት መሀከል ናቸው። ይኸም በትንቢተ ዳንኤል ቁልጭ ብሎ ተጽፏል። አንተ ግን በርታ፣ ተስፋ አለህ።"

የሚስተር ሮጀርስ አቀራረብ ልዩ ነው። እሱ በወዳጅነት፣ በመቀራረብ፣ በሙዝና በብርቱካን በማባበል ነበር የጆሆቫዊትነስ ተከታይ ሊያረገኝ የሚሞክረው። እኔም የሱን አቀራረብ የመረጥኩበት ሌላ ምሥጢር አልነበረውም። በዚያን ጊዜ በእንግሊዝ ሆስፒታሎች

ለህሙማን የሚቀርበው ምግብ እንደኔ ላለው ኢትዮጵያዊ አይዋጥም ነበር። ብበላውም ላመል አልፎ አልፎ ነበረ። ስለዚህ የሮጀርስ ሙዝና ብርቱካን እንዲሁም ደረቅ አይብ ደህና ለውጥ ሆኖልኝ ነበረ። ስለዚህ የሮጀርስ ጠያቂነት እንዳይቋረጥብኝ ለማድረግ በልቤ ቆርጬ ነበር። ለዚህ መቼም ዋናው ዘዴ ፍጹም አረመኔነቴን አለመልቀቅ፣ ግን አልፎ አልፎ አንዳንድ የሃይማኖት ጥያቄ፣ ምንም እንደማያውቅ ምንም እንዳልተማረ መጠየቅ ነው። ጥያቄው ግን መልስ ሰጪውን በሙሉ የሚያደናግር ወይም የሚያስቆጣ፣ ወይ የሚያስቀይም ሳይሆን፣ መልሱ በቀላል እንዲገኝ አድርጎ አመቻችቶ ማቅረብ መሆኑ ተገልጦልኛል።

"በል ለጊዜው ደህና ሁን፣ እስከ ሳምንት "ብሎኝ የሙዝና የብርቱካን ቦርሳውን ይዞ ውልቅ አለ።

"እሱን ተወው" አለችኝ ነርሷ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ። "ይልቁን ቸር ወሬ፣ እንኳን ደስ ያለህ! አራቱ ሚስቶችህ ሊጠይቁህ መጥተው እውጭ ተራቸውን ይጠብቃሉ። እኔም ገና ሲያቸው እነሱ መሆናቸውን አውቄ ስሮጥ መጣሁ።"

"ምን?!" አልኩ። "የምን ሚስት?" እንደመደንገጥ ብዬ ስለነበር አራት ሚስት እንዳለኝ ለጊዜው ረስቼው ነበር።

"የምን ሚስት?! ያንተው ናቸዋ። ያውም ቆንጆ ቆንጆ ልጆች! አራቱንም በተርታ ባንድ ረጅም ወንበር ላይ አስቀምጫቸዋለሁ። 'ሚስተር ለማ አይደለም?' አልኳቸው አራቱም ባንድ ቃል 'አዎ' አሉኝ። አራቱ ሚስቶችህ መሆናቸው ወዲያው ገባኝና 'ልንገረው' ብዬ መጣሁ። ከብዙ ጊዜ መለያየት በኋላ እንዲህ በድንገት ሲመጡልህ እንዳትደነግጥ ቀድሜ ላስጠንቅቅህ ብዬ ነው" አለች። ይህን ንግግር ለካ እጎንና ጎኔ ያሉት ጎረቤቶቼ- ሽማግሌው አይሪሽና ረጅሙ ግንበኛ ሰምተውት ኖሯል። "እንኳን ደስ ያለህ፣ ሚስተር ለማ" አለኝ ሽማግሌው በመገረም አይኑን አጉርጦ። ግንበኛው ግን የስሜቱን መገንፈል ማስታገስ አቅቶት፣ "ስሙ ሁላችሁም! "አለ ጮክ ብሎ። "ሚስተር ለማን እንኳን ደስ ያለህ በሉት - አራት ሚስቶቹ እዚህ መጥተዋል"

ይህን ሲሰሙ በሽተኞቹም ጠያቂዎቻቸውም በድንጋጤ ኩም ሲሉ ቤቱ ጭጭ እርጭ አለ። ጥቂት ቆይቶ ንግግር ተጀመረ፣ ግን በሹክሹክታ ብቻ ስለነበረ፣ ከዚያ በፊት ያልተለመደ ነገር ሆነብኝ።



ነርሷ ግን፣ በትምህርቷና በአሰለጣጠኗ ሞትን ያህል አስፈሪና አስደንጋጭ ነገር ገጽ ለገጽ የማየት ችሎታ ያላት በመሆኗ፣ በዚህ በድንገተኛ ዱብዳ ነገር ሳትሸበር ቃሏን ከፍ አርጋ በሽተኞቹን አስጠነቀቀቻቸው።

"አዎ፣ የሚስተር ለማ ሚስቶች አራቱም ሊጠይቁት መጥተዋል። ይህ ምን ታምር ነው ምንም ታምር አይደለም። የናንተ ሚስቶች ሊጠይቋችሁ እንደሚመጡት ሁሉ የሱም ሊጠይቁት ስንት አገር አቋርጠው መጥተዋል። ስለዚህ አሁን ሲገቡ በጨዋ ደንብ ተቀበሏቸው፣ እንግዶች ናቸው። እናንተም በሰው አገር ብትሆኑ ይኸው ነው። ያንን ሳቃችሁንና መገልፈጣችሁን አንዳንዶቻችሁ ብትተውት ይሻላል "አለች። የአዳራሻችን ዋና ቀላጅ ወንበሩን እያሽከረከረ ወደ አልጋዬ መጣ። እሱም አሥር ቀላጅና አላጋጭ ቢሆን፣ የዛሬው ወሬ ከሥሩ አናግቶታል።

"የለም ሚስተር ለማ፣ አራቱም ሚስቶችህ እንዲህ በድንገት ዱብ ከማለት፣ እንድትዘጋጅ ለምን በቴሌግራም አልነገሩህም መምጣታቸውን?" አለ።

"ሚስተር ለማ ገና በፊት ተናግሯል። ባገራቸው ቴሌግራም ወይ ቴሌፎን የለም። መልዕክት የሚተላለፈው፣ ወሬ የሚነገረው በ"ቶም- ቶም" ድቤ ነው ብሏል" አለ ግንበኛው ተሽቀዳድሞ።

"እውነት በድቤ ነው ሚስተር ለማ?" አለ ቀላጁ። እኔ ግን የድቤውን ነገር ልንገር አልነግራቸው ትዝ ባይለኝም መካድ ሰለማልችል "አዎ እውነት ነው በድቤ ነው" አልኩኝ። ቀልደኛውም ወደ አልጋው አመራ።

"ይልቅ ሚስተር ለማ" አለች ነርሷ" አሁን ምን ማድረግ ይሻላል? እንደምታውቀው በደንቡ መሠረት ባንድ ጊዜ አንድ ጠያቂ ነው እንዲገባ የተፈቀደው። ያ ሲወጣ የሚከተለው ይገባል ሚስቶችህ አራት ናቸው፣ ሁሉም ባንድ ጊዜ ሊገቡ አይችሉም ፕሮብሌሙ ይህ ነው"።

"ምን ፕሮብሌም አለው? እንደ ደንቡ ተራበተራ አስገቢያቸው" አልኳት።

"የምለው አልታየህም። መግባቱን በተራ ይግቡ እሺ፣ ብቻ ማንን አስቀድሜ ማንን አስከትላለሁ? አንዷ ብትቀድም አንዷ

ትቀየማለች፣ ትቆጣለች። የተቆጣችው ብትቀድም ሌላዋ ያልቀደመችው ትቆጣለች። እኔም ሴት ነኝ፣ የኛን የሴቶችን ጠባይ አውቀዋለሁ። ጥያቄው ማ ይቅደም ማ ይከተል? ነው" አለች።

እኔም በነገሩ ግራ እንደ መግባት ብሎኝ ጥቂት ሳሰላስል ሳለ "መፍትሄውን አገኘሁት "አለችኝ ነርሷ።" ስማቸውን ንገረኝ ልጻፈው። ከዚያ አንተ ያገባባቸውን ቅድም ተከተል ትነግረኛለህ። በዚያ መሠረት አስገባቸዋለሁ።" የኔ ችግር ደግሞ ሊጠይቁኝ የመጡት ሴቶች የኢትዮጵያ ተማሪዎች እነማን እንደሆኑ ስላላወቅሁ፣ ስማቸውን ለመናገር አልቻልኩም። ምን ይሻላል? ይኸም ሌላ ዓይን ፍጥጥ የሚያደርግ ጥያቄ ሆነና ቀረበ።

"በል ንገረኝ፣ ልጻፈው" አለች ነርሷ፣ እርሳስና ማስታወሻ ደብተር ከኮቷ አውጥታ።

እሷ አላውቀችም እንጂ እኔን ጨንቆኛል የጨነቀው ደግሞ እርጉዝ ባያገባም አንድ መላ መውለዱ አይቀርም። ስለዚህ "የለም ነርስ ስም አያስፈልግም፣ በስም ለመለየት አይቻልም። ሁሉም "ሚስስ ለማ" አይደለም የሚባሉት?"

"ይህንን አላሰብኩትም ነበር" አለች ነርሷ።

"ስለዚህ ዝም ብለሽ ሄደሽ ስም ሳትጠሪ ቁጥራቸውን ብቻ ነው መጥራት ቁጥር አንድ፣ ቁጥር ሁለት፣ ቁጥር ሶስት፣ ቁጥር አራት ስትይ እያንዳንዳቸው ቁጥራቸውን ያውቁታል። መጀመሪያ ያገባሻት ነች ቁጥር አንድ። ስለዚህ የክብር ደረጃዋ እንዳይነካ መጀመሪያ ቁጥር አንድን አስገቢ፣ ከዚያ ሁለት፣ ከዚያ ሶስትን፣ ከዚያ አራትን ታስገቢልኛለሽ" አልኳት።

"ገባኝ" ብላ ወደ በሩ አመራች። እኔ ይህን ማለቴ ጠያቂዎች የተቀመጡት በረጅም ወንበር በተርታ ስለሆነ፣ አንዷ ስትጀምር ሌሎቹ ተራቸውን ይዘው ይከተላሉ በሚል ግምት ነበር። እውነትም እንዳልኩት ሆኖ ነርሷ ተማሪ ሜሪ ታደሰን ወዲያው አስከትላ መጣች። ቤቱ ጭጭ እርጭ አለ። ሜሪ ቡርቱካን ይዛልኝ ነው የመጣችው" እዝጌር ይማርህ" አለችኝና በአማርኛ እጇን ዘረጋች፣ ተጨባበጥን ተቀመጠች።

"ቁጥር አንድ ግቢ፣' ስትል ጊዜ ነርሷ ወደ በሩ ጠጋ ብዬ የተቀመጥኩት እኔ ስለሆንኩ ተነስቼ መጣሁ" አለች ሜሪ። ወዲያው



በዚያ ባዳራሽ የተጋደመው በሽተኛ ሁሉ ዓይኑ በሷ ላይ መተከሉ ተሰማት፣ ለኔም ተሰማኝ።

"ምን ዓይነቶቹ ናቸው? ሰውም አይተው አያውቁ እንዴ? በዓይናቸው የሚባሉ ነው የሚመስሉት "አለችኝ።

"ጥቁር ብዙም አይተው አያውቁም። ከዚህ በፊት አይተውም እንደሆነ ብዙ ጊዜ ስለተኙ ተረስቷቸው ነው" አልኳት። "በዚያ ላይ እኔና አንቺ የምንነጋገርበት የአማርኛ ቋንቋም ፍጹም እንግዳቸው መሆኑን አትርሺ። ተገርመው ነው አይናቸውን ያፈጠጡት" ከዚያ የባጡን የቆጡን፣ የሀገር ቤት ወሬ፣ የለንደን ወሬ፣ የትምህርት የተማሪ ቤት ወሬ አወራችኝና ሰዓቷን አየት አደረገች።" በል ወንድሜ እኔ ብቻዬን ጊዜህን አላጥፋው እነሚሚ፣ ሶፍያ ሥርአተ ተራቸውን ይጠብቃሉ። ደህና ሁን ልሂድ። ቶሎ ብለህ ዳንና ለንደን ና "ብላኝ እንደገና ተጨባበጥን ወጣች።

ሜሪ እንደወጣች ነርሷ ወደ በሽተኛ ጓደኞቼ ተግሳጽና ማስጠንቀቂያዋን በተጨማሪ ወረወረች። "ልባርጉ እናንተ ቀላጆች ሁሉ አሁን ቁጥር ሁለትን ልጠራ ነው። መቀባጠራችሁን እንዳትጀምሩ እንግዲህ እንደ ባለጌ መንጋ። ጭዋነታችሁን አሳዩ" አለችና ወደበሩ አመራች።

"ሚስተር ለማን አንዳንድ ጥያቄ መጠየቅ አይፈቀድልንም?" አለ አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

"ጥያቄ አሁን አይቻልም፣ አያስፈልግም። እንግዶቹን ሁሉ ካሰናበተ በኋላ ምናልባት ሚስተር ለማ ጥያቄ እንድትጠይቁት ይፈቅድላችሁ ይሆናል። "ብላ ወጣ አለችና በዋናው በር አንገቷን ወደ ውጭ ብቅ አድርጋ "ቁጥር ሁለት ይግቡ!" ስትል ሰማኋት። ወዲያው ሚሚ ወልደማርያም ገባች። ሚሚ በቁመት ከሜሪ አጠር ብትልም የአጭር ቆንጆ ነበረች። እሷ የወይን ዘለላ ነው ይዛልኝ የመጣችው። ከእሷም ጋር እጅ ተጨባብጥን፣ ጥቂት ወሬ አወራርተን፣ ትንሽ ተቀላልደን ስንሳሳቅ ሳለ፣ ድንገት የፊቷ ሁኔታ ተለወጠብኝ።

"ምነው? ደህና ነው?" አልኳት።

" አይ ምንም አይደል፣ የፈረንጆቹ ሁኔታ ነው የከነከነኝ "አለች። "እንግዳ ሰውም አይተው አያውቁ እንዴ!? አለች። ዘወር ስል ሁሉም አይናቸውን እኔ ላይ ነው የተከሉት...

"ጥቁር ብርቃቸው ነው። አብዛኞቹ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት አመት ከአልጋ ሳይወርዱ፣ እውጭ ሳይወጡ የቆዩ ናቸው። ለዚህ ነው የሚያፈጡ የሚመስሉት። ሜሪም አሁን አንቺ ያልሽውን አንስታብኝ ነበር... ክፋት የለባቸውም፣ " አልኳትና አረጋጋኋት። እሷም ፈጥኜ እንድድንና ወደ ለንደን እንድመጣ አደራ ብላኝ በፈገግታ ተጨባብጠን ወጣች።

ከሚሚ ለጥቃ ቁጥር ሶስት ሶፍያ አብርሃ ገባች። ጥሩ ጥሩ ሙዝ አበረከተችልኝ። ለእርሷ ግን የበሽተኞቹ አይን መፍጠጥ እንዳያሳስባት አስቀድሜ ጉዳዩን ስላስረዳኋት ጉብኝቷ በለዘበ መስመር ነበር የተራመደውና የተፈጸመው። ከሶፍያ ለጥቃ ስርጉት ነች መጨረሻ የገባችው- ቁጥር አራት። እሷም በለንደን የነርሶች ማሰልጠኛ ኮሌጅ የነርስነትን ሞያ ስለነበር የምትማረው "ጊነስ" የሚባለው ጥቁር ወፍራም የእንግሊዝ ቢራ በእኛ ሆስፒታል የሚፈቀድ መሆኑን በማወቋ ጥቂት ትንንሽ ጠርሙሶች ይዛልኝ ነበር የመጣችው።

"ለንደን ሳለህ ቢራ እንደምትወድ ሰምቼ ምናልባት ውለታው ያስቸግርህ ይሆናል ብዬ ነው ይህን ያመጣሁልህ "አለችኝ። እኔም ከልቤ አመሰገንኳትና የበሽተኞቹን አይን ማፍጠጥ ነገር ሳታነሳው አንስቸ ላበረታታት ብሞክር፣ እሷ በለንደን ሆስፒታሎች እየተዘዋወረች ሞያዋን በምትለማመድበት ጊዜ የፈረንጅን በሽተኞች ጠባይ፣ በተለይ የዝቅተኛውን ክፍል የለመደችው መሆኗን ነገረችኝ። ተጨዋወትን አወራራን፣ ተሰነባበትን። ስርጉት፣ ማለትም አራተኛዋ ሚስቴ ስትወጣ ነው ክፍላችን በበሽተኞቹ ሊፈነዳ የደረሰው። ድንገት ጭብጨባው ቀለጠ ምስጋናውም የዚያኑ ያህል ነበር። አራት ሚስት አግብቻለሁ ያልኩት በግልፅ በተግባር በመታየቱ አድናቆቱ በሰፊው ነው የተነጠፈልኝ። "እንዲህ ነው ወንድ ማለት!" ተባለ። ቀጥሎ የጥያቄው ጋጋታ ተከተለ።

"ባልና ሚስት ከሆናችሁ በስንት ጊዜ ስትገናኙ እንዴት አትሳሳሙም?" አለኝ ሽማግሌው አየርላንዳዊ በቁም ነገር። ቀልደኛው ቀበል አድርጎ "ኤስኪሞዎች እንኳን አፍንጫ ላፍንጫ ነው አሉ የሚፈጋፈጉት... እውነት፣ በፊልም ያያቸው ሰው ነው የነገረኝ" አለ።

"ህንዶች አይሳሳሙም ይባላል" አለ ግንበኛው። ስለመሳሳም ወይም አለመሳሳም ጥቅምና ጉዳት በበሽተኞቹ ወንደላጤዎችና ጎልማሶች መሀከል የተጧጧፈ ክርክር ተነሳ። እኔ ሁሉንም በጨዋ



ደንብ እየሰማሁ፣ አዲስ በተገኘው ግርማ ሞገሴ ተጀቡኜ፣ ክብሬን ጠብቄ ዝም አልኳቸው። እነሱ ግን ዝምታዬን አልወደዱትም።

"ሚስተር ለማ፣ አስረዳን የማስረዳት ግዴታ አለብህ። እኛ ሚስቶችህን አክብረን አፋችንን ይዘንልህ ሳንበጠብጥ እስኪሄዱ ታግሰናል!" አለ አንዱ ከፊት ለፊቴ።

"አዎ! ማስረዳት አለብህ!" አሉ በህብረት።

"አስረዳቸው፣ ትምህርት ነው።" አለኝ ሽማግሌው።

"አንተ ካልክ እሺ። በአገራችን ሁለት ጠጉር ያበቀለ ይከበራል" አልኩት "ብቻ በጸጥታና በርጋታ ይስሙኝ፣ ከተንጫጩ አልናገርም።"

"ስሙ ሁላችሁም " አለ አዛውንቱ። "ሚስተር ለማ ማስረዳት ፈቅዷል። ግን በጥሞና ካልሰማችሁት አይሆንም ብሏል "አለ ድምጡን ከፍ አደረገና። ወዲያው ክፍሉ ፀጥ እረጭ አለ።

"መሳሳም በኔ አገርም አለ። የሚፈጸመው ግን እንዲህ እንደናንተ በገሀድ ባደባባይ፣ በጠራራ ጣይ አይደለም፣ በስውር ነው፣ በድብቅ፣ በጨለማ። ባልና ሚስት የሚሳሳሙት ሌሊት ሁለቱ አብረው ሲተኙ ነው። በጥቅጥቅ ጨለማ። እሰው ፊት በቀን መሳሳም ታላቅ ነውር ነው። እናንተ እዚህ እኔ ፊት የሚስቶቻችሁን ወይም የእጮኞቻችሁን ከንፈር እንደ ሙዝ ስታላምጡ ስትገማመጡ ሳያችሁ፣ ስለእናንተ እኔ አፍራለሁ" አልኩ።

"ለዚህ ነዋ ያልተሳሳማችሁት? አሁን ገባኝ" አለ አንዱ ከጎኔ፣ በሳቅና በስላቅ ሳይሆን በከበሬታ። እዚህ ላይ ሚስቶቼን ያስተናገደችው ተረኛ ነርስ ስትቻኮል መጣች።

"ሚስተር ለማ አራት ቆንጆ ቆንጆ ሚስቶች አሉህ። እውጭው በር ድረስ ሸኘሁልህ፣ ደግ አላረግሁም? ስንለያይ እያንዳንዳቸውን እየጨበጥኩ 'ጉድ ባይ ሚሲዝ ለማ፣ ጉድባይ ሚሲዝ ለማ' እያልኩ ሁሉንም ስሰናበታቸው አይናቸው በመገረም ይሁን በድንጋጤ ፍጥጥ ፍጥጥ ሲልብኝ ጊዜ ሥነ ሥርአት አጓድዬ እንደሆነ በማለት ሰግቼ ነበር። ኋላ ግን አራቱም ባንድነት በሳቅ ፕነፈሉና እነሱም 'ጉድ ባይ ነርስ' ብለውኝ ሄዱ። ምን አሳስቼ ይሆን? ሚስቶችህን ማስቀየም አልፈልግም" አለች።

"ምናልባት ቅደም ተከተላቸውን አላከበርሽ እንደሆን? መጀመሪያ ቁጥር አንድን ነበር መጨበጥ ያለብሽ" አልኩ።

"አዎ! አሁን ገባኝ። እኔ ደሞ የተራ ቁጥራቸውን ነገር በምን አስቤው! የጀመርኩት በቁጥር አራት ነበር ለዚህ ነዋ እንደዚያ ግር ያላቸው?"

"አግኝተሽዋል፣ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲህ ያለ ስህተት እንዳይለምድሽ።"

"እንኳን የነገርከኝ ለወደፊቱ እጠነቀቃለሁ።"

"አዎ። በተለይ አንቺ ራስሽ ለሚስት ቁጥር አምስትነት የታሰብሽ ስለሆንሽ፣ ከወደፊት እህቶችሽ ጋር አሁኑኑ መልካም ወዳጅነት ብትመሠርቺ አይከፋም አልኳት" በቁም ነገር።

"ምን?! እኔን ? ሃ ሃ ሃ ሃ !..." ተንከተከተች። "ስሙ ሁላችሁም!" አለች ወደ ክፍሉ መሀል ሄደችና። "ታላቅ የምስራች ላካፍላችሁ፣ ሚስተር ለማ መልኬን ጠባዬን ሲያጠና ነበር ለካ። የእስካሁን የጥናቱ ውጤት ስላረካው ለሚስት ቁጥር አምስትነት እኔን ጄን ጀርከርን አስቦኛል! ግሩም አይደለም ወይ?! " አለችና ሆዷን በእጇ ደግፋ ትንፋሽ እስኪያጥራት ድረስ በሳቅ ተንፈራፈረች። የበሽተኞቹ ጉባኤም "እንኳን ደስ ያለሽ! እንኳን ደስ ያለሽ!" ብለው አጨበጨቡላት። እሷም ሳቋን ማስታገስ አቅቷት፣ ከአዳራሹ እየሮጠች፣ እየተንገዳገደች ወጥታ ሄደች። በስተቀኝ የተኛው ግንበኛ የድርሻውን ከሳቀ በኋላ" ደሞ አምስተኛ!? አታረገውም!" አለኝ።

"ታይ የለ? ብቻ አንዴዬ ልዳንና ወገቤን ልጠግን" አልኩት ሳቅ ብዬ።

"መዳኑን አሁን ነው የምትድነው። ይኸ የኛው በሽታ በጥቁሮች ላይ መጀመሪያ ይጠናባቸዋል፣ ወዲያው ይለቃቸዋል። ጆኒ አባ በአራት ወር ብቻ ነው ድኖ የወጣው። አንተ ስንት ወር ሆነህ አሁን?"

"መንፈቅ ሊሞላኝ ምንም ያህል አልቀረኝ"

"በዚህ ሰሞን ወደ ደንበኛ አልጋ ባያዛውሩህና በእግርህ መራመድ እንድትለማመድ ባያደርጉህ ምን አለ በለኝ" አለ።

"ማን ነገረህ? ወሬ ሰምተሃል ከነሜትረን አካባቢ?" አልኩ።

"የምን? እንዲያው ነው፣ የራሴ ስሜት ነው፣ ትንቢት ነው" አለ።

"እንዳልከው ያርግልኝ ያባቶቼ አማልክት!" አልኩት።



በበነጋው ረፋድ ሲል ቀኑ ብራ ስለነበረ መቼም ፀሐይ ብርቅ ነች በእንግሊዝ አገር - ከነ አልጋችን እየተነዳን ለተለመደው ጣይ ሙቀት እሰፊው በረንዳ ላይ ተሰጣን። ብርድ ልብስና አንሶላችንን ተገፈን መለመላችንን ሁለት ሰአት ይሁን ሶስት ሰአት ጣይ እንደሞቅን፣ የምሳ ጊዜ ስለደረሰ ወንድ ነርሶቹ መልሰው ወደ ቤት ሲያገቡን ያ ቀንደኛው ቀልደኛ" እንዳትነኩኝ እቤት አልገባም" አለ። ለጥቆ "የሥራ ማቆም አድማ መተናል" አለ። ሌሎቹም" አዎ መተናል" ብለው በህብረት ጮሁ። ምክንያቱን ነርሶቹ ቢጠይቁ፣ "ለእናንተ አንናገርም" አሉ በሽተኞቹ። ነርሶቹ ከአልጋ የዋሉትን በግድ ሊያስገቧቸው ቢሞክሩ ባለ ተሽከርካሪ ወንበሮቹን ባለ መጫሚያዎቹ አንካሶች መንገዱን አጥረው አናሳልፍም አሉ። መቋሚያቸውን በነርሶቹ ላይ ቃጡባቸው ከናካቴው።

"እናንተ በጥጋባችሁ አንገባም ምሳ አንበላም ካላችሁ ይህ የሰው አገር ሰው ጠሙን ይዋል አይባልም፣ ባይሆን እሱን እናስገባለን" አለና አንዱ ነርስ ወደኔ አልጋ አመራ። እነሱን ተዋቸው፣ ሚስተር ለማ፣ አንተ ጨዋ ሰው ነህ፣ ግባና ምሳህን ብላ" አለና የተሽከርካሪ አልጋዬን ግርጌ በሁለት እጆቹ ጨብጦ ሊስብ ሞከረ። የአድመኞቹ አይናቸው ደም ለብሶ እኔ ላይ ተተከለ። እኔም መልዕክታቸው ገባኝና የአልጋዬን ፍሬን ለቀም ሳረገው አልጋው ቀጥ አለ

"ምን መሆንህ ነው ሚስተር ለማ? ፍሬኑን ልቀቀው እንጂ" አለኝ ነርሱ።

" ይቅርታ ነርስ፣ እኔም አልገባም፣ ከክፍል ጓደኞቼ አልነጠልም" አልኩት።

"ምን ጨነቀኝ?! ለእኛ ብላችሁ ሁላችሁም ጠማችሁን ዋሉ" ብሎ ነርሱ ውልቅ ብሎ ወጥቶ ሲሄድ፣ የቀሩት ነርሶችም ተከተሉት። ያደሙት በሽተኞች በድል አድራጊነት እየተሳሳቁ አጨበጨቡ።

"ደግ አርገሃል ሚስተር ለማ" አለኝ ሽማግሌው አየርላንዳዊ ጎረቤቴ። "አንተ ብቻ ተነጥለህ ብትገባ ኖሮ፣ ሁሉም ይጠምዱህ ነበር፣ አሁን ግን ሁሉም ናቸው በሆዳቸው የሚያመሰግኑህ" አለና፣ እጁን አጨበጨበ። "ስሙ ሁላችሁም! አንድ ልዩ ጭብጨባ ለሚስተር ለማ ይደረግለት!" እሱም እነሱም በህብረት አጨበጨቡልኝ። እኔም ስለጭብጨባው ምስጋናዬን አሰማሁ። ቢሆንም የአድማው መንስኤ ምን እንደሆነ ሳላውቅ እንዲያው እንደ በግ ተነድቼ ከአድመኞቹ መደመሬ ጥቂት ሳይቆረቁረኝ አልቀረም።

"ደግ ማድረጌ ይሰማኛል ግን የአድማው ሰበብ ምን ይመስልሀል?" አልኩት።

"ሰበቡማ የሆስፒታሉ ምግብ መበላሸት፣ ጣዕመቢስነት፣ መናኛነት ነው። ዘወትር የሚቀርብልን ቅቅል ድንችና ቅቅል ኩሩምባ ጎመን ነው አንዳንዴ ጠረኑ ራሱ አንጀት ይዘጋል። እንደምታየው፣ እኔም አልፎ አልፎ ካልሆን ብዙም አልበላው። እድሜ ለልጄ እሷ በየሳምንቱ ከለንደን የምታመጣልኝን ስንቅ ነው እየቆጠብኩ የምመገበው። አንተም ብትሆን በደረቅ አይብና በዳቦ በተቀላቀለ እንቁላል፣ በወተትና በጣሳ ምግብ ነው ያለኸው። የሆስፒታሉ ምግብ ቢጥም ኖሮ ይህን ያህል ገንዘብ አታወጣም ነበር" አለኝ።

"የኔ ለየት ያለ ነው፣ ባገሬ በበርበሬ፣ በሚጥሚጣ፣ በቃሪያና በቅመም የሚሰራ ምግብ ለምጄ ይኸ የናንተ የሰለጠነው አለም መና ውሀውሀ ነው የሚለኝ። አንዳንዴ ስበላው ያቅለሸልሸኛል ስለዚህ የበርበሬ ዱቄት ዘመድ ከአገሬ ባውሮፕላን እየላከልኝ ነው ምግባችሁን የተቋቋምኩት" አልኩት።

"ለሁሉም አንድዬ አድማ አድርገናል። ስለሆነም የሆስፒታሉን ባለሥልጣኖች መቋቋም ግዴታችን ነው" አለ በቀኝ ያለው ግንበኛ። እዚህ ላይ ሜትረኗ በነርሶች ታጅባ መጣች።

"ምንድነው የነካችሁ? ለምን አትበሉም? ግቡ ሲሏችሁ ካልገባችሁ፣ ቀኑ ቢመሽና እዚሁ ብርድ ላይ ብታድሩ በጤንነታችሁ ላይ ለሚደርሰው አደጋ ሆስፒታሉ ኃላፊነት የለበትም። ሌላው ይቅር ዝናብ ቢዘንብስ? ይህን ይህን ያሰባችሁበት አይመስልም። ችግራችሁን ንገሩንና በስነ ሥርአቱ በተቻለ ሁሉ እንረዳችኋለን።" አለች።

"ሜትረን ጊዜሽን አታጥፊ ከኛ ጋር በመከራከር። እኛ ለማነጋገር የምንጠይቀው የሆስፒታሉን ዴሬክተር ራሳቸውን ነው። ከዚያ በታች አይሞከርም!" አለ ቀላጁ አንካሣ። ሌሎቹም አጨበጨቡ።

"ዲሬክተሩ ዛሬ ከባድ ከባድ የቀዶ ጥገና ሥራ ስለያዙ ጊዜ የላቸውም። መልዕክቱን ለኔ ንገሩኝና ባይሆን ልንገርላችሁ" አለች ሜትረን በዲፕሎማሲ።



ባለ ተሽከርካሪው ወንበር ቀልደኛ ዛሬ አምርሯል። "ዲሬክተሩ ራሳቸው ካልመጡ ለማንም አንናገርም፣ ይህ የመጨረሻው ውሳኔያችን ነው። አይደለም ልጆች?" ሲል ጠየቀ።

"ነው!! የመጨረሻው ነው። ፍንክች የለም!" አሉ በህብረት።

"አንድዬ ተናግሬአለሁ፣ ትገቡ እንደሆን ግቡ። ካልገባችሁ ምን ጨነቀኝ፣ ዝናቡ ያበስብሳችሁ። ሬዲዮው ዛሬ ከሰዓት በኋላ ይዘንባል ብሏል፣ አስቡበት" ብላ ሠራዊቷን አስከትላ ወጣች። ለአምስተኛ ሚስትነት ያጨኋት ነርስ ቀረት አለችና ወደ አልጋዬ ቀርባ፣ "አንተም?! ምን ሆንኩ ብለህ ነው?" አለችኝ ከፈገግታ ጋር። መልሱን የሰጣት ግንበኛው ነው። "ምን ልታደርጊው ፈልገሻል ከጓደኞቹ ነጥለሽ? የፈሳች ጅንጀሮ!" አለና ሳቀባት። "አይዞሽ ለቀለበቱና ለሰርጉ ጊዜ አለሽ፣ አትቸኩይ!" ሌሎቹም አ! ብለው ስለሳቁባት ሌባ ጣቷን ቀስራ በምርና በቀልድ ቅልቅል ብቻ ዝታባቸው እየሮጠች ሄደች። ጥቂት እንደቆየን ዳሬክተሩ ሀኪም ከሌሎች ሀኪሞች ጋር መጣ።

"በሉ ንገሩኝ" አለ በፈገግታ።"ምስጢሩ ምንድነው ለሌላ ሰው የማይነገረው? አትፍሩ፣ ግልጥ አርጋችሁ እውነቱን ንገሩኝ/አጫውቱኝ/ እሰማለሁ" አለ።

የአድማው ቀንደኞች በየተራ እንደ ውዳሴ ማርያም አንበለበሉት። የምግቡን አበለሻሸት አንጠርጥረው እየተነተኑ ተናገሩ። ምኑም አልቀራቸው። የዳሬክተሩ ረዳት የሆነ ሐኪም ሀሳባቸውን በማስታወሻ ደብተሩ ያሰፍር ነበር። የምግቡ ኃጢአት ሲገባደድ የመጠጡ ቀጠለ። የወተቱ መበላሸት፣ የሻዩ መግማት ወዘተ.... ለመደምደሚያ ግንበኛው ጎረቤቴ፣

"የመጠጡ ነገር ከተነሳ የተዋለብንን ግፍ ልናገር። ግማሽ ደርዘን ጠርሙስ ጥቁር ቢራ ሚስቴ ከለንደን ድረስ ተሸክማ ያመጣችልኝን ሲስተሯ ወርሳኛለች። እዚህ ያሉት ሁሉ ምስክሮቼ ናቸው ለፈጸመችው ወንጀል"

"በዚህ ጉዳይ ጊዜ ባናጠፋ ይሻላል። የተወረሰውን 'ጥቁር ቢራ' ሲስተሯ ለሜትረኗ አስረክባለች። ቢራው ቢቀመስ አንዳንዱ ጠርሙስ ጂን፣ አንዳንዱ ዊስኪ የያዘ ሆኖ ተገኝቷል። አንድም ቢራ የያዘ ጠርሙስ አልተገኘም። ጠርሙሱ ብቻ ነው ቢራ፣ ውስጡ ደረቅ አልኮል ነው። ይህ የሆስፒታሉን ህግ ማፍረስ ስለሆነ ወደ ሌላ

ሆስፒታል በማዛወር ልትቀጣ ነበር። ሚስትህ ሰምታ ጥፋቷን አምና፣ ምህረት እንዲደረግ ብለለመነች ነው ነገሩን ችላ ያልነው። የተግሳጽ ደብዳቤ በቅርቡ ይደርስሃል። ይህ ወንጀል ቢደገም ከዚህ ሆስፒታል መውጣትህ ነው" አለ ሀኪሙ በቁም ነገር፣ ግን ያለ ንዴት። "እሺ የእናንተን በደል ሰምቻለሁ፣ በማስታወሻ ተይዟል አንዳንዴ እውነታችሁን ነው። የምግቡ ነገር ከሚያሳዝን ደረጃ መድረሱ እኔንም ተሰምቶኛል። አስፈላጊው እርምት እንዲደረግ አሁኑኑ አዛለሁ"። አለና ከፊቱ ፈገግታ ሳይለይ ወደ እኔ አልጋ መጣ።

"አንተ ለማ፣ ሚስተር ለማ እዚህ እነጭ ባህር ውስጥ ምን ታደርጋለህ? እንደምሰማው ምግብህን ከውጭ ግሮሰሪ ወይም ከለንደን እያስገባህ ነው አሉ የምትመገብ፣ ከአድማው ምን አገባህ?"

"ጌታዬ ባገራችን የፈሳች ጅንጀሮ ብቻ ነች ከጓደኞቿ የምትነጠል። እኔ የፈሳች ጅንጀሮ መሆን ስለማልፈልግ ከባልደረቦቼና ከቤተኞቹ ጋር መሰለፍ ግዴታዬ ነው። ሁሉ ሲወጣ እኔ ብቻ ብገባ ሰልፍ አያምርም" አልኩት።

"እንግዲህ የፈሳች ጅንጀሮ ላለመሆንና ሰልፍ ላለማበላሸት አይደለም አድመኛ የሆንከው። "ሳቅ አለ ሀኪሙ። "ይህ ምን ማለት እንደሆነ ለኔ አይገባኝም። ቢሆንም ያገርህን ባህል አታክብር አትባልም። የጅንጀሮዋን ነገር ሌላ ጊዜ ታስረዳኛለህ። በነገራችን ላይ ለእኔ ከሚፈላው ቡና የሚላክልህ አሁንም ይደርስህ የለ?"

"ያለማስታጎል ይሰጡኛል፣ አመሰግናለሁ" አልኩ።

ዴሬክተሩ ወደ ቀሩት በሽተኞች ዘወር አለና "በሉ እንግዲህ፣ አስፈላጊውን አደርጋለሁ ብዬ ቃል ገብቻለሁ። እናንተ ደሞ ለእኔ ስትሉ እቤት ግቡልኝ "አላቸው። ህመምተኞቹ በሙሉ በደስታ አጨበጨቡ። የእነሱ ጭብጨባ ሲያቆም ደመናው ተቀብሎ ይስገመግም ጀመር። አተር አተር የሚያህል የዝናብ ጠብታ አልፎ አልፎ ዱብ ዱብ ማለት ሲጀምር በነርሶቹ እየተነዳን ወደ መኝታው አዳራሽ ገብተን አልጋችን በየጥጋችን ቆመ።

በነጋታው ረፋዱ ላይ ዲሬክተሩ ሐኪም በሜትረኖች፣ በሲስተሮና በነርሶችም ታጅቦ ክፍላችንን ሊጎብኝ መጣ። የእያንዳንዱን በሽተኛ ብርድ ልብስና አንሶላ እያስገለጠ መርመር መርመር በማድረግ በፍጥነት ትእዛዙን ለሲስተሯ እየሰጠ ጉዞውን ቀጠለ። ሲስተሯም ትዕዛዙን በማስታወሻ ደብተሯ ወዲያው ነበር የምታሰፍረው። ሲል ሲል



ከእኔ አልጋ ሲደርስ ቆም አለና፣ "እስቲ ይኸ አፍሪቃዊ ከምን እንደደረሰ እንመልከት" አለ በፈገግታ። ገላለጡኝ። ጀርባዬን የታሰርኩበት ቀበቶ እንዲፈታ አዘዘ። ሐኪሙ በእጁ ደባበሰኝ። ስድስት ወር ሙሉ ያልሞከርኩትን ተገልብጬ በሆዴ አንድተኛ ተደረገ። የወገቤን ቁስል ጠባሳ ጫን ጫን እያለ መረመረና ትእዛዙን ለሲስተሯ ሰጥቶ ወደ ግምበኛው አመራ። ከዚያም የቀሩትን አዳርሶ እንደታጀበ ወጥቶ ሄደ። ለአምስተኛ ሚስትነት ያጯኋት ነርስም አብራ በአጀቡ ስለነበረች ወዲያው ስትሮጥ መጣችና ትንፋሽ እያጠራት፣

"ሚስተር ለማ፣ እንኳን ደስ ያለህ! ድኅሃል "አለችኝ። "ከእንግዲህ ከታሰርክበት አልጋ ወርደህ በእግርህ የምትራመድበት ቀን ደርሷል "አለች ጮክ ብላ። ይህን ሲሰሙ የክፍሉ በሽተኞች በደስታ አጨበጨቡልኝ። "እንኳን ደስ ያለህ" አሉኝ። አንዱ አምስት አመት ሙሉ ተኝቶ ገና ያልዳነ ሽምግል ያለ በሽተኛ ብቻ ነው እንደ ልማዱ በልቅሶ ሲንሰቀሰቅ የታየው። ይህን ባይ እኔም በደስታዬ ላይ ሀዘን ጨመረልኝ። ጎረቤቶቹ በሽተኞች አልቃሻውን እንደ ሕፃን ከበው ሲያባብሉት አየሁ እንደ ተለምደው።

ቀስ በቀስ በእግሬ መቆም ከዚያም መራመድ፣ ከዚያም በክፍሉ ወርድና ቁመት ከዘራ እየተመረኮዝኩ መንሸርሸር ተላመድኩ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ማገገሚያ እንደሚወስዱኝ ነገረችኝ ሲስተሯ። እኔ ግን በወጣትነት ችኮላዬ በቀጥታ ወደ ለንደን ለመመለስ መቁረጤን ገለጥኩላት። "ተው አይሆንም" ብትለኝም፣ የክፍሉ ባልደረቦቼን ሁሉ አንድ ባንድ እጃቸውን እየጨበጥኩ ተሰናብቼ ወደ ባቡር ጣቢያ በታክሲ አመራሁ። ከዚያም ተሳፍሬ ለንደን ከተማ ገባሁና ከመታመሜ በፊት ተከራይቼ እኖርበት ወደ ነበረው ቤት እንደገና በታክሲ ደረስሁ። ባለቤቲቱ ባልቴት በደስታ ተቀብላ የዱሮ ክፍሌን ሰጠችኝ። ቢሆንም አዲሱን የለንደን ኑሮ በአንድ በውል ባልተረዳሁት ምክንያት የሚያበሳጭና የሚያስተክዝ ሆኖ አገኘሁት። ችኩዬ ወደ ለንደን ከመመለስ ይልቅ ሲስተሯ እንደ መከረችኝ በፊት ወደ ማገገሚያ ጣቢያ ብሄድና እዚያ እየተዝናናሁ እረፍት ባደርግ ይህ ያሁኑ ንጭንጭና ብስጭት አይገጥመኝም ነበር ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ እረፍትና ጸጥታ በመሻት እንደገና በባቡር ተሳፍሬ 'ሄስቲንግስ' ወደምትባል የለንደን ትንሽ ከተማ ሄድኩኝ። እዚያም ከአንድ የባቡር ጣቢያ ሠራተኛ፣ ከሚስቱና ከደረሰች ልጁ ጋር በኪራይ ተዳብዬ ተቀመጥኩ።

ባለቤትየው የወዛደር መደብ አባል በመሆኑና ተራማጅ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያለው ስለነበር እንደኔ አይነቱን ጥቁር በማስገባቱ ተደስቶ ነበር። ሚስቱም ልጁም በተቻላቸው መጠን ይረዱኝ

ያስቡልኝ ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው እኔ በእንግሊዝ አገር ተማሪ በነበርኩበት በ 1940 እና በ 1947 ዓ.ም ገደማ ነው። መቼስ ያን ጊዜ በእንግሊዝ አገር የሚኖሩት አፍሪቃዊ ሆነ እስያዊ ሰው ጥቂት ብቻ ነበሩ። አብዛኛው ለትምህርት የመጣና ሲጨርስ ወደየአገሩ የሚመለስ እንጂ እዚያው ሰፋሪ አልነበረም። ስለዚህ ጥቁር አፍሪቃዊ ሆነ እስያዊ እንደ ብርቅ ነበር የሚታየው- በነጮቹ ነዋሪዎች ዘንድ። ቢሆንም አልፎ አልፎ ቤት ለጥቁር አናከራይም የሚሉ ነጮች አልታጡም። በአንዳንድ የገጠር ከተማማ ህፃናቱ አንድ ጥቁር ሲያዩ አይናቸውን መበልጠጣቸውና ምላሳቸውን መጎልጎላቸው ይታይ ነበር። እኔንም ይህ ዓይነቱ ሁኔታ በየጊዜው አጋጥሞኛል።

አንድ ቀን እንደተለመደው እግሬን ለማጠናከርና የባህር አየር ለመቀበል ከሰአት በኋላ ጥላ በረድ ሲል ከዘራዬን ተመርኩዤ በባህሩ ጠርዝ በሚሰራው መንገድ ሽርሽሬን ሳካሂድ ሳለ፣ የሰፈሩ ህፃናት በርከት ብለው ያጅቡኝ ጀመር። በእድሜ ከአራት እስከ ስድስት አመት አያልፉም። ጫጫታቸው ግን ልዩ ነበር። ጩኸታቸውም ሁለት ቃል ብቻ የያዘ ነው። አንዱ ያወርዳል፣ ሌሎቹ ይቀበላሉ፣ ማለትም ከኋላ ኋላዬ እየሮጡ እየተከተሉ" ብላክ ማን! ብላክ ማን" ብለው ነበር የሚያዘምሩት። ትርጉም "ጥቁር ሰው!" ማለት ነው። በዚህ አኳኋን እኔ ከዘራዬን ይዤ ቀድሜ እነሱ እየተከተሉኝ ጥቂት ከተጓዝን በኋላ ባጋጣሚ አንድ የብርድ ባርኔጣ የደፋ፣ ካፖርት የደረበ፣ እሱም ከዘራ የያዘ ሽምግል ያለ አዛውንት ከፊት ለፊታችን መጣ። እሱም ያስለመደውን የማታ ሽርሽር ኖርማል የሚያደርገው። የአጀቡኝን ህፃናት ሁኔታ ሲያይ በድንገት ቀጥ ብሎ አጠገቤ ቆመ።

"እናንት ልጆች! የሚያሳፍር ነገር ነው የምታደርጉት ነውር ነገር ነው የምትሰሩት" አለ በቁጣ ጮኸና። "ጥፉ ከዚህ" አለና ከዘራውን አንስቶ በማስፈራራት አባረራቸው፣ አሳደዳቸው። ህፃናቱም ደንግጠው ተበታተኑ። እኔም ሁኔታው ገርሞኝ ቆምኩ። ከዚያ ሰውየው ወደ እኔ ተመለሰና ባርኔጣውን አውልቆ ይቅርታ እንዳደርግ ጠየቀኝ። የሰው አገር እንግዳ ሆኜ እንዲህ ያለ የህፃናት ቅሌት ቢያጋጥመኝ፣ ህፃናቱ ያሳዩት እውነተኛውን የእንግሊዝ ጠባይ አይደለም። በሱ አስተሳሰብ ያሳዩት እውነተኛውን የእንግሊዝ ጠባይ አይደለም። በሱ አስተሳሰብ በዚህ እንዳልከፋ ደግሞ አሳሰበኝ። እኔ ግን" ህፃናት ናቸው ምን ያድርጉ? ከተወለዱ ጥቁር ሰው አይተው ስለማያውቁ ብርቅ ሆኖባቸው ነው።ቀላል ነው ነገሩ፣ ምንም አይደል። እኔም' ጥቁር ሰው' በመባሌ ቅር አይለኝም፣ እውነት ነው ጥቁር ነኝ። ስለዚህ የእርስዎ በዚህ መጨነቅ ተገቢ አይመስለኝም" አልኩት በፈገግታ። "ህፃናት ምን ያውቃሉ?"



"ቢሆንም ቢሆንም፣ ህፃናቱ ትልቅ ብልግና ነው ያሳዩት። እኔ እንዳንተ ስቄ አላልፈውም። ነውር ነው" አለና ከኪሱ የመታወቂያ ካርዱን አውጥቶ ሰጠኝ። "ስሜም፣ አድራሻዬም፣ ስልኬም እዚሁ ላይ አለ። ቤቴም ቅርብ ነው። ፈቃድህ ቢሆን የፊታችን እሁድ እኔ ቤት ምሳ ብትጋበዝልኝ ደስታውን አልችለውም" አለኝ።

እኔም የሀሳቡን ቅንነት ተመልክቼ "አመሰግናለሁ ጥሪውን እኔም ተቀብያለሁ" አልኩት።

"ለመጨዋወቻ ጊዜ እንዳያጥረን ጥቂት ቀደም ብለህ በስድስት ሰዓት ብትመጣ ጥሩ ነው። ከሚስቴና ከልጆቼ ትተዋወቃለህ" አለ። "በነገራችን ላይ ከየት አገር ነው አመጣጥህ? ከአፍሪቃ መሆኑን አውቃለሁ"

"አገሬ ኢትዮጵያ ነው"

" እንዴ፣ ኢትዮጵያማ ጥንታዊ ታሪክና ስልጣኔ ያላት አገር አይደለችም!? ክርስትና እንኳን እናንተ የተቀበላችሁት ከኛ የትና የት ቀድማችሁን ነው። ሙሶሊኒ የዋለባችሁን ግፍ ሁሉ፣ የመርዝ ጢሱን ነገር ጭምር አውቃለሁ" አለ።

"ጥቂት እንደርስዎ ያገሬን ታሪክ የሚያውቅ አዛውንት ሳገኝ እደሰታለሁ" አልኩት አጸፋውን።

"ሁሉንም እሁድ ስትመጣ በሰፊው እንጫወታለን። እኔም አንድ ኢትዮጵያዊ በአካል ሲያጋጥመኝ ዛሬ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። ይገርማል!... ለጊዜው እቸኩላለሁ፣ እሁድ እስክንገናኝ ደህና ሁን" ብሎኝ ሽርሽሩን ፈንጠር - ፈንጠር እያለ ቀጠለ።

"ደህና ይሁኑ!" እንዳልኩት በእንግሊዛውያኑ ህፃናት ነገር እንደገና ሳቅሁና እኔም እንከል እያልኩ የሽርሽር ጉዞዬን ከአስፋልቱ መንገድ ወጥቼ በባህሩ ጠርዝ፣ በአሸዋው ላይ ቀጠልኩ። የምረግጠው አሸዋ ሌላ አሸዋ አስታወሰኝ ያደጉሁባት የሐረር ከተማ፣ የአደሬ ጢቆን አሸዋ። እኔ ራሴ በህፃንነቴ ከመንደር ጓደኞቼ ጋር ሳደርግ የነበረውም ነገር ትዝ አለኝ። እልም እልም አለኝ።

ከጣሊያን በፊት ነው። አንድ እንግሊዝ ነጋዴ በሀረር ከተማ በግምቡ ክልል ውስጥ አንዲት ሱቅ ነበረችው። ቀን ቀን ከሱቅ ይውላል። መኖሪያው ግን በአደሬ ጢቆ፣ ከእኛ ቤት ራቅ ብሎ፣ ከልጅ እያሱ ቤት በላይ ነበር። እንግሊዙ ጧት ወደ ሱቅ የሚሄደው፣

ማታም ወደ ቤቱ የሚመለሰው በብስክሌት ነበረ። በዚያን ዘመን ደግሞ በእኛ አካባቢ ፈረንጅም ቢስክሌትም ታይቶ የማይታወቅ ብርቅ ነገር ነበር። አውቶሞቢልማ አልፎ አልፎ ብቅ ያለ እንደሆን እንደ ታላቅ ተአምር ነበር የሚቆጠረው። የእኛ ሰፈር ህፃናት ቀኑን እስከ አስር ሰዓት ፊደል ስንቆጥር ነው የምንውለው። ከምሳ በፊትና በኋላ ወደ ማታ የኔታችን ሲያስናብቱን ተጠራርተን በአውራ ጎዳናው ዳርና ዳር ቆመን እንጠብቃለን የምንጠብቀው ያንን እንግሊዝና ቢስክሌቱን ነው። እሱም ልክ በሰዓቱ ከጆጎል ብቅ ይልና በቢስኪሌቱ ሆኖ በአውራ ጎዳናው በአደሬ ጢቆ ወደ መኖሪያ ቤቱ ይጓዛል። እኛጋ ሲደርስ ታዲያ ሁላችንም በአንድ ድምፅ "ፈረንጅ ! ፈረንጅ! ፈረንጅ!" እያልን እናወካበታለን። በልጅ አንደበታችን አጅበን እንሸኘዋለን።



## መንግስቱና የሥነ-ጽሑፍ ሽልማት

ብዙ ሰው እንደሚያስታውሰው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ-መንግስት በልማትና በኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ በኢትዮጵያና በአፍሪካ ጥናትና ምርምር ዘርፍ፣ በበጎ አድራጎትና በስነ ጥበባት ዘርፍ የላቀ ተግባር ለፈፀሙና አርአያነት ያለው ጠቃሚ ተግባር ለአከናወኑ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ሰዎች ሽልማት የሚሰጥ አንድ ተቋም በ1955 ዓ.ም. በንጉሰ ነገስቱ ስም ተቋቁሞ ነበር። የዚህ ድርጅት የስነ-ጽሁፍ ተሸላሚዎች ከነበሩት መካከል አራተኛው ተሸላሚ ባለቅኔና ፀሃፊ ተውኔት መንግስቱ ለማ እንደነበሩ ይታወሳል። እንደማንኛውም የሽልማት ድርጅት የአሰራር ደንብና ስርዓት መሰረት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅትም አንድ ተሸላሚ የተዘጋጀለትን ሽልማት ከተቀበለ በኋላ አጠር ያለ ንግግር ማድረግ ይጠበቅበት ነበር። በዚህ መሰረት መንግስቱ ለማም የ1960 የሥነ ጽሁፍ ተሸላሚ ሆነው በመመረጥ የተዘጋጀላቸውን የወርቅ ኒሻንና ዲፕሎማ ከሰባት ሺህ የኢትዮጵያ ብር ጋር ከተቀበሉ በኋላ በንጉሱና በስነ ስርአቱ ታዳሚዎች ፊት ያረጉትን ንግግርና ከሽልማቱ በፊት ስለሳቸው የቀረበውን አጭር መግለጫ በመዘክርነትም ሆነ በማጣቀሻነት የየራሳቸው ዋጋና ጠቀሜታ ይኖራቸዋል በሚል እምነት ከዚህ በታች እንዳለ አስፍረነዋል።

### አቶ መንግስቱ ለማ

አቶ መንግስቱ ለማ በ1921 ዓ.ም ሐረር ተወለዱ። ዜማና ቅኔ በዚሁ ጠቅላይ ግዛት ከተማሩ በኋላ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህታቸውን (ለንደን ስኩል ኦፍ ኤኮኖሚክስ ኤንድ ፖለቲካል ሳይንስ) ቀጠሉ።

አቶ መንግስቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ሆነው ከ1958 ዓ.ም ጀምሮ በዋና ዲሬክተርነት አገልግሎታቸውን ያበረክታሉ።

አቶ መንግስቱ ለማ የአማርኛ ሥነ ጽሁፍ በመሸጋገሪያ ዘመን በሚገኝበት ጊዜ ሲወርድ የመጣውንም የአማርኛ ወዝና ለዛ ሳይለቁ በአዲስ ስልት የሚጽፉ ደራሲ ናቸው።

በጽሑፋቸው ውስጥ ስለ ሕይወት፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ ሞት፣ ስለ ትዝታና ስለ ሌሎችም ዘላቂ ቁም ነገሮች በጥልቅ ስሜት የሚያነሣሱ ብዙ በአማርኛ ግጥሞችን ፅፈዋል። አቶ መንግሥቱ በቀድሞ የአማርኛ የግጥም ስልት ሳይወሰኑ በአዳዲስ መንገድም

የሚጽፉ ደራሲ ናቸው። ለምሳሌ ያህል "የግጥም ጉባኤ" በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ያሉትን ግጥሞች ለመጥቀስ ይቻላል።

በትያትርም ረገድ አቶ መንግስቱ "ያላቻ ጋብቻ"ና "ጠልፎ በኪሴ" በተባሉት የኮሜዲ ጽሑፎቻቸው የጋብቻን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ በጥንቱ ባህልና ወደ አገራችን በገቡ አዳዲስ አሳቦች መካከል የተፈጠረውን ግጭት መልካም አድርገው ገልፀውታል።

አቶ መንግስቱ የሊቁን የአለቃ ለማን የሕይወት ታሪክ "መጽሐፈ ትዝታ" በተባለው ጽሑፍ ሲያቀርቡ ካለፈው ዘመናት እውቀት ከአረጋዊው ቃል በረከት አድርገው ለማስቀረት ችለዋል።

ደራሲው የሊቁን ታሪክ መነሻ በማድረግ የዛሬውን ትውልድ መረሳት የማይገባቸው ከቅኔ፣ ከዜማ፣ ከብሉይ፣ ከሐዲስና፣ ከፍትሐ-ነገስት ትምህርት አባቶች ጋር አስተዋውቀዋል።

በተጨማሪም በተባለው መጽሐፍ ውስጥ የግርጌ ማብራሪያዎች በማስገባት፣ ከባድ ቃላትን በመተርጎም በርከት ያሉ የግእዝ ቅኔዎችን በመፍታትና ሰፋ ያለ የስምና የቃላት ማውጫ በማቅረብ ለመጽሐፍ ጠቃሚ የሆነ ዘመናዊ እቅድ ሰጥተውታል።

ከዚህ በላይ የተገለፀውን የደራሲነት ሙያ መሰረት በማድረግ አቶ መንግስቱ ለማ የ1960 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት የወርቅ ኒሻንና ዲፕሎማ ከሰባት ሺህ የኢትዮጵያ ብር ጋር ተሰጥቶአቸዋል።

<u>የአቶ መንግስቱ ለማ መልስ</u>

የደራሲ ተግባር እንደ ምግባረ ጽድቅ 'ዓላማዊ ዋጋ አገኝበታለሁ ሳይባል ለድርሰትነቱ ብቻ የሚደከምበት ቢሆንም እንደ ጃንሆይ ያለ ገባሬ ሠናያት ይኸንኑ እያወቀ የድርሰትን ሙያ ከፍ ባለ ሽልማት አክብሮ ሲያስከብረው ማየት የሕይወትን ውበት፣ የሰውን ታላቅነት በዓይነ ሰስታ ያስመለክተናል።

በጥንታዊያኑ ታላላቅ የኢትዮጵያ ባለቅኔዎች አንፃር ገና ወጣኒዎች የሆንነው ያሁኑ ዘመን ወጣት ደራሲንና ፀሃፍት ሊቃውንት አባቶቻችንን አርአያ ታዛቢ አድርገን ኅሊናችን ወደያዘነበለበት የድርሰት አቅጣጫ ስንሰማራ ሊያድርብን የሚገባው የይሉኝታ ስሜት መንታ ይሆንብናል።



በመጀመሪያ ደረጃ እነ ክፍለ ዮሐንስ፣ እነ ራስ ወልደገብርኤል፣ እነ አራት ዓይና ጎሹ እነ ማን መልስህ ወደስላሴ፣ እነ ቅኔ ፈጣሪ ወልደ ዮሐንስ፣ እነ ሀብተማሪያም ቅኔ በጉንጩ ምን ይሉኛል? ማለትን እንድናዘወትር፣ ያገራችንን ታሪክ ማንበባችን ያባቶችን ቅርስ መቅመሳችን ያስገድደናል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ግርማዊነትዎ ከዘረጋልን ዘመናዊ ትምህርት ገበታ የቀሰምነው እውቀት፣ እነ ሼክስፒር፣ እነ ሞሊዬር፣ እነ ኢብሠን፣ እነ ቶልስቶይ፣ እነ ቤርናርድሾ፣ እነ ራቢንድራናት ታጎር፣ ምን ይሉኛል? ያሰኘናል።

ለማበረታቻ፣ አይዞህ ለመባያ፣ ከግርማዊነትዎ የተሰጠውን በቀዳማዊ ኃይለሣላሴ ታሪካዊ ስም የተሰየመውን የዚህን ታላቅ ሽልማት ክብርና ከፍተኛ ደረጃ በየበኩላችን ለመጠበቅ የምንችለው፣ መንታውን ይሉኝታ ከብእራችንና ከቀለም ቀንዳችን ያላራቅን እንደሆን ብቻ ነው።

በዚህ በከፍተኛ ጎዳና አዲሱን የኢትዮጵያን ሥነ ጽሑፍ ለማራመድ ደራሲዎች ሁሉ በያቅማችን ለምናደርገው ጥረት የግርማዊነትዎ የደጋፊነት ምሳሌ በሌሎችም አድሮ የድርሰት አፍቃሪያንን ቁጥር እንዲያበረክትልን መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት።
ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ።
ኢትዮጵያችን በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር።